በኢፌዴሪ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል
የግብርና የማዘመን የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ዘርፍ

# የአትክልትና ፍራፍሬ ምርምርና ልማት ፍኖተ ካርታ

መጋቢት 2008 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማዉጫ


1. መግቢያ.....5

1.1 የጥናቱ ዓላማ እና አስፈላጊነት.....6

1.2 የጥናቱ ስልት.....7

2. የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሁኔታ ትንታኔ.....8

2.1 ሀገራዊ ወቅታዊ የሁኔታ ዳሰሳ.....8

2.1.1. የሰዉ ሀይል ልማት.....12

2.1.2. የቴክኖሎጂ ደረጃ.....13

2.1.3. የመሠረተ ልማት አቅርቦት.....17

2.1.4. የሎጀስቲክስ እና የገበያ ልማት.....19

2.1.5. የግል ባለሀብቶች ተሳትፎ.....25

2.1.6. የጥራት እና ደረጃ ሁኔታ.....27

2.2. የቤንች ማርክ ሀገር ሁኔታ.....29

2.2.1. የሰዉ ሀይል ልማት.....30

2.2.2. የቴክኖሎጂ ደረጃ.....30

2.2.3. የመሠረተ ልማት አቅርቦት.....32

2.2.4. የሎጀስቲክስ እና ገበያ ልማት.....33

2.2.5. የግል ባሀብቶች ተሳትፎ.....36

2.2.6. የጥራት እና ደረጃ ሁኔታ.....37

3. የክፍተት ትንታኔ (Gap Analysis).....39

3.1. የሰዉ ሀይል ልማት.....40

3.2. የቴክኖሎጂ ደረጃ.....42

3.3. የመሠረተ ልማት አቅርቦት.....44

3.4. የሎጀስቲክስ እና ገበያ ልማት.....46

3.5. የግል ባለሀብቶች ተሳትፎ.....48

3.6. የጥራት እና ደረጃ ሁኔታ.....49

4. የዘርፉ ተግዳሮቶች እና መልካም አጋጣሚዎች.....50

4.1. በሰው ሃይል ልማት.....51

4.2. የቴክኖሎጂ ደረጃ.....52

4.3. የመሠረተ ልማት አቅርቦት.....53

*4.4. የሎጀስቲክስ እና ገበያ ልማት*......55
*4.5. የግል ባለሀብቶች ተሳትፎ*......57
*4.5.* የጥራት እና ደረጃ ሁኔታ......58
**5. ስትራቴጂያዊ ግቦችና የአፈጻጸም አቅጣጫዎች**......59
*5.1 የአትክልት ልማት እስትራቴጂክ ግቦች እና የአፈፃፀም አቅጣጫዎች*......59
*5.1.1. በመካከለኛ እና በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሃይል ማፍራት*......60
*5.1.2. የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ደረጃ ማሳደግ*......61
*5.1.3. መሰረተ ልማት ማሟላትና አጠቃቀም ማሻሻል*......62
*5.1.4. የተሟላ የሎጂስቲክስ እና ቀልጣፋ የገበያ አገልግሎት ማስፋፋት*......63
*5.1.5. የተደራጁ ወጣቶች እና የግል ባለሀብቶችን ተሳትፎ ማሳደግ*......64
*5.1.6. የአዉሮፓን የጥራት ደረጃ  የሚያሟሉ ምርት ማምረት*......65
*5.2. የፍራፍሬ ልማት እስትራቴጂክ ግቦች እና የአፈፃፀም አቅጣጫዎች*......67
*5.2.1. በመካከለኛ እና በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሃይል ማፍራት*......67
*5.2.2. የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ደረጃ በማሳደግ የኢንዱስትሪ ትስስርን  ማጠናከር*......68
*5.2.3. መሰረተ ልማት ማሟላትና አጠቃቀም ማሻሻል*......69
*5.2.4. የተሟላ የሎጂስቲክስ እና ቀልጣፋ የገበያ አገልግሎት ማስፋፋት*......70
*5.2.5. የተደራጁ ወጣቶች እና የግል ባለሀብቶችን ተሳትፎ ማሳደግ*......71
*5.2.6. የአዉሮፓን የጥራት ደረጃ    የሚያሟሉ ምርቶች ማምረት*......72
**6. ማጠቃለያ - የአትክልት እና የፍራፍሬ ልማት ለኢትዮጵያ ህዳሴ ያለው እንደምታ**......73
ዋቢ (References)......75
ዕዝል (Annex)......78

# አኅፅሮተ ማጠቃለያ (Executive Summary)


ሀገራችን አትክልትና ፍራፍሬ ማምረት ከፍተኛ እምቅ አቅም ያላት ሀገር ብትሆንም ይህን አቅም አሟጦ በመጠቀም እና ለኢኮኖሚ እድገት የላቀ ድርሻ እንዲያበረክት ከማድረግ አንፃር ብዙ አልተጠቀመንበትም፡፡ በኢትዮጵያ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በዋናነት ከአነስተኛ ማሳ ገበሬዎች የሚሰበሰብ ሲሆን በቀዳሚነት ለአምራቹ የቤተሰብ ፍጆታ ታሳቢ በማድረግ የሚመረት ሆኖ ቀሪዉ በጣም አነስተኛ መጠን ለገበያ ይቀርባል፡፡ በተጨማሪ ቁጥራቸዉ በጣም አነስተኛ የሆኑ ባለሀብቶች (commercial farms) የሚመረቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ያሉ ሲሆን ምርቶቻቸዉን በዋናነት ለኤክስፖርት ገበያ የሚዉል ምርቶችን ያመርታሉ፡፡

ኢትዮጵያ በ2006 ዓ.ም 38,667,235.31 ቶን የአትክልት ምርት ያመረተች ሆኖ ከዚህም ውስጥ 126 ሺህ ቶን (0.33 ከመቶ) ኤክስፖርት በማድረግ የተቀረው ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የዋለ ነው፡፡ ዋነኞቹ የሚመረቱ የአትክልት ምርቶች ጎመን፣ ሽንኩርት፣ ቃሪያ፣ ቲማቲም፣ ድንች፣ ጎደሬ፣ ቀይ ስር እና ካሮት ናቸው፡፡ የፍራፍሬ ምርትንም ስንመለከት በ2006 ዓ.ም ሀገሪቷ 4.98 ሚሊዮን ቶን ምርት የተመረተ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 4.97 ሚሊዮን ቶን ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ሲውል የተቀረው 18.6 ሺህ ቶን (0.37 ከመቶ) ደግሞ ለኤክስፖርት የዋለ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ዋነኞቹ የፍራፍሬ ምርቶች የሆኑት ሙዝ፣ ማንጎ፣ አቮካዶ፣ እንጆሪ(ስትሮቤሪ)፣ ሎሚ፣ ብርቱካን፣ አናናስ እና ፓፓያ ናቸው፡፡

ሀገሪቷ ካላት የማምረት አቅም እና ፍላጎት አኳያ ሲታይ አሁን እየተመረተ ያለውም ሆነ ለኤክስፖርት እየዋለ ያለው መጠን እጅግ በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ለዚህም በዋነኛነት የሚጠቀሱት ችግሮች በቂ የሰለጠነ የሰው ሀይል እጥረት፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና ደረጃ ዝቅተኛ መሆን፣ የሎጀስቲክስ እጥረት፣ የዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃን ያልጠበቀ ምርት ለገበያ በስፋት ማቅረብ አለመቻል እና በዘርፉ የባለሀብቶች ተሳትፎ አነስተኛ መሆን ናቸው፡፡ ዘርፉን ለማዘመን እና በቀጣይነት እንዲያድግ በማድረግ ለሀገራችን ህዳሴ የበኩሉን እንዲያበረክት ለማድረግ ሀገሪቷ ያላትን ዕምቅ አቅም አሟጦ በመጠቀም እና የዘርፉን ተግዳሮቶች በመፍታት ትኩረት ሰጥቶ በመስራት በግብርና ዘርፍ የታየዉን እድገት ማስቀጠል፣ ለወጣቶች ተጨማሪ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የግብርናና ኢንዱስትሪ ትስስር ማጠናከር እና የተሻለ የዉጭ ምንዛሪ ማስገኘት ያስችላል፡፡

# ክፍል አንድ

## 1. መግቢያ

የሆርቲካልቸር ዘርፍ ነባር የግብርና ዘርፍ ቢሆንም በአገራችን የዘመናዊ የሆርቲካልቸር አመራረት ታሪክ ከአራት አስርት አመታት የሚዘል አይደለም፡፡ ግብርና ለሀገራችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ዋነኛ የትኩረት ማዕከል ስለሆነ የሚፈለገው መዋቅራዊ ሽግግር ወደ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ሰብሎች አመራረትና የግብርና ኮሜርሻላይዜሽን ቢሆንም ፍጥነቱ ከሚፈለገው አንፃር አሁንም በጣም አዝጋሚ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሌሎች ሀገሮችን ተሞክሮ ስንመለከት ወደ ከፍተኛ እሴት ያለው የግብርና ውጤት እና የዳበረ አግሮኢንዱስትሪ ግንባታ ለመሸጋገር ዋናው ስትራቴጂ በሆርቲካልቸር ሰብሎች ላይ የሚደረገው ዘርፈ ብዙ ለውጥ እንደሆነ እንረዳለን፡፡

በኢትዮጵያ በምርት መጠንና በሚመረትበት የመሬት ስፋት እንዲሁም በኤክስፖርት ዘርፍም ድርሻ ካላቸው የአትክልት ምርት ዓይነቶች ውስጥ ቲማቲም፣ ጎመን፣ ድንች፣ ካሮት፣ ፎሶሊያ እና ቃሪያ ሲሆኑ የፍራፍሬ ዓይነቶች ደግሞ ማንጎ፣ ሙዝ፣ አቮካዶ፣ ኢንጆሪ፣ መንደሪን፣ አናናስ፣ አፕል፣ ሎሚ፣ ፓፓያና ወይን ናቸዉ፡፡ የተለያየ አየር ፀባይ፣ የመሬት አቀማመጥ፣ ለም አፈር፣ በቂ የዕርጥበት መጠን እና ሰፊ የሰዉ ጉልበት ያላት ሀገር በመሆንዋ በአለም ገበያ ተወዳዳሪ የሆነ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ትልቅ እድል ያላት ሀገር እንደሆነች ይታወቃል፡፡

የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት 95 ከመቶ በአነስተኛ ማሳ ላይ የሚመረት ሲሆን አምስት ከመቶ በሰፋፊ ኮሜርሻል እርሻ ላይ ነዉ፡፡ በኮሜርሻል እርሻዎች የሚመረቱት አትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በትላልቅ ከተሞች የሚቀርቡ ሲሆን ወደሌሎች ሀገራት በተለይ አዉሮፓ፡ መካከለኛ ምስራቅ እና ጎረቤት የአፍሪካ ሀገራት ኤክስፖርት ይደረጋል፡፡ በአርሶ አደሮች የሚመረቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በአምራቹ በፍጆታና ሌሎች ጠቀሜታ የሚውል ሲሆን በጣም አነስተኛ ምርት ለተጨማሪ ገቢ ማስገኛ በአካባቢው ገበያ ለፍጆታ ይሸጣል፡፡ በማዕከላዊ ስታቲክስ ኤጀንሲ የ2006 ዓ.ም የምርት አጠቃቀም መረጃ የሚያሳየው ከተመረተው የአትክልት ምርቶች ውስጥ 19.3% እና ከቋሚ ሰብሎች ምርቶች ፍራፍሬና ቡናን ጨምሮ በአማካይ 40% ወደ ወደ ገበያ እንደሚወጣ ያመለክታል፡፡

በ2006 ዓ.ም የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ እና የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ መረጃ እንደሚያመለክተዉ ከሆነ ከሚመረተዉ የአትክልት ምርቶች ውስጥ 99.7% እና የፍራፍሬ ምርቶች 99.6% ለሀገር ዉስጥ ገበያ የቀረበ ሲሆን 126.46 ሺ ቶን የአትክልት ምርቶች እና 18.65

ሺ ቶን የፍራፍሬ ምርቶች ወደ ዉጭ ሀገር በመላክ 45.72 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (39.78 ከአትክልት እና 5.94 ከፍራፍሬ) የዉጭ ምንዛሪ አግኝታለች (CSA,2014 እና EHDA, 2014)፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ለሀገር ዉስጥም ሆነ ለዉጭ ገበያ የቀረበዉ የምርት መጠን ሀገሪቷ ካላት እምቅ የማምረት አቅም እና የተወዳዳሪነት ሁኔታ ሲታይ ብዙ ወደፊት መራመድ የሚችል ሴክተር እንደሆነ ያሳየናል፡፡

ለኤክስፖርት ገበያ ምርቱ እንዳያድግ ዘርፉን የያዙ ብዙ ችግሮች ያሉ ቢሆንም በዋናነት ሊጠቀሱ የሚችሉት የምርታማነት ማነስ፣ በጥራት ያለማምረት፣ የተሻሻሉ ግብአቶች አለመጠቀም፣ የባለሙያዎች ድጋፍ አናሳ መሆን እና የሎጀስቲክስ እጥረት መኖር ናቸዉ፡፡ እነዚህንና ሌሎች በየወቅቱ የሚታዩትን ችግሮች እና ተግዳሮቶችን ነቅሶ በመለየት እና የተመረጡ የመፍትሄ ሀሳቦችን በመተግበር በዘርፉ ልማት ላይ ጉልህ ለዉጥ ማምጣት ይቻላል፡ ያስፈልጋልም፡፡

በዚህ መሠረት ይህ ፍኖተ ካርታ በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ሀገሪቱ ያላትን እምቅ አቅም መሠረት በማድረግ እና ለቀጣይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶች እና የመፍትሄ ሀሳቦችን በመለየት ሀገሪቷ የዘርፉን ምርት በብዛት እና በጥራት ለዓለም ገበያ በመላክ ከፍተኛ የዉጭ ምንዛሪ እንድታገኝ በሚደረገዉ ጥረት ዉስጥ ለ2ኛዉ (እትዕ) እና ለ3ኛ ዕትእ የፖሊሲ ግብዓት የሚሆን ሀሳቦችን በማቅረብ ዘርፉን ለማዘመን የተዘጋጀ ፍኖተ ካርታ ነዉ፡፡

## *1.1 የጥናቱ ዓላማ እና አስፈላጊነት*

በዋናነት ይህ ጥናት በኢትዮጵያ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ለማሳደግ የሚያግዙ የፖሊስ ሀሳቦችን በማመንጨት ለመንግስት በማቅረብ ለሁለተኛዉ እና ለሶስተኛዉ የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ (ለሚቀጥሉት 10 አመታት) ግብአት ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም የፖሊሲ ሃሳብ ለማቅረብ የዘርፉን ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀት አስፈላጊ ስለሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርምርና ልማት ሁኔታ በቅድሚያ ለማጥናት ነው፡፡ ዝርዝር የጥናቱ ሂደት ውስጥ የዘርፉን ምርት እና ምርታማነት ዕምቅ አቅም መዳሰስ፤ ለኢትዮጵያ የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርቶች የዓለም አቀፍ ገበያ መዳረሻዎችን እና የጥራት ደረጃዎችን መለየት፤ በዘርፉ ስኬታማ የሆኑት ሀገራትን ልምድ በመቀመር እና ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛማድ ተሞክሮ መቅሰም፤ ዘርፉ በማምረት እና ኤክስፖርት በማድረግ ዙርያ ያሉትን ተግዳሮቶች እና ክፍተቶችን በመለየት

ስትራቴጂካዊ የመፍትሄ ሀሳቦችን ማስቀመጥ እና በዘርፉ ኤክስፖርት በሚያድግበት ሁኔታ ላይ የፖሊሲ ሀሳብ ማመንጨት ናቸዉ፡፡ በዚህ ፍኖተ ካርታ ሰነድ ውስጥ የሚካተቱ የትግበራ አቅጣጫዎች በባለቤትነት የሚያስፈፅመዉ ተቋም ይህንን የመነሻ ሰነድ አዳብሮ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ፣ ፕሮግራምና ፕሮጀክቶች እንደሚነድፍ ይጠበቃል፡፡

## *1.2* የጥናቱ ስልት

ይህ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ፍኖተ ካርታ በቀጣይ አስር ዓመታት በሀገሪቱ በዘርፉ ያለዉን ልማት የሚያመለክት ሲሆን ጥናቱ የተጠቀመዉ ስልት የሀገር ዉስጥ እና የቤንችማርክ ሀገር የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ነባራዊ ሁኔታ በመዳሰሳ በዘርፉ ያሉትን ክፍተቶች፣ ተግዳሮቶች እና መልካም አጋጣሚዎችን በመለየት የዘርፉን እድገት የሚያመለክት ስትራቴጂክ ግቦች እና የአፈጻጸም አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ ነዉ፡፡ ለዚህ ጥናት መረጃዎችን በዋናነት ከሚመለከታቸው የመንግስት ሴክተር መስሪያ ቤቶች፣ ከታተሙ እና ካልታተሙ በዘርፉ የተደረጉ ቀደምት ጥናቶች፣ በዘርፉ በሀገር ዉስጥ ያሉትን የልማት ፀጋዎች በመስክ በመጎብኘት እና የመረጃ መረብን በመጠቀም የተሰበሰቡ ሲሆን፣ የተገኙትንም መረጃዎች ለመቀመርና ለመተንተን የተለያዩ ዘዴን (Qualitative and quantive analysis) ጥቅም ላይ ዉለዋል፡፡

# ክፍል ሁለት

## *2. የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሁኔታ ትንታኔ*

የአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ በሀገራችን ግብርና ውስጥ ፈጣን መዋቅራዊ ለውጥ እንዲያመጣ የሀገር ውስጥ የዘርፉን ሁኔታ ከማየት በተጨማሪም የሌሎች በዘርፉ መልካም ተሞክሮ ያላቸውንም ሀገሮች ሁኔታ በመዳሰስ እና የነሱን ተሞክሮ ቤንች ማርክ በማድረግ መስራትን ይጠይቃል፡፡ በዚሁ መሰረት አትክልትና ፍራፍሬ ልማት ከሀገራችን እና መልካም ተሞክሮ ካላቸው ከሌሎች ሀገሮች ሁኔታ እንደሚከተለው ተዳሷል፡፡

### *2.1 ሀገራዊ ወቅታዊ የሁኔታ ዳሰሳ*

የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ሥራ በመላው ሀገሪቱ ሊባል በሚችል መልኩ የሚተገበር የግብርና ዘርፍ ነው፡፡ በ2006 ዓ.ም በኢትዮጵያ 164,731.69 ሄክታር መሬት የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን ለማምረት ጥቅም ላይ ዉሎ በአጠቃላይ 5,838,636.23 ቶን ምርት ማግኘት ተችሏል (CSA, 2014)፡፡ ከምርት ዓመቱ ቀደም ብሎ ካለው አምስት ዓመት የምርት ሁኔታ አኳያ ሲታይ የ18 ከመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ በ2006 ዓ.ም ከተመረተው ምርት ውስጥ 145,110 ቶን ኤክስፖርት ተደርጎ 45.72 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተገኝቷል (EHDA,2014)፡፡

በኢትዮጵያ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በዋናነት ከገበሬዎች ማሳ የሚሰበሰብ ሲሆን በቀዳሚነት ለአምራቹ የቤተሰብ ፍጆታ ታሳቢ በማድረግ የሚመረት ሲሆን የቀረዉ በቤተሰብ ደረጃ በጣም አነስተኛ በሚባል መጠን ለገበያ ይቀርባሉ፡፡ በተጨማሪም እንደ ሀገር ቁጥራቸዉ በጣም አነስተኛ የሆነ በባለሀብቶች/ኢንቨስተሮች (commercial farms) የሚመረቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ያሉ ሲሆን ምርቶቻቸዉን ለኤክስፖርት ገበያ የሚዉል ምርቶችን ያቀርባሉ፡፡

በኢትዮጵያ የተለያዩ ስነምህዳሮች ከመኖራቸዉ ጋር ተያይዞ ብዙ ዓይነት የአትክልት ምርቶች በማምረት ትታወቃለች፡፡ በ2006 ዓ.ም ያለዉን መረጃ እንኳን ስናይ በሀገሪቱ 846,798.6 ቶን

የአትክልት ምርቶች እና 37,820,436.71 ቶን የስራስር ምርቶች ተመርተዋል፡፡ መረጃዉ እንደሚያሳየዉ የስራስር ምርቶች አብላጫውን ድርሻ የሚይዝ ሲሆን ከነዚህም ስኳር ድንች፣ ጎደሬ፣ ድንች፣ ቀይ ስር እና ካሮት ከከፍተኛ እስከ ዝቅተኛ የምርት መጠን በመያዝ በተመሳሳይ ዓመት የተመረቱ ናቸው፡፡ በተመሳሳይ ዓመት ሌሎች የአትክልት ምርቶችን ስናይ የአበሻ ጎመን፣ ቀይ ሽንኩርት፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ቃሪያ፣ ቲማቲም፣ ጥቅል ጐመን እና ሰላጣ በምርት መጠናቸው በቅደም ተከተል ከከፍተኛ እስከ ዝቅተኛ ይዘዉ የተመረቱ ናቸዉ (ሠንጠረዥ 1)፡፡ በኢትዮጵያ በዘርፉ የተደረጉት ጥናቶች እንደሚያሳዩን ከሆነ የአትክልት አማካይ ምርት እና ምርታማነት ካለው አቅም እና ከሌሎች ሀገሮች አኳያ ሲታይ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ በ2006 ዓ.ም ያለው መረጃ እንደሚያሳየው ከሆነ የአትክልት ምርታማነት በአማካይ 192 ኩ/ሄ ሆኖ ተመዝግቧል (EIA 2012; CSA, 2014)፡፡

ሠንጠረዥ 1፡ የኢትዮጵያ አትክልት ምርት እና ምርታማነት (2004 – 2006)

| ሰብል | 2004 የምርት ዘመን | | | 2005 የምርት ዘመን | | | 2006 የምርት ዘመን | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የመሬት ሽፋን በሄክታር | የምርት መጠን በቶን | ምርታማነት (ቶን/ ሄክታር) | የመሬት ሽፋን በሄክታር | የምርት መጠን በቶን | ምርታማነት (ቶን/ ሄክታር) | የመሬት ሽፋን በሄክታር | የምርት መጠን በቶን | ምርታማነት (ቶን/ ሄክታር) |
| አትክልት | 95001.27 | 968393 | | 77917.01 | 754799.6 | | 93224.56 | 846798.6 | |
| ሰላጣ | 163.54 | 404 | 2.5 | 75.01 | መ.የ. | መ.የ. | 239.88 | 592.59 | መ.የ. |
| ጥቅል ጎመን | 4,802.90 | 43,483.90 | 9.1 | 3,049.01 | 23,224.70 | 7.6 | 3,961.84 | 27,018.83 | 6.8 |
| የአበሻ ጎመን | 31,783.56 | 323,180.50 | 10.2 | 34,791.05 | 370,995.20 | 10.7 | 34,503.80 | 360,327.16 | 10.4 |
| ቲማቲም | 7,255.93 | 81,738.10 | 11.3 | 7,237.35 | 55,514.30 | 7.7 | 7,257.45 | 39,373.02 | 5.4 |
| ቃሪያ | 6,970.87 | 65,766.80 | 9.4 | 10,588.52 | 85,547.80 | 8.1 | 6,167.47 | 41,250.36 | 6.7 |
| ቆስጣ | 267.57 | 1,700.80 | 6.4 | 310.7 | 329 | 1.1 | 307.23 | መ.የ. | መ.የ. |
| ቀይ ሽንኩርት | 30,478.35 | 328,157.40 | 10.8 | 21,865.37 | 219,188.60 | 10 | 24,375.70 | 219735.27 | 9.0 |
| ነጭ ሽንኩርት | 13,278.55 | 123,961.50 | 9.3 | 21,258.43 | 222,547.90 | 10.5 | 16,411.19 | 159,093.60 | 9.7 |
| ስራስር | 153,002.44 | 12,189,110.76 | 334.11 | 160,834.33 | 32,340,671.49 | 1,214.67 | 166,017.14 | 37,820,436.71 | 858.99 |
| ቀይ ስር | 2484.96 | 245430.49 | 98.77 | 1795.25 | 168485.13 | 93.85 | 1643.15 | 140749.38 | 85.66 |
| ካሮት | 0.00 | 135,502.63 | * | 1,132.94 | 510,467.00 | 450.57 | 1,602.46 | 67,120.34 | 41.89 |
| ድንች | 59,508.67 | 4,754,405.46 | 79.89 | 74,934.57 | 8,633,477.92 | 115.21 | 66,745.61 | 7,849,934.00 | 117.61 |
| ጎደሬ | 39,695.59 | 3,152,420.66 | 79.41 | 41,337.62 | 11,177,733.55 | 270.40 | 42,656.73 | 11,935,383.02 | 279.80 |
| ስኳር ድንች | 51,313.22 | 3,901,351.52 | 76.03 | 41,633.95 | 11,850,507.89 | 284.64 | 53,369.19 | 17,827,249.97 | 334.04 |

ምንጭ፡ CSA 2014

ለኤክስፖርት የሚዉሉ የኢትዮጵያ ፍሬሽ የአትክልት ምርቶች በዋናነት ለጅቡቲ እና በጅቡቲ በኩል ለመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት የሚላኩ ናቸዉ፡፡ እነዚህ ምርቶች ከመላዉ ሀገሪቱ ከግል ባለሀብቶች ማሳ እና ከገበሬወች ማሳ የሚሰበሰቡ ሲሆን በዋናነት ከምሥራቅ ሀረርጌ፣ ከድሬደዋ አቅራቢያ ወረዳዎች፣ እና ከስምጥ ሸለቆ ሀይቆች አከባቢ ነው፡፡ ከገበሬዎች ማሳ የሚሰበሰቡ ምርቶች በደላላዎች ይሁንታ በሚወሰን መልኩ ከተሰበሰቡ በኋላ በቀጥታ በትላልቅ መኪናዎች ተጭነው ጅቡቲ ወደብ ላይ ይደርሳሉ፡፡

ወደ መካከለኛው ምሥራቅ እና አጎራባች ለሆኑ የአፍሪካ ሀገራት የሚላኩት የአትክልት ምርቶች ቲማቲም፣ ሽንኩርት፣ ጐመን እና ድንች ሲሆኑ ወደ አውሮፓ ሀገራት የሚላከው ግን በዋናነት green “bobby” beans ሲሆን ዋና መዳረሻቸውም ኔዘርላንድ እና ጣሊያን ናቸው፡፡ በተጨማሪም ለአውሮፓ ገበያ ሲባል Peas, Mangetouts, Cherry tomatoes እና asparagus በአንዳንድ በለሀብቶች ለሙከራ የማምረት እና የመላክ ጅምሮች አሉ፡፡

ከገበሬዎች ማሳ ተሰብስበዉ ኤክስፖርት የሚደረጉ ምርቶች ምንም እሴት ሳይጨመርባቸው እንደተመረቱ በጅምላ የሚላኩ እና ሲመረቱም ሆነ ሲጓጓዙ በቂ ጥንቃቄ እና አስፈላጊው እንክብካቤ ስለማይደረግላቸው ሲሸጡ ዋጋቸው ዝቅተኛ ነዉ፡፡ ኤክስፖርት የሚደረጉት የአትክልት ምርቶች በብዛትም ሆነ በጥራት ሀገሪቷ ካላት አቅም አንፃር ሲታይ በጣም አነስተኛ ከመሆኑ አንፃር የሚጠበቀውን ያህል የውጭ ምንዛሪ ለሀገሪቷ እያስገኘ አይደለም፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የኢትዮጵያን የፍራፍሬ ምርት እና ምርታማነትን ስናይ በመላዉ ሀገሪቱ ለፍራፍሬ ምርት ምቹ የሆኑ የተለያዩ ስነምህዳሮች ስላሉ የተለያዩ የወይና ደጋ (temperate) እና የቆላ (tropical) ፍራፍሬዎች ለማምረት ከፍተኛ ዕምቅ አቅም አላት፡፡ በሠንጠረዥ 2 እንደተመለከተው በ2006 ዓ.ም የምርት ዘመን 71,507.13 ሄክታር መሬት ለፍራፍሬ ምርት ዉሎ 4,991,838 ቶን የምርት መጠን የተገኘ ሲሆን ምርታማነታቸውንም በአማካይ 134.07 ኩ/ሄ ነበር (EIA, 2012, CSA 2014)፡፡ በምርት ዘመኑ ከተመረቱት የፍራፍሬ ዓይነቶች በዋናነት አቮካዶ፣ ሙዝ፣ ዘይቱና፣ ማንጎ፣ ሎሚ፣ ብርቱካን፣ ፓፓያ እና አናናስ ይገኙበታል፡፡ እነዚህ የፍራፍሬ ምርቶች በየገበሬዎች ማሳ በቅይጥ ግብርና (mixed agriculture) እና በባለሀብቶች ኮሜርሻል እርሻዎች ላይ የተመረቱ ናቸዉ፡፡

ሠንጠረዥ 2፡ በኢትዮጵያ የፍራፍሬ ምርት እና ምርታማነት (2004 – 2006 ዓ.ም)

| ፍራፍሬ | 2004 የምርት ዘመን | | | 2005 የምርት ዘመን | | | 2006 የምርት ዘመን | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የመሬት ሽፋን በሄክታር | የምርት መጠን በቶን | ምርታማነት (ቶን/ ሄክታር) | የመሬት ሽፋን በሄክታር | የምርት መጠን በቶን | ምርታማነ ት (ቶን/ ሄክታር) | የመሬት ሽፋን በሄክታር | የምርት መጠን በቶን | ምርታማ ነት (ቶን/ ሄክታር) |
| አቮካዶ | 9,023.91 | 73,096.80 | 8.1 | 8,938.24 | 25,633.20 | 2.9 | 10,590.59 | 18,206.36 | 1.7 |
| ሙዝ | 35,869.31 | 291,257.70 | 8.1 | 36,012.19 | 302,502.20 | 8.4 | 41,356.88 | 340,012.58 | 8.2 |
| ዘይቱን | 1,357.15 | 2,215.00 | 1.6 | 1,492.32 | 1,173.00 | 0.8 | 2,039.71 | 850.28 | 0.4 |
| ማንጎ | 8,058.28 | 72,752.90 | 9 | 8,808.64 | 69,750.70 | 7.9 | 10344.51 | 4,660.95 | 0.5 |
| ሎሚ | 894.36 | 8,160.30 | 9.1 | 754.23 | 5,516.80 | 7.3 | 1128.15 | 72,186.98 | 64.0 |
| ብርቱኳን | 3,609.67 | 48,750.50 | 13.5 | 2,999.21 | 35,745.80 | 11.9 | 3,244.80 | 31,182.65 | 9.6 |
| ፓፓያ | 2,496.41 | 42,573.30 | 17.1 | 2,752.08 | 38,694.30 | 14.1 | 2,467.63 | 31,588.25 | 12.8 |
| አናናስ | 163.66 | 532.3 | 3.3 | 215.69 | መ.የ. | መ.የ. | መ.የ. | መ›የ. | መ.የ. |
| **አጠቃላይ** | **61,472.75** | **539,338.80** | | **61,972.60** | **479,016** | | **71,507.13** | **4,991,838** | **69.8** |

ምንጭ፡ CSA 2014

ከኢትዮጵያ ኤክስፖርት የሚደረጉ የፍራፍሬ ምርቶችን ከአትክልት ምርቶች ኤክስፖርት ጋር ስናስተያየዉ በመጠንም ሆነ በዋጋ ያነሰ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ አብዛኛዎቹ የፍራፍሬ ምርቶች በጅቡቲ ወደብ በኩል ወደ መካከለኛው ምስራቅ የሚላኩ ሲሆን ወደ አውሮፓ ገበያ የሚላኩ ቢኖሩም መጠናቸዉ በጣም ትንሽ ነዉ፡፡ ለኤክስፖርት ከኢትዮጵያ የሚመረቱ ምርቶች በዋናነት ሙዝ፣ ሲትረስ፣ ወይን፣ ማንጎ፣ ፓፓዬ እና አቮካዶ ናቸው፡፡ የምርቶቹ የገበያ መዳረሻዎች ጅቡቲ፣ ሳኡዲ አረቢያ፣ እና የመን ናቸው፡፡ ግን ይህ ነው የሚባል አይደለም፡፡ የመካከለኛ ምስራቅ ሀገሮች በራሳቸው የሚያመርቱት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ቢመጣም የሀገር ዉስጥ ፍላጎታቸዉ በከፍተኛ መጠን እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ ያለውን የገበያ ፍላጎት ማሟላት ስለማይችሉ በሀገራችን የሚፈለገዉን የጥራት ደረጃ አሟልተን ብናመርት በገበያው ጥሩ ተወዳዳሪ ሆነን መዝለቅ እንደምንችል በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች ያሳያሉ (EHDA, 2013; Zuurbier, 2013)፡፡

የኢትዮጵያ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ሀገራዊ ወቅታዊ ሁኔታን ለመዳሰስ የዘርፉን አስቻይ ሁኔታዎችን ማለትም  የሰዉ ሀይል ልማት፣ የቴክኖሎጂ ደረጃ፣ የመሰረተ ልማት፣ የሎጀስቲክስ አቅርቦት፣ የጥራት ደረጃ እና የግል ባለሀብቶች ተሳትፎ ሁኔታ ማወቅና ማጎልበትን ስለሚጠይቅ እንደሚከተለዉ ተዳሰዋል፡፡

### 2.1.1. የሰዉ ሀይል ልማት

እንደሌሎቹ የግብርና ሥራዎች ሁሉ በኢትዮጵያ የአትክልትና ፍራፍሬ ሥራ በዋናነት በገበሬዎች ማሳ ላይ የሚከናወን ቢሆንም በባለሀብቶች የሚሰሩ ኮሜርሻል የአትክልትና ፍራፍሬ እርሻዎችም በሀገሪቷ ይገኛሉ፡፡ በዚህ ሥራ ላይ የተሰማሩትን የሰው ኃይል ብዛት፣የሙያ ስብጥር እና የትምህርት ደረጃ መረጃ ማግኘት ከባድ ቢሆንም በዉስን ደረጃ መሳተፍ ከጀመሩት ባለፊ ዘርፉ በሚፈልገው ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል ግን እንደሌለው ለማወቅ የሚያስቸግር አይደለም፡፡ የአርሶ አደሮች የአትክልትና ፍራፍሬ አመራረት በተለምዶ ከቤተሰቦቻቸው እና ከአካባቢ በቀሰሙት እዉቀት እና ባካበቱት ልምድ የሚሰሩ ሲሆን ዘመናዊ የአሰራር ዘዴን ግን አይደለም፡፡ ከዚህም የተነሳ የዘርፉ ምርት አነስተኛ እና ከፍተኛ ጥራት የገደለዉ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በዘርፉ የሀገሪቷን የተወዳዳሪነት አቅም ጎድቷል፡፡

በሀገሪቱ የከፍተኛ ትምህርት ማዕከላት ካለፉት 10 ዓመታት ወዲህ በሆርቲካልቸር ትምህርት ዘርፍ በብዛት ተማሪዎችን በተለያየ ደረጃ እያሰለጠኑ ይገኛሉ፡፡ የ2006 የኢትዮጵያ ትምህርት ሚኒስትር ሪፖርት (MOE, 2006) እንደሚያሳየው 13 ዩኒቨርስቲዎች በሆርቲካልቸር ሳይንስ ዘርፍ በመጀመሪያ ዲግሪ ሥልጠና እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ዩኒቨርስቲዎች ከሚሰጡት ቅድመ ምረቃ (Under Graduate) ትምህርት በተጨማሪ በዘርፉ በሁለተኛ እና በሶስተኛ ዲግሪ (Post Graduate) የትምህርት መርሃ ግብሮችን በመከፈት በዘርፉ ለሚያስፈልገዉ የሰዉ ሀይል የድርሻቸዉን እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡ ከዩኒቨርስቲዎች በተጨማሪም በሀገሪቷ የተለያዩ ክልሎች የተቋቋሙ የግብርና ቴክኒክ እና ሙያ ኮሌጆች በሆርቲካልቸር ትምህርት መርሃ ግብር በሰርቲፊኬት እና በዴፕሎማ ደረጃ በማሰልጠን ላይ ይገኛሉ፡፡

እነዚህ ከዩኒቨርስቲም ሆነ ከቴክኒክ እና ሙያ ኮሌጆች የሚመረቁ የሰው ኃይል ቁጥራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ቢሆንም ዘርፉን ለማሳደግ እና ለማዘመን ከሚፈለገው አንፃር ሲታይ ግን አሁንም በቂ የሰለጠነ የሰው ኃይል በዘርፉ እንደሌለ የሚታይ ሀቅ ነው፡፡ ያሉትም የዘርፉ የዩኒቨርስቲ ምሩቃን በብዛት በፌደራል፣ በክልሎች እና በዞኖች ደረጃ ተመድበው እየሰሩ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በቀበሌ እና በወረዳ ደረጃ በመገኘት በቅርበት ለአርሶ አደሮች እና ለባለሀብቶች የተሻለ የሙያ ድጋፍ ከመስጠት አኳያ ግን አሁንም በሀገራችን ትልቅ ክፍተት አለ፡፡ በድህረ ምረቃ ደረጃ የተማሩትም ቢሆኑ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በማስተማር ስራ

በብዛት ተጠምደው ያሉ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በቅርበት በዘርፉ የሚታዩትን ችግሮች ከመፍታት አንፃር የጎላ ችግር ይታይባቸዋል፡፡

የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት በተለያዩ ሙያዎች የሰለጠኑ ሙያተኞች ከመፈለጉ ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ አሁን ያለው የሰለጠነ የሰው ሀይል ዘርፉን ለማሳደግ የሚያስችል ደረጃ ላይ አይደለም፡፡ የሰው ሀይል ጉዳይ ሲነሳ የተመራቂዎች ብዛት ብቻ ሳይሆን ዋናው ጉዳይ የተመረቁትም ቢሆኑ ዘርፉ የሚፈልገውን እውቀት እና ክህሎት መያዝን ማረጋገጥ ስለሚያስፈልግ ጭምር ነው፡፡ በዚህ ረገድ በዘርፉ ከተሰማሩት አንዳንድ ቀጣሪ ባለሀብቶች በመስክ ጉብኝት ወቅት መረዳት እንደተቻለው አንዳንድ ከከፍተኛ ትምህርት ተመርቀዉ ለስራ ወደ እነሱ የሚሄዱ በዘርፉ በቂ ክህሎት እና ችሎታ የሌላቸው እንደሚያጋጥማቸው እና ተመራቂዎቹን ከመቅጠር ይልቅ በሥራ ላይ የተለማመዱ (ምሩቃን ያልሆኑ) ሠራተኞችን ለመቅጠር እንደሚገደዱ መረዳት ተችሏል፡፡

አትክልትና ፍራፍሬ አምራች አርሶ አደሮችን በኤክስቴንሽን ከመደገፍ አንፃር ሲታይ በየቀበሌው የተመደቡ የልማት ሠራተኞች ያሉ ቢሆንም በሆርቲካልቸር ዘርፍ በቂ የሚባል የትምህርት ዝግጅት ስለሌላቸው በሚፈለው መጠን አምራቾቹን ሊደግፉ አልቻሉም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ የልማት ሰራተኞች የሰብል እና የእንስሳትን ምርት ለማሳደግ ትኩረት ሰጥተዉ የሚሰሩ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚሰጡት ምክር እና ድጋፍ አናሳ ነው፡፡

## *2.1.2. የቴክኖሎጂ ደረጃ*

የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት እና ምርታማነት ለማሳደግ የቴክኖሎጂ ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የአትክልት  እና ፍራፍሬ ምርት ለዘመናት ኋላ ቀር በሆኑ ቴክኖሎጂዎች ላይ በመመሥረት ሲመረት መቆየቱ ይታወቃል፡፡ እነዚህ ቴክኖሎጂዎች የሰዉ ጉልበትን ከመቆጠብ እና ለተወሰነ ምርት መገኘት የራሳቸው ድርሻ ቢኖራቸውም አሁን ዘመኑ ከደረሰባቸው ዘመናዊ የማምረቻ ዘዴዎች ጋር ሲነፃፀሩ ግን ምርት የሚያባክኑ፣ የምርቱን  ጥራት የማያረጋግጡ እና አምራቾቹን  ተወዳዳሪ የሚያደርጉ አይደሉም፡፡

የዘርፉን ምርት እና ምርታማነትን በመጨመር እንደ ሀገር ተወዳዳሪ ለመሆን ዘመኑ ያፈራቸው ቴክኖሎጂዎች ማላመድ እና መጠቀም አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነዉ፡፡ በአትክልትና ፍራፍሬ ረገድ ያሉ ቴክኖሎጂዎች በአንደኛ ደረጃ ስነ ሕይወታዊ ቴክኖሎጂዎች ማለትም ዝርያን ማሻሻል ወይም

አዲስ በማግኘት የተሻለ ምርት የሚሰጥ በሽታን የሚቋቋም ወይም ድርቅን የሚቋቋም ቴክኖሎጂ ሊሆን ይችላል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ቴክኖሎጂው የኬሚካል ቴክኖሎጂ ማለትም ማዳበሪያ፡ የተባይ እና የአረም መቆጣጠሪያ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በሦስተኛነት ሊጠቀስ የሚችለዉ መካኒካል የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀሙ የማምረት ስርዓት ሲሆኑ እነሱም የእርሻ መሳሪያዎች (Farm Machinery) እና የእርሻ ቁሳቁሶች (Farm Equipment) ናቸው፡፡ አራተኛ እና የመጨረሻው የዘርፉ የቴክኖሎጂ ዓይነት የሥራ አመራር አስተዳደራዊ ቴክኖሎጂዎች (Management Technology) ሲሆን እሱም የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ሥራ ለመምራት የሚያስችል ዕውቀት እና ክህሎት ነው፡፡

በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ዘመናዊ ቴክኖሎጂ መጠቀም ግድ ከሚሉ ሥራዎች ዉስጥ የመስኖ አጠቃቀም፣ የማዳበሪያ አጠቃቀም፣ የማሳ ዝግጅት፣ ዝርያን የማባዛት እና የቲሹ ካልቸር አጠቃቀም ወሳኞቹ ናቸው፡፡ ከቫይረስ እና ከባክቴሪያ ነፃ የሆነ ችግኞችን ማባዛት እና ማግኘት በተለይም በእንጆሪ፣ በድንች እና በሙዝ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ መግረዝ (Shoot tip grafting) በሲትረስ ፍራፍሬዎች ምርትን ለመጨመር የሚረዳ የዘመኑ ቴክኖሎጂ ሲሆን ምርት ጥራትን በማሻሻል ትልቅ ድርሻ አለዉ፡፡ በባዮ ቴክኖሎጂ በተለይም በጄነቲክ ኢንጅነሪንግ እና ፕሮቶፕላስት ፊዩዥን (Protoplast fusion) በመጠቀም የምንፈልገውን ባሕሪ በመቀየር በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚፈለገዉን የምርት መጠን እና ባሕሪ ያለዉ ምርት ማግኘት እንችላለን፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም በኢትዮጵያ እንደ ሀገር በአነስተኛ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ፡፡

ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች የመስኖ ቴክኖሎጂ ከመጠቀም አኳያ ሲታይ የመስኖ ውሃ መጠቀም በኢትዮጵያ የተለመደ ቢሆንም አርሶ አደሮች በመስመር ውሃ መልቀቅ (Furrow irrigation) እና ውሃ በማጥለቅለቅ (Flood irrigation) በብዛት ይጠቀማሉ፡፡ ይህ ዓይነቱ የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ግን ውሃን የሚያባክንና የእርሻ መሬትን ለምነት ስለሚቀንስ በሂደት የአርሶ አደሩን ምርት እና ምርታማነት ሊቀንስ ይችላል፡፡ በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ላይ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶች በብዛት የስፐርንክለር (Sprinkler) እና ዲሪፕ (Drip) የመስኖ ውሃ ቴክኖሎጂ ይጠቀማሉ፡፡ ይህ ቴክኖሎጂ ዉሃን በአግባቡ ለመጠቀም ከማስቻሉም አልፎ እጽዋቶቹ ውሃን በሚፈልጉ መጠን እንዲያገኙ ስለሚያደርግ ምርታማነትንና የምርት ጥራትን ይጨምራል፡፡ ይሁን እንጂ ለዚህ ቴክኖሎጂ ግብአት የሚሆኑ መሣሪያዎች በሙሉ ከውጭ ሀገር ስለሚገቡ ከፍተኛ ወጪ ይጠይቃሉ፡፡ ይሁን እንጂ ባሁኒ ግዜ የስፐሪንክለር መስኖ መሣሪያዎች በብረታ ብረትና

ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን (METEC) መመረት መጀመሩ መልካም አጋጣሚ ነዉ፡፡ በተጨማሪም ቴክኖሎጂውን በአግባቡ ለመጠቀም በሙያው በቂ እውቀት እና ክህሎት ያለው ሰው ስለሚያስፈልግ እና በዚህ ዘርፍ በሀገራችን የሰልጠነ በቂ የሰው ኃይል በሚፈለገዉ መጠን ካለመገኘቱ ጋር ተያይዞ ቴክኖሎጂዉን በስፋት ከመጠቀም አንጻር ትልቅ ተግዳሮት ይታይበታል፡፡

በኢትዮጵያ ግሪን ሀውስ ቴክኖሎጂ በመጠቀም አትክልት እና ፍራፍሬን ማምረት በቅርብ ጊዜ የተጀመረ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እንደሚፈለገው የተስፋፋ አይደለም፡፡ ያለውም ቢሆን በአንጻራዊ መልኩ በዋናነት ለአበባ እና ለአትክልት ምርት እየዋል ያለ ሲሆን ለፍራፍሬ ምርት ግን ኢንጆሪን ለማምረት ከሚጠቀሙበት በስተቀር በብዛት ስራ ላይ አልዋለም፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ የተለመደው ጥብቅ እርሻ ዓይነት መቆሚያዎቹ ከብረት የተሰሩ ሆነው በፐላስቲክ ፊልም (Polythene) የተሸፈነ ስለሆነ የእርሻ ማሳውን ሙቀት እና እርጥበት በሚገባ መጠን ለመቆጣጠር የሚረዳ ዘመናዊ አሰራር ነው፡፡ በዚሁ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የውሃ መጠንን፣ የማዕድናት ይዘት፣ ካርቦዳይኦክሳይድ በተገጠመለት ኮምፒውተር በመታገዝ መቆጣጠር ይቻላል፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ አትክልት እና ፍራፍሬን ለማምረት እየተጠቀሙ ያሉት በዘርፉ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶች ሲሆኑ በዘርፉ የተሰማሩ ገበሬዎች ቴክኖሎጂውን አይጠቀሙትም፡፡ እነዚህ ገበሬዎች የማይጠቀሙበት ምክንያት ቴክኖሎጂውን ለመጠቀም ከፍተኛ እውቀት እና ክህሎት እንዲሁም ለመግዛት ከፍተኛ ወጪ ስለሚጠይቅ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ግሪን ሀውስ ለመገንባት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች በሙሉ ከውጭ የሚገቡ ሲሆኑ ግሪን ሀውሱንም ለመገንባት ያሉት በሀገር ዉስጥ ያሉት የፈረንሳይ፣ የህንድ እና የእስራኤል ድርጅቶች ናቸው፡፡ በአትክልትና ፍራፍሬ ወደፊት ሀገሪቷ እምርታዊ ለዉጥ እንድታመጣ ከተፈለገ ለግሪን ሀዉስ ግንባታ ግብአት የሚሆኑትን በሀገር ዉስጥ ማምረት መጀመር ያስፈልጋል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ ሊያገለግሉ የሚችሉ የቲሹ ካልቸር ተቋማት ከማደራጀት አኳያ በጅምር ደረጃ የሚገኝ ተሞክሮዎች ያሉ ሲሆን ይህን በማጠናከር ቴክኖሎጂዉ ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት እድገት የሚያበረክተዉ ድርሻ አሟጦ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ቲሹ ካልቸር የአትክልትና ፍራፍሬ አመራረት ሰርዓትን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገርና ከፍተኛ እሴት ያላቸውን የማብቀያ መሳሪያዎች (Planting Material) በመጠቀም በፍጥነትና በብዛት የማምረት (Micro propagation) ቴክኖሎጂን ለመጠቀምና የአምራቾች ምርታማነት በማሳደግ የዘርፉን ኤክስፖርት በረጅም ጊዜ አስተማማኝ ማድረግ ያስችላል፡፡

በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ሂደት ምርቱንና ተክሉን በተባይ እና በበሽታ እንዳይጎዳ መከላከል በጣም ወሳኝ ሥራ ነው፡፡ የጥበቃ ሥራዎቹም ቀድሞ ከመከላከል እስከ የተጎዳ እጽዋት ማከም ድረስ መሥራትን ይጠይቃል፡፡ በሽታን የመከላከል አቅማቸው ከፍ ያሉትን ዝርያ መጠቀም፣ የአካባቢ ንጽሕና መጠበቅ እና የአፈርን ጤናማነት መጠበቅ ዋነኞቹ ሲሆኑ የተጎዱ እጽዋትን ደግሞ ለማዳን ኬሚካል መርጨት፣ የተጎዱትን ለይቶ ማስወገድ እና በሽታ አምጪዎችን ለይተው መመገብ የሚችሉ ነብሳትን (Biological Control) መጠቀም ያጠቃልላል፡፡ አንዳንድ ማዳን የማይቻሉ በሽታዎች (ለምሳሌ Agrobacterium) ጭምር ስላሉ ሁል ጊዜ ቀድሞ የመከላከል ሥራው አጠናክሮ መሥራት ተገቢ እንደሆነ በዘርፉ ተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ የተቀናጀ የተባይ መቆጣጠሪያ ዘዴ (Integrated Pest Management) እየተተገበረ ያለ ሲሆን ይህ ዘዴ የእጽዋትን ጤንነት ለመጠበቅ የሚያስችል ከመሆኑም ባሻገር ባህላዊና ባዮሎጂካል መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን በግምባር ቀደምትነት በመተግበር፤ኬሚካል የመጠቀም አካሄድን በመቀነስ፤ ተባይን በመቆጣጠር በሰውና በአካባቢ ላይ ኬሚካሎች ሊያደርሱ የሚችሉትን ተጽእኖ ይቀንሳል፡፡ የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር አምራች ላኪዎች ማህበር በአሰራር ስነምግባሩ (Code of practice) ውስጥ ይህንኑ ዘዴ በዋነኛነት እርሻዎቹ እንዲገለገሉበት እየሰራ ያለ ሲሆን ሁሉም ኮሜርሻል በተቻለ መጠን እየተገበሩበትና የተመረጡ ኬሚካሎችን ብቻ በመጠቀም ላይ እያተኮሩ ይገኛሉ፡፡

የአትክልት ምርቶች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት በማዘጋጃ ክፍል (Pack house) ውስጥ በማቆየት ለገበያ እንዲመች አድርጎ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በማዘጋጃ ክፍል ውስጥ በዋናነት የሚሰሩ ሥራዎች አላስፈላጊ የሆኑ ቅጠሎችን ማስወገድ (Defoliation)፣ ጥራት ያለውን ምርት በደረጃ መለየት (grading) እና የማሸግ ሥራዎች ናቸው፡፡ በማዘጋጃ ክፍል እና በማጓጓዣ ወቅት፣ የምርቱን የቅዝቃዜ ሰንሰለት ጠብቆ መሥራት ስለሚያስፈልግ ለዚህ የሚረዱ ቴክኖሎጂዎችንም በስፋት መጠቀሙ ግድ ይላል፡፡

እነዚህ ቴክኖሎጂዎች በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል እና ካፒታል የሚፈልጉ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ የአትክልት ምርት በብዛት ሥራ ላይ ውለው አይታዩም፡፡ በዘርፉ የተሰማሩት ባለሀብቶች ግን ቴክኖሎጂውን ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት እና መጠቀም የተሻለ ተሞክሮ ያላቸዉ ሲሆን ከኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ ምክንያት ግን ቴክኖሎጂዉን በሚፈለገዉ መጠን ከመጠቀም አኳያ ግን ችግር እንደፈጠረባቸዉ ይታያል፡፡

### 2.1.3. የመሠረተ ልማት አቅርቦት

ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት የሚያስፈልጉ ወሳኝ ከሆኑ መሠረተ ልማቶች የመስኖ፣ የግሪን ሀወስ፣ የማዘጋጃ ክፍል (pack house)፣ የመንገድ፣ የሀይል፣ የመስኖ፣ የገበያ እና የመገናኛ ዘዴወች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸዉ፡፡ እነዚህ ወሳኝ መሰረተ ልማቶች ባልተሟሉበት የዘርፉን ልማት ትራንስፎርም በማድረግ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለመሆን ከባድ ይሆናል፡፡ በተለይ የመንገድ መሠረተ ልማት እንደሚፈለገዉ አለመኖር የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርቶች ዋጋ እንዲንር ከማድረጉም በተጨማሪ ለዓለም አቀፍ ገበያ ጥራት ያለው ምርት ሀገራት እንዳያቀርቡ ያደርጋል፡፡

የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በባህሪው ቶሎ የሚበላሽ (perishable) ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ቶሎ ወደ ገበያ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ለዚህ ደግሞ የመንገድ መሠረተ ልማት መኖር እና አለመኖር ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ በኢትዮጵያ 90% የሚሆነው የኢምፖርት እና ኤክስፖርት እንዲሁም 95% የህዝብ መጓጓዣ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚከናወነዉ በመኪና መንገድ መሠረተ ልማት በኩል ሲሆን በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ዋና ዋና ከተሞች ደረጃውን በጠበቀ አስፋልት መንገድ በመገናኘታቸው እና የገጠር ወረዳዎች እና ቀበሌዎችም ጭምር በመንገድ መረብ የተያያዙ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በቀላሉ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ወደ ገበያ ለማውጣት የጎላ እጥረት አይታይበትም (Temesgen, 2006)፡፡

የሃይል መሰረተ ልማት የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ለማሳደግ እና ጥራቱን ጠብቆ ለገበያ እንዲቀርብ ትልቅ ድርሻ ይጫወታል፡፡ በገጠር የሀገራችን ክፍሎች ያለው የኤሌክትሪክ መሰረተ ልማት ካለመዳረሱ ጋር ተያይዞ በነዚህ ቦታዎች የሚመረቱ የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርቶች በይዘታቸዉ ጥቂት ቢሆኑም የምርቶቹን ጥራት ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ በኤሌክቲሪክ ሃይል የሚሰሩ መሰረተ ልማቶችን ለማቅረብ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ በግል ባለሀብቶች የሚከናወነው የአትክልትና ፍራፍሬ ኮመርሻል እርሻዎች በከተማ አቅራቢያ ከመገኘታቸው ጋር ተያይዞ የኤሌክትሪክ መሰረተ ልማት ችግር የለባቸውም፡፡ ይሁንና በተደጋጋሚ የሀይል መቆራረጥ ስለሚያጋጥማቸው ለከፍተኛ ወጪ እንደሚዳርጋቸው በተደጋጋሚ የሚያነሱት ጉዳይ ነዉ፡፡

የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርት ለማከማቸት እና የቅዝቃዜ መጠኑን ጠብቆ ለማቆየት የቀዝቃዛ መጋዘን መሰረተ ልማት መኖር ለዘርፉ እድገት ወሳኝ ነው፡፡ በሀገራችን አንዳንድ አትክልት

ማምረት የቻሉ አከባቢዎችን ሲናይ ይህ የቀዝቃዛ መጋዘን መሰረተ ልማት ካለመስፋፋቱ ጋር ተያይዞ በአጠቃላይ የተገኘዉ ጥቂት ምርትም እንኳ ብትሆንም በቀላሉ ለብልሽት ስትዳረግ ደግሞ በስፋት ይታያል፡፡ የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርቶችን በማምረት የሚታወቁ የተወሰኑ የሀገራችን ክፍሎች ለምሳሌ በምሥራቅ ሀረርጌ፣ በምስራቅ ሸዋ፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ እና በአንዳንድ የደቡብ አከባቢዎች እንኳ የሚሰበሰቡ ምርቶች አስፈላጊውን የጥራት ደረጃ ስለማያሟሉ እና ለገበያ ታስበዉ (Commercial) ስለማይመረቱ በሀገር ውስጥም ይሁን በኤክስፖርት ገበያ ዋጋቸው ዝቅተኛ ነዉ፡፡ ይህን ችግር ለመፍታት በአንዳንድ አካባቢዎች (ለምሳሌ በአዳሚ ቱሉ ዩኒዮን) አምራች ገበሬዎች በማህበራት በመደራጀት የጋራ የማከማቻ መጋዘኖችን የመገንባት እና የመጠቀም ጅማሮዎች የሚታዩ ሲሆን ይህን ልምድ ለሌሎችም በማካፈል እና በማስፋፋት ችግሩን መፍታት ይቻላል፡፡ የግል ባለሀብቶች የየራሳቸው ቀዝቃዛ መጋዘኖች ስለሚገነቡ ለገበያ ለሚያቀርቡት የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ጥራት የበኩሉን ድርሻ አበርክቶላቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በዓመት የ5.3% ካርጎ አገልግሎት እድገት በማሳየት በዘርፉ እምርታ እያስመዘገበ ያለ ድርጅት ነዉ፡፡ ለዚህ እድገት በዘርፉ የሚያስፈልጉትን መሠረተ ልማቶች ለማሟላት የተደረገዉ ጥረት ትልቅ ሲሆን ሀገሪቷ አሁንም የዘርፉን መሠረተ ልማት እያስፋፋች ትገኛለች፡፡ በቦሌ አለም አቀፍ አየር ማረፊያ፣ በግንቦት 20 አለም አቀፍ አየር ማረፍያ እና በአሉላ አባነጋ አለም አቀፍ አየር ማረፊያዎች የዘመናዊ የዕቃ መጫኛ፣ የማቀዝቀዣ፣ እና የማቆያ መሠረተ ልማቶች ተሟልተውላቸዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የካርጎ አገልግሎቱን በማስፋት በዓለም ከ40 በላይ መዳረሻዎችን በአፍሪካ፣ በአውሮፖ፣ በመካከለኛው ምሥራቅ እና በኤሺያ በመፍጠር የሀገሪቱን የአትክልት፣ የፍራፍሬ፣ የሥጋ እና የአበባ ምርቶችን በማጓጓዝ በ2012 እና በ2013 እኤአ. ከ6 ቢልዩን ብር በላይ ገቢ የተገኘ ሲሆን ለዚህም ውጤት በዘርፉ መሠረተ ልማትን ለማሟላት የተሰራው ሥራ ትልቅ ድርሻ አበርክቷል፡፡

በአሁኑ ግዜ የኢትዮጵያ መንግስት የተለያዩ የሀገሪቷን ከተሞች ከወደብ ጋር በባቡር መሠረተ ልማት ለማገናኘት እና የመርከብ ትራንስፖርት ለማሳደግ እየሰራ ያለው ሥራ የሀገሪቷን የአትክልት ምርቶች በተለይም የድንችና የሽንኩርት ምርቶችን እንዲሁም ከፍራፍሬ የሙዝ ምርትን ለመካከለኛ ምሥራቅ ሀገራት ለማቅረብ ተጨማሪ አቅም ይፈጥርላታል፡፡

### 2.1.4. የሎጀስቲክስ እና የገበያ ልማት

በኢትዮጵያ የአትክልት ምርት ተመርቶ እስከ ተጠቃሚዎች ድረስ ባለው ሁኔታ እስከ 35% ብክነት ያጋጥማል(Joosten, 2011)፡፡ ይህ ብክነት ከፍ ያለበት ምክንያትም ምርቱ ከተመረተ በኋላ የማሸግ እና የማከማቸት ሥሪዎች በአግባቡ ስለማይሰሩ እና በሚፈለገው ጊዜ ተጓጉዞ ተጠቃሚዎች ጋር ስለማይደርስ ነው፡፡ አምራቾች በተለይም ገበሬዎች የራሳቸው የሆነ የተጠናከረ የማከማቻ ዘዴ ስለሌላቸው ገበያው እስኪረከባቸው ድረስ በዝናብ እና በፀሐይ ምርታቸው የሚጎዳበት ሁኔታ በሰፊው ይታያል፡፡ ከዚህም የተነሳ ምርታቸው የተሻለ ዋጋ ባያወጣላቸውም እንኳ እንዳይበላሽባቸው ሲባል ብቻ ባለው የገበያ ዋጋ እንዲሸጡ ይገደዳሉ፡፡

ከትራንስፖርት አኳያም ሲታይ በኢትዮጵያ የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርቶችን ወደ ገበያ ለማጓጓዝ ከፍተኛ የሆነ የዘመናዊ የትራንስፖርት እጥረት አለ፡፡ ለዚሁም ሲባል በገበሬዎች እና በባለሀብቶች ተመርተው ለገበያ የማይቀርቡ በተለይም የአትክልት ምርቶች በብዛት በትላልቅ የሀገራችን ከተሞች ዙሪያ የተወሰኑ ናቸው፡፡ ወደ ጎረቤት ሀገሮች እየተላኩ ያሉትም የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ያሉ ቢሆንም እንኳ በቂ የማጓጓዣ መኪና እና ቀዝቃዛ ኮንተይነር እጥረት በሰፊዉ ስለሚታይ ጥራቱን እና መጠኑን ጠብቆ ወደሚፈለግበት ቦታ አይደርስም፤ ቢደርስም ለማጓጓዝ የሚያስከፍለዉ ገንዘብ በጣም ከፍተኛ ስለሚሆን በዋጋዉ ጭምሪ ምርቶቹ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ስለዚህ አትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በባሕሪያቸው ቶሎ ስለሚበላሹ ይህን ለመከላከል ምቹ የሆነ የማከማቻ ቦታዎችን መምረጥ፣ ተገቢውን የማሸግ ሥራ መስራት፣ የቅዝቃዜ ሰንሰለቱን መጠበቅ እና በቂ የማከማቻ መጋዘኖችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የካርጎ አገልግሎት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከ40 በላይ መዳረሻዎች ያሉት እና አገልግሎቱንም ከግዜ ወደግዜ እያሳደገ የመጣ ቢሆንም የአገልግሎቱ ፈላጊዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ መጠን እያደገ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ፤ ያለው ፍላጎት እና አገልግሎት አይጣጣምም፡፡ በተለይ የአበባ፣ የአትክልት፣ የፍራፍሬ እና የሥጋ ኤክስፖርት ላይ የተሳተፉ ባለሀብቶች ቁጥር እያደገ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የአገልግሎቱ ፋላጊዎች በከፍተኛ መጠን በመጨመሩ በአየር መንገድ ያለው የሎጅስቲክስ አቅርቦት በጣም አናሳ እና ወደፊት መሻሻል ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ባለፉት 5 ዓመታት 817.8 ቶን የፍራፍሬ ምርቶች እና 1184.8 ቶን የአትክልት ምርቶች ከደቡብ አፍሪካ፣ ከግብጽ፣ ከታንዛኒያ፣ ኬኒያ እና ሱዳን ወደ ሀገር ዉስጥ አስገብታለች (Joosten, 2011)፡፡ እነዚህ ወደ ሀገር ዉስጥ የገቡ ምርቶች በከፊል ወይም በሙሉ በኢንዱስትሪ የተቀነባበሩ

ምርቶች ሲሆኑ በሁሉም በሀገሪቷ ከተሞች በሚገኙ የሸቀጣሸቀጥ ሱቆች እና በሱፐር ማርኬቶች በስፋት ይሸጣሉ፡፡ በኢትዮጵያ የሚመረቱ የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርቶች በብዛትም ሆነ በጥራት በኢንዱስትሪ ተቀነባብረዉ ለሀገሪቱ ገበያ ያልቀረቡ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ኢምፖርት የተደረጉ የዘርፉ ምርቶች የሀገር ዉስጥን ገበያ ተቆጣጥረዉ ይገኛሉ፡፡

ኢትዮጲያ በኢንዱስትሪ ያልተቀነባበሩ የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርቶችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኤክስፖርት ማድረግ የጀመረች ሲሆን ዋና ዋና መዳረሻዎችም የአዉሮፓ ሀገራት፣ የመካከለኛ ምሥራቅ ሀገራት እና የአፍሪካ ሀገራት ገበያዎች ናቸዉ፡፡ ሀገሪቷ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶቿን ከ 100 በላይ ለሆኑ የዓለም ሀገራት የምትልክ ሲሆን አብላጫዉን ግን በአፍሪካ ላሉ ጎረቤት ሀገሮች፣ ለመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት እና ለአውሮፓ ሀገራት በመላክ ትታወቃለች (ሠንጠረዥ 3) ፡፡ ኤክስፖርት ከሚደረጉ ምርቶች በአትክልት ዘርፍ በዋናነነት ሽንኩርት፣ ቲማቲም፣ ጎመን እና ድንች በአትክልቱ ዘርፍ ሲሆን ከፍራፍሬ ምርት ደግሞ ሙዝ፣ ብርቱካን፣ አቮካዶ ምርቶች ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 3: አሥር ቀዳሚ የኢትዮጵያ አትክልትና ፍራፍሬ ኤክስፖርት ገበያ መዳረሻዎች

| ተ.ቁ | የገበያ መዳረሻ<br>(Market Destination) | የብዛት ድርሻ ከመቶ<br>(% share in Quantity) | የዋጋ ድርሻ ከመቶ<br>(% share in value) |
|---|---|---|---|
| 1. | ሶማሊያ | 46.3 | 37.2 |
| 2. | ጂቡቲ | 44.0 | 26.4 |
| 3. | ኔዘርላንድ | 3.0 | 17.1 |
| 4. | የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ | 3.3 | 9.3 |
| 5. | ሱዳን | 1.8 | 1.8 |
| 6. | ኢንግሊዝ | 0.2 | 1.8 |
| 7. | ቤልጂየም | 0.4 | 1.8 |
| 8. | የመን | 0.3 | 1.0 |
| 9. | ሳዉዲ አረቢያ | 0.4 | 0.8 |
| 10. | ሩሲያ | 0.1 | 0.1 |

ምንጭ: EHDA, 2012

ከኢትዮጲያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ዓመታዊ ሪፖርቶች የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተዉ ከሆነ ሀገሪቷ ከ2004 እስከ 2006 ዓ.ም. 360 ሺ ቶን አትክልት እና 45.65 ሺ ቶን ፍራፍሬ ወደ ተለያዩ ሀገራት ኤክስፖርት በማድረግ በተመሳሳይ ጊዜ 151.1 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የዉጭ ምንዛሪ አግኝታለች (በሠንጠረዥ 4) ፡፡

ሠንጠረዥ 4፡ የኢትዮጵያ አትክልትና ፍራፍሬ ኤክስፖርት (2004 – 2006)

| የምርት ዓይነት | 2004 | | 2005 | | 2006 | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መጠን* | ገቢ** | መጠን* | ገቢ** | መጠን* | ገቢ** | መጠን* | ገቢ** |
| አትክልት | 110.67 | 48.66 | 123.57 | 48.6 | 126.46 | 39.78 | 360.7 | 137.04 |
| ፍራፍሬ | 12.93 | 4.49 | 14.09 | 4.03 | 18.65 | 5.94 | 45.67 | 14.46 |
| **ድምር** | **123.6** | **53.15** | **137.66** | **52.63** | **145.11** | **45.72** | **406.37** | **151.1** |

*መጠን በሺህ ቶን ** ገቢ በሚK=ዮን ዶላር

ምንጭ፡ ከEHDA ዓመታዊ ሪፖረቶች ላይ የተቀናበረ

የአውሮፓ ህብረት ሀገራት የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶ ገበያን ስናይ ሀገራቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን በሀገራቸዉ አምርተዉ ለሀገር ዉስጥ ገበያ ከሚያቀርቡት በተጨማሪ ከሌሎች ሀገሮች በመግዛትም ይታወቃሉ፡፡ የምሥራቅ አውሮፓ ሀገራት የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርት ገበያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ያለ ሲሆን የምዕራብ አዉሮፓ ሀገራት ገበያ ግን በመጠኑ ግዙፍ ቢሆንም ከአመት አመት የሚያሳየዉ የእድገት ፍጥነት ግን በጣም አነሳ ነው፡፡ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ወደዚህ ገበያ በብዛት የሚላከው ከላቲን አሜሪካ፣ ከሜዲትራንያን አካባቢዎች እና ከአፍሪካ ሀገራት ነው፡፡ ገበያው ከዚህ በፊት ንግዱ ውስጥ ላሉ እና አስቀድመው ግንኙነት ያላቸውን የማስቀጠል ሁኔታ የሚታይበት ሲሆን አዲስ ወደ ገበያው መቀላቀል ለሚፈልጉት ግን በቀላሉ የሚቀመስ ካለመሆኑም በተጨማሪ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ምርቶች ይዞ ማቅረብንና እና የምግብ ደኅንነት ሰርተፍኬቶች ማሟላትን ይጠይቃል፡፡ በዘርፉ ያለዉ የአዉሮፓ ገበያ የሚወሰነው በአህጉሩ በሚገኙ ትላልቅ የገበያ ማዕከላት እና ጅምላ አከፋፋዮች ሲሆን አቅራቢዎች ግን ዋጋን የመወሰን እና የመደራደር አቅም የተወሰነ ነዉ፡፡ የአውሮፖ ፍራፍሬ እና አትክልት ገበያ የአማራጭ ገበያ (a substitution market) ሲሆን አብዛኛው ግብይት የሚካሄደው ቀደም ብለው ኮንትራት ካላቸው አቅራቢዎች እና ትላልቅ አከፋፋዮች (ለምሳሌ Greenery in Holland እና ትላልቅ ሱፐር ማርኬቶች (ለምሳሌ Tesco in UK, Aldi in Germany) ጋር ብቻ ነዉ፡፡ በ2014 (ኢ.አ) 33 ቢልየን ዩሮ የሚያወጣ የፍራፍሬ ምርቶች ወደ አውሮፓ ገበያ የገቡ ሲሆን ከምርቶቹ ዉስጥም ሙዝ፣ ወይን፣ አፕል እና ሲቲረስ ፍራፍሬዎች ትልቁን ድርሻ ይይዛሉ፡፡ ከአውሮፓ ገበያ ኒዘርላንድ፣ ቤልጅየም፣ ዩናይትድ ኪንግደም እና ጀርመን እነዚህን ምርቶች ወደ ሀገራቸው

በማስገባት ትልቁን ድርሻ ሲይዙ ወደ አውሮፓ የፍራፍሬ ምርትን በመላክ የሚታወቁት ሀገራት ግን አሜሪካ፣ ቱርክ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ናሚቢያ፣ ቺሊ፣ ኮስታሪካ፣ ኮሎምቢያ፣ ኢኳዶር፣ አርጀንቲና ብራዚል እና ሞሮኮ ናቸው፡፡ በተመሳሳይ ዓመት ወደ አውሮፓ ገበያ የገባው የአትክልት ምርት 19.3 ቢሊየን ዩሮ የሚገመት ሲሆን ምርቶቹ የተላኩባቸው ሀገራትም ሞሮኮ፣ ቻይና ቱርክ፣ እስራኤል፣ ግብጽ፣ ካናዳ፣ ኬንያ፣ አሜሪካ እና አርጀንቲና ናቸው፡፡

የአውሮፓ ገበያ ለኢትዮጵያ የአትክልት ምርት ከጎረቤት የአፍሪከ ሀገራት እና የመካከለኛው ምስራቅ ቀጥሎ በሦስተኛ ደረጃ የሚመደብ ገበያ ነው፡፡ ከኢትዮጵያ ወደዚህ ገበያ ኤክስፖርት የምታደረገዉ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሲሆን በ2006 ዓ.ም. ብቻ 167,422.50 ኪ.ግ የፍራፍሬ ምርት ተልኮ 201,083.44 የአሜሪካን ዶላር ገቢ አግኝታለች (ሠንጠረዥ 5)፡፡ በዋናነት ኢትዮጵያ ምርቷን የላከችባቸዉ ሀገሮች ኔዘርላነድ፣ጀርመን፣ኢንግሊዝ እና ቤልጂየም ናቸዉ፡፡ የኢትዮጵያ አምራቾች እና ላኪዎች ወደ አውሮፓ ገበያ ለመግባት የነበራቸውን ስትራቴጂክ ግንኙነት ወይም አምራቾቹ ራሳቸዉ ቀድሞ በነበራቸዉ የመሸጫ ቦታዎችን በመጠቀም በገበያዉ መሳተፍ ችለዋል፡፡

የአዉሮፓ ህብረት ሀገራት የአትክልት እና የፍራፍሬ ገበያ ከፍተኛ የጥራት እና ደረጃ መስፈርት ማሟላትን ግድ ከማለቱም ባሻገር ምርቶችን ቀጣይነት ባለዉ መልኩ (consistent) ማቅረብን ይጠይቃል፡፡ የኢትዮጲያ የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርቶች በአብዛኛዉ የአዉሮፓን የአትክልት እና የፍራፍሬ ገበያ የጥራት እና ደረጃ መስፈርት ለማሟላት ገና ብዙ መስራትን የሚጠይቅ ከመሆኑም በተጨማሪም አመቱን ሙሉ አስተማማኝ ምርቶችም የማይቀርቡ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሀገሪቷ ከዚህ ገበያ መጠቀም ያለባትን ያህል እስካሁን አልተጠቀመችበትም፡፡

ሠንጠረዥ 5: ከኢትዮጵያ ወደ አዉሮፓ ገበያ ኤክስፖርት የተደረገ የፍራፍሬ ምርቶች (2004 - 2006)

| ተ.ቁ | መዳረሻ | 2004 | | 2005 | | 2006 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክብደት (ኪ.ግ) | ዋጋ (USD) | ክብደት (ኪ.ግ) | ዋጋ (USD) | ክብደት (ኪ.ግ) | ዋጋ (USD) |
| 1. | ቤልጂየም | 82.00 | 29.02 | 2,618.00 | 2,131.97 | 21,370.00 | 23,315.00 |
| 2. | ፈረንሳይ | | | 780.00 | 265.20 | | |
| 3. | ጀርመን | 250.00 | 375.00 | 3,643.00 | 1,031.47 | 38,000.00 | 27,930.00 |
| 4. | ኢጣሊያ | 52.00 | 1,930.69 | 2,151.00 | 648.06 | | |
| 5. | ሊቱኒያ | | | 240.00 | 33.60 | | |
| 6. | ኔዘርላነድ | 41,633.00 | 108,606.66 | 38,299.00 | 41,542.51 | 80,315.00 | 109,648.87 |
| 7. | ፖርቹጋል | | | | | 18,500.00 | 13,135.00 |
| 8. | ቱርክ | | | 40.00 | 6.40 | | |
| 9. | ኢንግሊዝ | 16,175.58 | 57,723.73 | 10,239.00 | 4,252.05 | 9,237.50 | 27,054.57 |
| | አጠቃላይ | 58192.58 | 168665.1 | 58,010.00 | 49,911.26 | 167,422.50 | 201,083.44 |


ምንጭ፡ ከEHDA ዓመታዊ ሪፖርቶች የተቀነባበረ

የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት የፍራፍሬ ምርት ገበያ ከጊዜ ወደ ጊዜ በፍጥነት እያደገ ያለ ሲሆን እድገቱ በዓመት 3% አከባቢ ይሆናል፡፡ በአትክልት ገበያ ዘርፍም ተመሳሳይ የገበያ እድገት እንዳለ ጥናቶች ያሳያሉ (ስዕል 1)፡፡ በ2013 በመካከለኛ ምሥራቅ ሀገራት የ2.5 ቢሊየን የአሜሪካ ዶላር የሚገመት የፍራፍሬ ምርቶችን ወደ ሀገራቸው አስገብተዋል፡፡ ከነዚህ ምርቶች መሀከልም ዋናዎቹ አፕል፣ ብርቱካን፣ ሙዝ ፣ ወይን እና ማንጎ ናቸው፡፡ ከስዕል 1 ለማየት እንደሚቻለዉ ወደ መካከለኛዉ ምስራቅ የሚገባዉ የፍራፍሬ ምርት መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄዱን ነዉ.፡፡ የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት የፍራፍሬ ገበያ ከአውሮፓ ገበያ አንፃር ሲወዳደር በጣም ተለዋዋጭ (fragile) እና ለማክሮ ኢኮኖሚ መዋዠቅ በቀላሉ ተጽእኖ የሚታይበት ከመሆኑ በተጨማሪ የዋጋ እና የገቢ መለዋወጥም ቀጥተኛ ምላሽ የሚሰጥ ነው፡፡

የኢትዮጵያ አጎራባች የሆኑ የአፍሪካ ሀገራትን ገበያ ማለትም የሱዳን፣ የደቡብ ሱዳን፣ የኬንያ፣ የሱማሊያ፣ የሪፐብሊክ ኮንጐ፣ ጋቦን እና የጅቡቲ የአትክልትና ፍራፍሬ ገበያን መጠቀም የጀመረች ሲሆን በየዓመቱ 3 ከመቶ ጭማሪ እያሳየ በመሄድ ያለ ነው፡፡ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት በኢኮኖሚያቸው ከሰሀራ በስተደቡብ ካሉት ሀገራት የተሻለ እድገት እያስመዘገቡ ከመሆናቸው አንፃር ወደፊትም ኢትዮጵያ ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርቷ የተሻለ ገበያ ልታገኝ ትችላለች፡፡ እነዚህ ሀገራት በቅርበት ከመገኘታቸው በተጨማሪም የጠበቀ የምግብ ደህንነት ቁጥጥር የማይደረግባቸው

ከመሆናቸው ጋር ተያይዘዉ ኢትዮጵያ በዘርፉ አሁን ባለው ምርት እና የማምረት ብቃት በአካባቢው ምርቷን ለጊዜዉ መሸጥ ትችላለች፡፡ ይሁን እንጂ የዚህ ዓይነቱ የጥራት ደረጃዉ ዝቅ ያለ የምርት ገበያ ሁኔታ ዘላቂ ሊሆን ስለማይችል ወደፊት በአዉሮፓ የጥራት ደረጃ በማምረት አስተማማኝ የሆነ ገበያ በሀገራቶቹ መያዝ እና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡ በስዕል 1 እንደተመለከተው ኢትዮጵያ በ2005 (እኤ) 25,335.10 ቶን እና በ2010 (እኤ) 25,335.1 ቶን የአትክልት ምርት ወደ አፍሪካ ሀገራት የላከች ሲሆን የኤክስፖርት መጠኑም በተጠቀሱት ዓመታት እያደገ መሄዱን ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ መልኩም በፍራፍሬ ዘርፉ ለነዚሁ ሀገራት 7,323.3 ቶን በ2005 ኤ.አ እና 7,567 ቶን ኤክስፖርት የተደረገ ሲሆን በነዚህ ዓመታት ልዩነት የኤክስፖርት እድገቱ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም ፡፡

ስዕል 1፡ለአፍሪካ አጎራበች ሀገሮች የኢትዮጵያ የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርቶች ኤክስፖርት





ምንጭ፡ (ፀጋዬ 2010)

ኢትዮጵያ ለሀገር ዉስጥ እና ለኤክስፖርት ገበያ የምታቀርበዉ የአትክልት እና ፍራፍሬ ምርት የገበያ ሰንሰለት በጣም ረጅም ከመሆኑም በተጨማሪ ብዙ ተሳታፊዎች የሚሳተፉበት እና ግልጽነት የጎደለዉ ነዉ፡፡በዚህ ረገድ የሚጠቀሱት ተዋንያኖችም ግብይት፣አምራቾች፣ደላሎች፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች፣ጅምላ ነጋዴዎች፣ቸርቻሪዎች እና ተጠቃሚዎች ናቸዉ (ስዕል 2)፡፡ በአትክልትና ፍራፍሬ አቅርቦት ሰንሰለት ላይ አምራቾች ወሳኙን ድርሻ ቢይዙም የራሳቸው የሆነ የግብይት እስትራቴጂ ስለሌላቸው ነጋዴዎች መጥተው ከማሳ እስኪገዙ ድረስ የሚጠብቁበት ሁኔታ በብዛት ይታያል፡፡ በዚህ ሁኔታ አምራቾች ብዙን ጊዜ የዋጋ ተቀባዮች እንጂ በምርታቸው ላይ ዋጋን የሚወስኑ አይደሉም፡፡ ደላሎች አምራች እና ገዢን ማገናኘት፣ ትራንስፖርት

በማመቻቸት እና የምርቱን ስርጭት በመወሰን በገበያው ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ከተመረተበት አካባቢ ለፍጆታ ወደሚውሉበት አካባቢ በማጓጓዝ በግብይት ሰንሰለቱ የጎላ ድርሻ አላቸዉ፡፡ የጅምላ ነጋዴዎች ምርቱን በብዛት ከአቅራቢያቸው ወይም ከአምራቾች ተቀብለው በችርቻሮ ለሚሸጡ ነጋዴዎች በጅምላ ያስረክባሉ፡፡ በሀገር ውስጥ ያሉ እና በጎረቤት ሀገራት ያሉ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ገዥዎች በስዕል 2 ከተቀመጡት የግብይት መተላለፍያዎች መስመሮች (market channel) በአንዱ የሚፈልጉትን ምርት የሚያገኙ ሲሆን በሀገር ዉስጥ ያለዉ ግብይት ግን ረጅም የሆነዉን መስመር (መስመር 1) አዘወትረዉ ይጠቀሙበታል፡፡

ሥዕል 2: የአትክልትና ፍራፍሬ ግብይት መተላለፍያዎች (Marketing Channel)




### *2.1.5. የግል ባለሀብቶች ተሳትፎ*

የኢትዮጵያ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ስናይ በአብዛኛው[1] አርሶ አደሮች የአገሪቱ ቁልፍ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ተዋናዮች ሁነዉ እናገኛቸዋለን፡፡ ከኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ (CSA, 2014) የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በ2005 የሰብል ዘመን 14.72 ሚሊዮን አርሶ አደሮች የተሳታፉ ሲሆን 61,972.6 ሄ/ር መሬት በፍራፍሬ፣ 396,513.54 ሄ/ር መሬት በአትክልትና ስራስር ሰብሎች ተሸፍኖ ነበር፡፡ በምርት ዘመኑ ከምርት አኳያም ከ479,336.06 ቶን በላይ በፍራፍሬ እና 4,482,169.94 ቶን ከአትክልትና ስራስር የተገኘ

1 በኢትዮጵያ አርሶ አደሮች 90 ከመቶ የሚሆነውን የግብርና ምርት የሚያመርቱ ሲሆኑ፣ 96 ከመቶ በግብርና ልማት የተሸፈነውን የመሬት መጠን ይወክላሉ (CSA, 2014)፡፡

መሆኑን ያመለክታል፡፡ በአጠቃላይ የተሳታፊውም ሆነ  የምርት መጠኑ ላለፉት 10 አመታት እየጨመረ የሄደ መሆኑን ያሳያል፡፡ እነዚህ አርሶ አደሮች የሚያመርቱት በአብዛኛው በዝናብ ቢሆንም፣ በብዙ አካባቢዎች በአነስተኛ መስኖ የሚደገፍ  ከመሆኑ አንፃር የምርት መጠኑና የአቅርቦት ጊዜው በጣም ተለዋዋጭ ነው፡፡ ከሰኔ እስከ መስከረም የምርት አቅርቦቱ በጣም የሚያንስበት እና ለምርቶቹ ከፍተኛ ዋጋ የሚኖርበት ጊዜ ሲሆን ከጥቅምት እስከ ጥር ባሉት ወራቶች ደግሞ መካከለኛ እና እየጨመረ የሚሄድ የምርት አቅርቦት ያለበት ወራቶች ሲሆን ከየካቲት እስከ ግንቦት ግን ከፍተኛ ምርት የሚገኝበት ሆኖ ገበያው ግን እየቀዘቀዘ የሚሄድበት ወቅት ነው፡፡

የባለሀብቶችን ተሳትፎ በማበረታታት የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች  ለሀገር ውስጥና እና ለኤክስፖርት ገበያ ምርት ለማቅረብ ሲባል በባለሀብቶች የሚከናወኑ (Commercial Farms) እርሻዎች በኢትዮጵያ መልካም ሊባል የሚችል ጅማሮዎች አሉ፡፡ በ1990ዎቹ አጋማሽ የኢትዮጵያ መንግስት  ባወጣው የግል ድርጅቶች ፖሊሲና የግል ኮሜርሽያል ኤክስፖርት ምርትን የማበረታታት ስራ በመሰራቱ በተወሰነ የግል ዘርፍ ኩባንያዎች በፍራፍሬ እና አትክልት ምርት በማምረት፣ በማቀነባበር እና ለውጭ በመላክ ረገድ ጥሩ የሚባል መነቃቃት ታይቷል (Joosten *et al.,* 2011)፡፡ ከኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጄንሲ (EHDA) የተገኘዉ መረጃ እንደሚያመለክተዉ ከሆነ በሰኔ 2005 ዓ.ም. 36 (ሰላሳ ስድስት) የግል ኮሜርሽያል እርሻዎች 11768.3 ሄክታር መሬት በማልማት የፍራፍሬና አትክልት ምርቶችን ለሀገር ዉስጥ እና ለዉጭ ሀገር ገበያ አቅርበዋል (የ2005 EHDA ዓመታዊ ሪፖርት)፡፡  በባለሀብቶችን ተሳትፎ የአርባ ምንጭ የሙዝ እርሻ  እና የላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ ኢንተርፕራይዝ  ዋነኛዎቹ የሀገሪቱ የፍራፍሬና የአትክልት ማምረቻ ቦታ ሲሆን ከነዚህ እርሻዎች የሚመረቱ ምርቶች በዋናነት ብርትኳን ፣ ማንጎ፣ ፓፓያ፣ ወይን፣ ቲማቲም፣ ቀይ ሽንኩርት ሲሆኑ በከፊል ተቀነባብረዉ እና ሳይቀነባበሩ ለሀገር ውስጥ እና ለዉጭ ገበያ ይዉላሉ፡፡ ለውጭ ገበያ (በተለይም ለጅቡቲ) የሚላኩ የቲማቲም ከችአፕ (tomato ketchup) ፣ ጁስ፣ የቲማቲም ድልህ እና የብርቱካን ማርማላድ ከዋነኞቹ ምርቶች መካከል የሚጠቀሱ ናቸዉ፡፡

## 2.1.6. የጥራት እና ደረጃ ሁኔታ

ጥራት የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ገበያ ላይ በገዢዎች ተቀባይነት እንዲኖረው እና የገበያ ዋጋንም ከሚወስኑት ጉዳዮች ዋነኛው ነው፡፡ የትኩስ ፍራፍሬ እና አትክልት ጥራት የሚገለጠው በገጽታ (appearance)፣ ሽታ (sensory)፣ ቀለም፣ ጣዕም (flavor) እና የምግብነት ይዘት ሲሆኑ ሸማቾች በነዚህ መስፈርቶች ከፍተኛ ነው ለሚሉት ከፍ ያለ ዋጋ ይከፍላሉ፡፡ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ጥራት የምርቱ ደህንነት ላይ የሚመሰረት ሲሆን ይህም ከማንኛውም አካላዊ እና ኬሚካል አደጋ ከሚያደርሱ እንዲሁም ምርቱን ከሚበክሉ ጥቃቅን ነፍሳት ነፃ መሆን ግድ ይላል (Rosa, 2011)፡፡

አትክልትና ፍራፍሬ ኤክስፖርት ለማድረግ እና በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ ለመሆን ጥራቱን የጠበቀ እና የተሻለ ደረጃ ያለው ምርት ይዞ መቅረብ አለበት፡፡ የጥራት መስፈርት ተብለው በአሁኑ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋሉ መመሪያዎች ያሉ ሲሆን እነሱም በዋናነት Global-GAP እና ISO ናቸው፡፡ እነዚህ የጥራት መስፈርቶች የሸማቹን ፍላጎት ያገናዘበ ምርት ማለትም ማሳ ላይ ከሚኖረው የምርት ሂደት ጀምሮ ሸማቹ ጋር እስኪደርስ ድረስ እንዲኖር ለማድረግ ነው፡፡ Global-GAP አትክልትና ፍራፍሬ በምርት ጊዜ አካባቢን የሚበክል የአሰራር ሁኔታ እንዳይኖር አነስተኛ የኬሚካል ማዳበሪያ ጥቅም ላይ እንዲውል እና የሰራተኞችን እና የሌሎች እንስሳትን የሚጎዳ ተግባራት እንዳይከናወኑ ይከላከላል፡፡

በኢትዮጵያ የሚመረቱ በተለይም ከአነስተኛ ማሳ የሚሰበሰቡ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች እነዚህ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቀመጡትን መስፈርቶች የማያሟሉ ሲሆኑ ኤክስፖርት ሊደረጉ የማይችሉ ናቸዉ፡፡ በመሆኑም አብዛኛው ምርት ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ይውላል፡፡ በዚህ ረገድ በሰፋፊ ኮሜርሻል የግል ባለሀብቶች እርሻ ላይ የሚመረቱት የ Global-GAP የጥራት መስፈርትን ስለሚያሟሉ ምርቶቻቸው ወደ አውሮፓ ገበያ እና ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ገበያ እየተላኩ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ አበባ አትክልትና ፍራፍሬ አምራች ላኪዎች ማኅበር የዘርፉን ዘላቂ አመራረት ለማሳደግ የአሰራር ኮድን በማስተዋወቅ ሀገሪቷ ጥራት ያለዉ ምርት ለአለም ገበያ በማቅረብ እና ብቁ ተወዳዳሪ በመሆን ከዘርፉ የተሻለ ጥቅም እንድታገኝ እየሰራ ነዉ፡፡ ይህ የአሰራር ኮድ አምራቾች የአትክልትና ፍራፍሬ አመራረትን ዘላቂ በሆነ ዘዴ እንዲያመርቱ በመመሪያነት የሚያግዝ ሲሆን አምራች ላኪዎች በአካባቢ ጥበቃ፣ በሰራተኛ አያያዝ ፣ምቹና ከስጋት ነፃ የሆነ

የስራ ቦታን ለመፍጠር እንዲሁም በማኅበረሰብ ልማት ስራዎች ላይ እንዲሳተፉ የሚያበረታታ ነው። የአሰራር ኮድ ኦዲት የሚደረገው መሰረቱን ኔዘርላንድ አገር ባደረገ ድርጅት ሲሆን በዚሁ መሰረት በ2005 ብቻ 55 እርሻዎች ለነሃስ፣ 12 እርሻዎች ለብር፣ 3 እርሻዎች ለወርቅ ደረጃዎች ብቁ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

| **የአሠራር ኮድ ደረጃዎች** | | |
|---|---|---|
| የነሀስ ደረጃ | የብር ደረጃ | የወርቅ ደረጃ |
| ➢መሠረታዊ የውስጥ ቁጥጥር መዘርጋት<br>➢የመዝገብ አያያዝና አካባቢ ጥበቃ<br>➢የቅጥር አሠራርና ሙያዊ ደህንነት | ➢ዘላቂ የግብርና አሠራር<br>➢የአካባቢ ጥበቃ<br>➢የሠራተኛ የሥራ ቦታ ደህንነት | ➢ የምረት ጥራት አስተዳደር<br>➢የማኅበራዊ ልማት ተሳትፎ መጐልበት<br>➢የሰው ኃይል አቅም ግንባታ<br>➢"Fair Trade Certification" ያሟላ |

## 2.2. የቤንች ማርክ ሀገር ሁኔታ

የዓለም የምግብ እና የእርሻ ድርጅት (FAO) መረጃ እንደሚያመለክተው በ2014 እ.ኤ.አ የዓለማችን የቆላ ፍራፍሬ (tropical fruit) ምርት 82 ሚሊዮን ቶን የደረሰ ሲሆን ከመነሻ ዓመት 2004 እ.ኤ.አ ጋር ሲታይ የ1.7% ተከታታይ ዓመታዊ እድገት አለው፡፡ ከነዚህ አጠቃላይ ምርት 78% የሚሸፍኑት ማንጎ፣ አናናስ፣ አቮካዶ እና ፓፓያ ናቸው፡፡ እነዚህ ምርቶች 90% ያክል የሚመረቱት በታዳጊ ሀገራት ሲሆን አሜሪካ (U.S.A) እና አውሮፓ ሕብረት ደግሞ የምርቶቹን 70% ገበያ መዳረሻ ናቸዉ (FAO,2014)፡፡ በተመሳሳይ ዓመት (በ2014 እ.አ.) የዓለም የአትክልት ምርት ከአንድ ቢልዮን ሜትሪክ ቶን በላይ ሲሆን ከዚህም በቀዳሚነት የሚጠቀሱ የምርት ዓይነቶች ቲማቲም፣ ሐብሐብ፣ ሽንኩርት፣ ጎመን፣ ዱባ፣ መደረቻ (egg plant) ፣ ካሮት እና ቃሪያ ዋነኛ ምርቶች ሲሆኑ በማምረት የሚታወቁት ሀገራት ግን ቻይና እና ህንድ ከኤሽያ፣ ናይጄሪያ እና ታንዛኒያ ከአፍሪካ እና ብራዚል ከላቲን አሜሪካ ናቸው (statista, 2015) ፡፡

የሀገራት የዓለም የአትክልት እና የፍራፍሬ ንግድ ተሳትፎ ካላቸዉ የምርት መጠናቸዉ ድርሻ ጋር የሚስተካከል አይደለም፡፡ ለምሳሌ የቻይና እና የህንድ ብናይ እነዚህ ሀገራት ከዓለማችን ከፍተኛ አምራች ቢሆኑም ሀገራቸዉ ውስጥ ካላቸው ከፍተኛ ገበያ በዘርፉ ኤክስፖርት በማድረግ እምብዛም የሚጠቀሱ አይደሉም፡፡ የአትክልት ምርት ኤክስፖርት በማድረግ የተሻለ ተሞክሮ ያላቸው የላቲን አሜሪካ ሀገራት (ሜክሲኮ፣ ቺሊ እና ብራዚል) እና የሜድትራንያን ሀገራት (ሞሮኮ፣ ጣሊያን እና እስራኤል) ናቸው (Diop and Jaffee, undated) ፡፡

ብራዚል በምድር ወገብ አካባቢ ሰፊ መሬት ያላት እና ለግብርና በተለይም ለፍራፍሬ ምርት የሚመች ስነ ምህዳር፣ በቂ ውሃ እና የአፈር ዓይነት ያላት ሀገር ናት፡፡የሀገሪቱ የፍራፍሬ ምርት በተወሰኑ ቦታዎች እና ምቹ የተፈጥሮ ሀብት ባለበት ቦታዎች የተወሰነ ሲሆን እሱም በደቡብ ምሥራቅ 49.8 ከመቶ እና በሰሜን ምስራቅ 27.0 ከመቶ የሀገሪቷ የፍራፍሬ ምርት የሚመረቱበት አከባቢዎች ናቸዉ፡፡ ብራዚል ከቻይና (140 ሚሊዮን ቶን) እና ከህንድ(158 ሚሊዮን ቶን) ቀጥላ ከዓለም ሦስተኛ (38 ሚሊዮን ቶን በማምረት) የፍራፍሬ አምራች ሀገር ስትሆን 2.3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ይሸፍናል፡፡ብራዚል በተለያየ ጊዜ የተሳኩ የፍራፍሬ ምርት ትራንስፎርሜሽን ያደረገች ሲሆን በተለይም ከ1998 ($120 ሚሊዮን) እስከ 2004 ($370 ሚሊዮን) በ300% እድገት ያሳየ የፍራፍሬ ምርት ለዓለም ገበያ አቅርባለች፡፡

### 2.2.1. የሰዉ ሀይል ልማት

ብራዚል ከ100,000 በላይ በምርምር ላይ የተሰማሩ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠኑ የሰው ኃይል ያላት ሲሆን በየአመቱም ከሁሉም የሀገሪቷ ዩኒቨርስቲዎች ከ13,000 በላይ በሦስተኛ ዲግሪ (PhD) የትምህርት ደረጃ ተመርቀው የሰው ሀይል ገበያውን ይቀላቀላሉ (Nelson, 2013; Zuurbier 2013) ፡፡

በመንግሥት የሚደገፈው የሀገሪቱ ትልቁ የምርምር ማዕከል የሆነው የብራዚል ግብርና ምርምር ኮርፖሬሽን (EMBRAPA) በሆርቴካልቸር ልማት ዘርፍ ከፍተኛ ምርምር የሚያደርግ እና በሺዎች የሚቆጠሩ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን ለማሰባሰብ እና ለማፍራት የበቃ ድርጅት ነዉ፡፡ ኮርፖሬሽኑ ከሚያደርጋቸው የግብርና ምርምር ውስጥ በሆርቲካልቸር የባዮቴክኖሎጂ ምርምር በቀዳሚ የሚጠቀስ ሲሆን በዚህም ዘርፍ ከ10,000 በላይ ከፍተኛ ተመራማሪዎች ከ2000 በሚበልጥ የጥናት ቡድኖች ውስጥ በማካተት የምርምር ሥራን በመስራት የዘርፉን እድገት እየደገፉ ይገኛሉ (Cardoso, undated) ፡፡ የብራዚል የፍራፍሬ ምርት በከፍተኛ የሰው ጉልበት (labour intensive) ላይ የተመሰረተ ሲሆን በአንድ ሄክታር የፍራፍሬ ማሳ ከ2-5 ለሚሆኑ ሰዎች የሥራ ዕድል ፈጥሮአል፡፡ በአትክልት ልማት ዘርፍ 7.3 ሚሊዮን ሰዎች በ2014 ሥራ ላይ እንደተሰማሩ መረጃዎች ያመለክታሉ (statista, 2015) ፡፡

### 2.2.2. የቴክኖሎጂ ደረጃ

በብራዚል የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ለማሳደግ በዘርፉ የተሻሻሉ ቴክኖሎዎችን በመጠቀም ረገድ ከፍተኛ ስኬት አስመዝግባለች፡፡ በዚህ ረገድ የብራዚል ግብርና ምርምር ኮርፖሬሽን (EMBRAPA) እና ሌሎች የምርምር ማዕከላት ባደረጉት የቴክኖሎጂ ፈጠራ እና ማላመድ በሀገሪቱ ከ300 በላይ የሚሆኑ የተለያዩ ሀገር በቀል እና ከውጭ የገቡ የፍራፍሬ ዝርያዎች ይገኛሉ፡፡ በዚህ የተሻሻለ ቴክኖሎጂ ከመጠቀማቸዉ የተነሳ የብራዚል የፍራፍሬ ምርት ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ እሴት ከተጨመረበት በኋላ ነው ለገበያ የሚቀርበው፡፡

በብራዚል በተለይም ለአትክልት ምርት ጥብቅ እርሻ ቴክኖሎጂ አጠቃቀማቸዉ በተሻለ ደረጃ ያለ ሲሆን በተለይም ጥላ (umbrella) የሚባለው ጥብቅ እርሻ ዓይነት በስፋት ጥቅም ላይ የዋለ ነዉ፡፡

ሀገሪቷ ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በከፍተኛ መጠን የመስኖ ቴክኖሎጂ የምትጠቀም ሀገር ስትሆን በዋናነትም የጠብታ መስኖ (drip irrigation)፣ እና ሃይድሮፖኒክስ (hydroponics) በስፋት ሥራ ላይ ዉሎአል (Guedes, 2010)፡፡ የብራዚላዊያን የመስኖ ግብአት ገበያ ስናይ 80% በመርጨት ዘዴ (aspersion system)፣ 7% በብናኝ መልክ የመርጨት ዘዴ (micro-aspersion) ፣ እና 4% በማንጠባጠብ (dripping system) የተያዘ ነው፡፡

የአትክልትና ፍራፍሬ ዘር እና ችግኝ ለማባዛት የቲሹ ካልቸር ቴክኖሎጂ የመጠቀም ልምዳቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ዓለም ላይ ያሉ የአትክልት ዘር ወይም ችግኝ አቅራቢ ድርጅቶች በብራዚል ቅርንጫፍ በመክፈት እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ በሀገሪቷ 7 ትላልቅ የአትክልት ዘር አቅራቢ ድርጅቶች ያሉ ሲሆን እነሱም የየራሳቸው የዘር ማባዣ እና የምርምር ማዕከል በመጠቀም ለሁሉም የብራዚል ስነምህዳር የሚመች ዘር ወይም ችግኝ ይቀርባሉ፡፡

በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት እና ምርታማነትን ለማሳደግ መንግሥት ከፍተኛ በጀት ለምርምር ሥራ በየዓመቱ የሚመድብ ሲሆን በዋናነትም በብራዚል የግብርና ምርምር ኮርፖሬሽን (EMPRAPA) ሥር የሚተዳደር የአትክልት ምርታማነት ማሳደግ ላይ ብቻ ትኩረት በማድረግ ምርምር የሚያደርግ ማዕከል አላቸው፡፡ በካምፕናስ (Campinas) አካባቢ የሚገኘው የአግሮኖሚ ኢንስቲቱዩት (institute for agronomia-IAC) በአበባ፣ በመዓዛማ ሰብሎች እና በአትክልት ምርቶች ላይ ምርምር የሚያደርግ ሲሆን በማዕከሉ ብቻ ከ20 በላይ የሚሆኑ በሶስተኛ ዲግሪ (PhD) ደረጃ የሰለጠኑ ተመራማሪዎች አሉ (Gueded, 2010; Zuurbier,2013)፡፡

የሀገሪቱ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ከቦታ ቦታ የሚለያይ ሲሆን ይህም ካለው የተፈጥሮ ፀጋ እና ከአምራቾች የአቅም ሁኔታ የሚወሰን ነው፡፡ በግሪን ሀውስ ለሚመረቱት የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በሚጠቀሙት የተሻለ ቴክኖሎጂ የሙቀት እና የውሃ መጠንን ይቆጣጠሩታል፣ አፈር ወለድ የበሽታ መንስኤዎች (pathogen) እና ሌሎችንም በተሳካ መንገድ በመቆጣጠር ምርት እና ምርታማነታቸውን አሳድገዋል፡፡ ከአፈር ጋር ተያይዘው ለሚከሰቱት ችግሮች (salination, diseases and physical degradation) ለመፍታት ሲባልም በተጨማሪነት ያለ አፈር የማምረት ቴክኖሎጂ እና ዘዴን የመጠቀም ሁኔታ በከፍተኛ መጠን እያደገ መቷል፡፡ ውሃን እና ማዳበሪያን የመቀላቀል ዘዴ (fertigation) በመጠቀም በመስኖ የማልማት ዘዴም በሰፊው ጥቅም ላይ እየዋለ ያለ ቴክኖሎጂ ነው (Gueded, 2010)፡፡

### 2.2.3. የመሠረተ ልማት አቅርቦት

የብራዚል የመንገድ መሰረተ ልማት አቅርቦት ከክልል ክልል የሚለያይ ሲሆን በተነፃፃሪ ከፍተኛ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ባለበት በሀገሪቱ የደቡብ እና የደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች የተጠናከረ እና የተሻለ የመሰረተ ልማት አቅርቦቶች አሉ፡፡ የሀገሪቷ 60% የሚሆነው የመጓጓዣ ዘዴ በአውራ ጎዳና መንገዶች በኩል ነው፡፡ በሀገሪቷ 29,000 ኪ.ሜ የባቡር ሀዲድ ዝርጋታ ያለ ሲሆን የሀገሪቱን የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በሀገር ውስጥ እና ወደ ወደብ በማጓጓዝ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ የሚጫወት ሲሆን ከአጠቃላይ የሀገሪቱ የባቡር አገልግሎትም 25% ያህሉ የባቡር ትራንስፖርት ሀገሪቷ ከሌሎች አጎራባች ሀገሮች ማለትም ከአርጀንቲና፣ ቦሊቪያ እና ከኡራጋይ ጋር እንዲትተሳሰር አድርጓታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እስከ 2023 እ.አ ድረስ መንግሥት የ12,000 ኪ.ሜ የባቡር ሀዲድ በመዘርጋት በዘርፉ የሚታየውን የመሰረተ ልማት ችግር በዘላቂነት ለመፍታት እየሰራ ይገኛል፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ሀገሪቷ 40,000 ኪ.ሜ በውሃ ላይ ማጓጓዝ የሚችል ዕምቅ አቅም ቢኖራትም የተጠቀመችዉ ግን ከዕምቅ አቅሟ 13% ብቻ ነው፡፡

ብራዚል ውስጥ አምስት ዓለም አቀፍ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ ማረፊያዎች ያሉ ሲሆን እነዚህ የአውሮፕላን ማረፊያዎች መንገደኞችን ከማጓጓዝ በተጨማሪ ለዕቃ (cargo) ማጓጓዣም ጭምር ጥቅም እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ የአውሮፕላን ማረፊያዎች የተሻለ ሊባል የሚችል የማቀዝቀዣ እና የማከማቻ ክፍሎች የተሟሉላቸው ስለሆነ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን ከሀገሪቷ ወደ አሜሪካ እና አውሮፓ ሀገራት ለማጓጓዣ ጥቅም ላይ እየዋሉ ይገኛሉ፡፡

በብራዚል በ2014 40 (አርባ) በአውሮፓ የጥራት ደረጃ ግሪን ሀውስ የሚያመርቱ ተቋማት አሉ፡፡ ከዋጋዋ አንፃር ሲታይ ሀገር ውስጥ የሚመረተው ጥብቅ እርሻ  ግብአቶች አነስተኛ ሲሆኑ ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ጥላ (umbrella) የሚባለው ጥብቅ እርሻ ዓይነት በሜትር ስኩዌር 11.9 የአሜሪካን ዶላር አካባቢ ነው፡፡ በግሪን ሀውስ ለሚመረቱ አትክልትና ፍራፍሬ የሚሆኑ ጥብቅ እርሻ ፕላስቲክ እና የአየር ሙቀት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችም ሁሉ በሀገር ውስጥ ይመረታሉ፡፡ ለአትክልትና ፍራፍሬ ችግኝ ወይም ዘር ማብቀያ የሚሆን የማብቀያ ጠረጴዛ (growing tables) ቀደም ብለው በኔዘርላንድ የተመረተውን ሲጠቀሙ የነበረ ሲሆን ዋጋው ውድ ከመሆኑ ጋር

ተያይዞ በሀገር ውስጥ ከአልሙኒየም የተሰራ የማብቀያ ገንዳ በመፈብረክ በሰፋት ሥራ ላይ እንዲውል አድርገዋል፡፡

የሀገሪቱ መንግሥት በተለያየ ጊዜ ባደረገው ኢንቨስትመንት እና የገጠር የኤሌክትሪክ ማስፋፍያ ፕሮጀክቶች 98% የሀገሪቱ ሕዝብ እና 93% የገጠር ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ መሰረተ ልማት ተሟልቶላቸው አስተማማኝ የሀይል አቅርቦት ያገኛሉ (zurbier, 2013)፡፡ ይህ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በዘመናዊ መልክ ለማምረት እና የሚያስፈልገውን የሙቀት መጠን በመጠበቅ የተሻለ ጥራት ያለዉ ምርት ለዓለም ገበያ በማቅረብ ከዘርፍ ሀገሪቷ የተሻለ ተጠቃሚ እንድትሆን ካደረጓት ጉዳዮች በቀዳሚነት ሊነሳ የሚችል ነው፡፡

## *2.2.4. የሎጀስቲክስ እና ገበያ ልማት*

በአንድ ሀገር ውስጥ የተደራጁ የሎጀስቲክስ አገልግሎት መኖር የዳበረ ኢኮኖሚን ለመገንባት ትልቅ ድርሻ የሚጫወት ሲሆን ምክንያታዊ የሆነ የምርት ዋጋ እንዲኖር ለማድረግ እና ተወዳዳሪ እና የተረጋጋ ገበያ ለመፍጠር ያስችላል፡፡ ከዚህ አንፃር የብራዚል የአትክልትና ፍራፍሬ ሎጀስቲክስ እና ገበያ አቅርቦት እና አጠቃቀም በሀገሪቱ ለተመዘገበው የዘርፉ እድገት የበኩሉን ድርሻ አበርክቷል፡፡

በብራዚል የግብርና ምርምር ኮርፖሬሽን (Embrapa) በ2013 እ.አ. በተደረገው ጥናት በብራዚል 30% የፍራፍሬ ምርት እና የ35% የአትክልት ምርት ለብክነት ይዳረጋል፡፡ ከዚህ ውስጥ ግማሽ ያህሉ የሚበላሹት ከማጓጓዣ ጋር በተያያዙ ችግሮች ሲሆን የተቀሩት ደግሞ ከአያያዝ ጉድለት ጋር ተያይዞ በሱፐር ማርኬት እና በቂ የማሸጊያ ሥራዎች ካለመስራታቸው ጋር ተያይዞ ነው፡፡ በሀገሪቷ በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት የድህረ ምርት ብክነት በጣም ከፍተኛ ሲሆን በተከታታይ የሎጀስቲክስ አቅርቦትን ለማሻሻል በተሰራው ሥራ ግን ትርጉም ባለው መልኩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣቱን ከሀገሪቱ የተገኙት መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ባለፉት 10 ዓመታት ብራዚል ደረቅ ጭነት የማጓጓዣ አቅሟን በተለይም አትክልትና ፍራፍሬ ማጓጓዣ አቅሟን ከሁለት እጥፍ በላይ ያሳደገች ሲሆን በተለይም የወደብ አገልግሎትን የጉምሩክ ክሊራንስን እና የመጓጓዣ ዘዴዎችን በማዘመን የተገኘ ለውጥ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ በ2010 እ.አ. ከዓለማችን ሶስተኛዋ የግብርና ምርት ላኪ ሀገር ሆናለች፡፡ በብራዚል 60% የአትክልት ምርት

የቅዝቃዜ መጠበቂያ መሰረተ ልማቶች እና ሎጂስቲክስ የተሟሉላቸው ስለሆነ ምርቶቹ ጥራታቸውን ጠብቀው ወደ ሚፈለገው ቦታ ማድረስ አስችለዋል፡፡

በብራዚል በ2010 እ.አ  ከአጠቃላይ በቀላሉ የሚበላሹ (perishable) የግብርና ምርቶች 20% በአየር ትራንስፖርት ኤክስፖርት ታደርጋለች፡፡ ይህ ዓይነቱ የአየር ትራንስፖርት የካርጎ አገልግሎት በየአመቱ በብራዚል በ10.13% እያደገ እየሄደ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ የ0.65% የሀገሪቱን የሎጀስቲክስ አገልግሎት ድርሻ አለው፡፡ በሀገር ውስጥ ሆነ ለኤክስፖርት የሚውሉ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች የቅዝቃዜ መጠናቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ እና እንዲጓጓዙ ከምርት አሰባሰብ ጀምሮ በማከማቻ፣ በማሸጊያ፣ እና በማጓጓዣ ከፍተኛ ጥንቃቄ ይደረጋል፡፡ ይህን በማድረግ ሀገሪቷ ረጅም ርቀት በማጓጓዝ ለአውሮፓ እና ለመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ከፍተኛ ጥራት ያለው የፍራፍሬ እና አትክልት ምርቶችን ለማቅረብ ችላለች፡፡ የብራዚል ኢኮኖሚ ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ መጠን እያደገ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የሀገሪቷ የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርት ኤክስፖርት እያደገ ስለመጣ በዚያኑ መጠን የሎጀስቲክስ ፍላጎትም በከፍተኛ መጠን ማደግ ችሏል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ የሎጀስቲክስ ዋጋ መናር የተከሰተ ሲሆን ይህም ዋጋ ከአጠቃላይ የሀገሪቷ ምርት (GDP) 20% የሚሆነውን ያህል ይሸፍናል፡፡

የተቀናጀ የሎጀስቲክስ አገልግሎት ለመስጠት መንግሥት ተከታታይ የለውጥ ሥራዎች የሰራ ሲሆን በዚህም በዋናነት ሊጠቀስ የሚችለው ያልተቀናጀ  እና በቂ ያልሆነ የትራንስፖርት አገልግሎት ማሻሻል ረገድ የተሰራው እና ብዙ ለውጥ የታየበት አንዱ ነው፡፡ ይህ ለማድረግ የተቀናጀ የሎጀስቲክስ መፍትሄ (integrated) በኮንትራት መልኩ ሥራ ላይ በማዋል በዘርፉ ለውጥ ሊታይ ችሏል፡፡ መንግሥት በሚያደርገው በተጨማሪ የግሉ ዘርፍ በሎጀስቲክስ አቅርቦት እንዲሳተፍ በመደረጉ አገልግሎቱ እና አቅርቦቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል ታይቶበታል፡፡ በሀገሪቱ ዋናዎቹ የሎጀስቲክስ አገልግሎት አቅራቢ የሆኑ ድርጅቶች DHL, TNT, America Latina logistica, Comprtia Vale de Rio Dole, express Mercurio, Penske and Ryder ናቸው፡፡ ለግብርና ልማት የሚውሉ በተለይም የመስኖ ግብአቶች ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ ምንም ዓይነት የጉሙሩክ ቁጥጥር እና ታሪፍ የለበትም፡፡ ከዚህ አንፃር ቀልጣፋ የሆነ የወደብ እና የጉሙሩክ አገልግሎት ስለሚሰጥ ማንኛውም ሰው ምንም መሰፈርት እንዲያሟላ ሳይጠየቅ የመስኖ ግብአቶችን ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት መጠቀም ይችላል፡፡

የብራዚል የሆርቲካልቸር ምርት ገበያ ሰንሰለት እና መዳረሻዎች  ስንመለከት የሀገሪቷ የፍራፍሬ ምርት ገበያ በዓመት እስከ 5.8 ቢልየን ዶላር ገቢ የሚያስገኝ ሲሆን ዋነኞቹ የንግድ አጋሮቹ ደግሞ

አሜሪካ፣ አርጀንቲና ቻይና፣ ጀርመን፣ ኔዘርላንድ፣ ጃፓን እና ቺሊ ናቸው (zurbier, 2013) ፡፡ ሀገሪቷ በዘርፉ በዓለም አቀፍ ገበያ ትልቅ ትኩረት እና ቦታ ያላት ሲሆን ለዚህም ሲባል በጥራት እና ልቆ ለመገኘት፣ በዝርያ ማሻሻል፣ በበሽታ ቁጥጥር፣ በመስኖ ሥራ እና ገበያ ተኮር ሥራዎች ላይ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት አድርጋለች (zurbier, 2013)፡፡

ብራዚል ኤክስፖርት የምታደርጋቸው የትሮፒካል ፍራፍሬ ምርቶች ሲሆን በዋናነት ማንጎ፣ Melons፣ ብርቱካን፣ ወይን፣ ፓፓያ እና ሙዝ ናቸው፡፡ ሀገሪቱ ወደ ሀገር ውስጥ የምታስገባው የወይና ደጋ ፍራፍሬዎች (Temperate fruit) ሲሆኑ ኤክስፖርት ከምታደርገው በእጅጉ ያንሳል፡፡ ወደ 70 ከመቶ የብራዚል የፍራፍሬ ኤክስፖርት ምርት ለአውሮፓ ገበያ የሚላክ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ለኤሽያ እና ለመካከለኛው ምሥራቅ ገበያ በብዛት ማቅረብ ጀምረዋል (Souza and Neto 2010)፡፡ የብራዚል የአትክልት ምርት ስናይ የዓመት ምርት መጠኑ ከሌሎች ሀገሮች አንፃር ሲወዳደር በጣም ከፍተኛ የሚባል ሲሆን በ2014 እ.አ. 12,064,810 ሜትሪክ ቶን 890688.26 ሄክታር መሬት በመጠቀም እየተመረተ ሲሆን ምርታማነትን ስናይ በአማካይ 3.56 ቶን በሄክታር ነዉ (ECO HIVE, 2015)፡፡ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚውል የአትክልት ምርት ኤክስፖርት ከሚደረገው በጣም ከፍተኛ ሲሆን በሀገር ውስጥ ያሉ ትላልቅ የአትክልት ሱፐርማርኬቶች እና ቸርቻሪዎች በመጠቀም ለገበያ ይቀርባል፡፡

የብራዚል የአትክልትና ፍራፍሬ ገበያ በሀገር ውስጥ እና በኤክስፖርት ደረጃ ሲታይ ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ ዘርፉ የሀገሪቷ አጠቃላይ ምርት (GDP) ከሚያድገው በላይ እያደገ ይገኛል፡፡ በዘርፉ ጥብቅ እርሻ ቴክኖሎጂዎች ገበያ፣ የዘር ወይም ችግኝ እና የሎጀስቲክስ ገበያ በፍጥነት እያደጉ ከሚገኙት ግብአቶች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በሀገር ውስጥ የሱፐር ማርኬቶች መስፋፋት (በዓመት የ3% እድገት) ለአትክልትና ፍራፍሬ ግብይት መሻሻል የራሱን ድርሻ ተወጥቷል፡፡ የብራዚል ቅርንጫፍ የሆነው ዩኒቬጅ (UNIVEG) የንግድ ኩባንያዎች በሀገር ውስጥ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማከፋፈል የጎላ ድርሻ አለው (Gueded, 2010)፡፡

## 2.2.5. የግል ባህብቶች ተሳትፎ

ብራዚል ኤክስፖርት ከምታደርጋቸው 70 ከመቶ ማንጎ እና 60 ከመቶ ወይን ከገበሬዎች ማሳ የሚሰበሰብ ነው (Souza and Neto 2010)፡፡ የግል ባለሀብቶችም ቢሆን የኢንቨስትመንት ተሳትፎአቸዉ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ በዘርፉ ሀገሪቱ በምታመርተዉ ምርት ላይ ከፍተኛ ድርሻ አላቸዉ፡፡

ዩኒቬጅ (UNIVEG) በብራዚል የአትክልትና ፍራፍሬ የገበያ ስርአቱ እንዲሳለጥ ትልቅ ሚና ተጫዉቶአል፡፡ ይህ ኩባንያዎቹ ምርቶቻቸዉን ወደ ሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውስጥ ወደሌሎች ሀገሮች ለማጓጓዝ በቂ እና ዘመናዊ የማጓጓዣ ዘዴዎችን የሚጠቀም ሲሆን አገልግሎቱንም ይበልጥ ለማስፋት እየሰራ መሆኑ ይታያል፡፡ ኩባንያው ቀዝቃዛ መኪናዎችን እና ጥራት ያለው የማሸግ አገልግሎቶችን ስለሚሰጥ የሀገሪቱ ምርት ጥራቱን ጠብቆ ወደ ሚፈለገው የኤክስፖርት ገበያ እንዲጓጓዝ ረድቷል፡፡

ለአትክልትና ፍራፍሬ የሚውል የሎጀስቲክስ አገልግሎቶችን የብራዚል መንግስት ከሚያቀርበው በተጨማሪ የአውሮፓ ትላልቅ የሎጀስቲክስ አቅራቢ ኩባንያዎች በሀገሪቱ ስለሚንቀሳቀሱ ምርቶቹን ተወዳዳሪ በሆነ ዋጋ እና ጥራቱን በጠበቀ መልኩ በሀገር ውስጥ እና ለኤክስፖርት ገበያ ማቅረብ ችለዋል፡፡ እነዚህን የአውሮፓ የሎጀስቲክስ ኩባንያዎች በፈጠሩት ውድድር እና ልምድ ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ የሀገር ውስጥ የግል የሎጀስቲክስ አቅራቢዎች መበራከት በመቻላቸው በዘርፉ ያለውን የዋጋ እና የአቅርቦት ችግር በከፍተኛ መጠን መቀነስ ችሏል፡፡ የግሉ ዘርፍ በብራዚል በሀገሪቱ ለአትክልትና ፍራፍሬ ግብይት የሚረዱ ሱፐርማርኬት እና ሌሎችንም የገበያ ማዕከላትን ከመገንባት በተጨማሪም የሀገር ውስጥ እና የኤክስፖርት ንግዱ እንዲጠናከር የጎላ ሚና ተጫዉተዋል፡፡

### 2.2.6. የጥራት እና ደረጃ ሁኔታ

ጥራቱን የጠበቀ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ለገበያ ማቅረብ የሀገራትን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን እንደሚጨምር እሙን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ብራዚል በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ ለመሆን ጥራት ላይ ትኩረት አድርጋ በመስራት ስኬቶችን አስመዝግባለች፡፡ በተለይ ሁሉም ኤክስፖርት የሚደረጉ የፍራፍሬ ምርቶቿ በዘርፉ የተቀመጠውን የዓለም የመልካም እርሻ (Global GAP) እና ISO የሚያሟሉ ስለሆነ በቀላሉ ምርቶቹ በአውሮፓ፣ በአሜሪካ እና በመካከለኛው ምሥራቅ ገበያ ቀርበው ተወዳዳሪ መሆን ችለዋል፡፡ ከነዚህ የዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃ ከማሟላት እና ከመጠቀም በተጨማሪ በሀገራቸው BRC Global Food የሚባል የምግብ ደህንነት እና የጥራት ደረጃዎችን በማስቀመጥ ሁሉም የሀገሪቱ የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርት እና ድህረ ምርት አያያዝ ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን እየሰሩበት ይገኛሉ፡፡

የብራዚል ምርቶች በአውሮፓ ገበያ በብዛት ተቀባይነት አግኝተው ተወዳዳሪ ሊሆኑ የቻሉበት አንዱ ምክንያት በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ረገድ የአውሮፓን የጥራት እና ደረጃ መስፈርቶችን አሟልተው መቅረብ ስለቻሉ ነው፡፡ የአውሮፓ የጥራት እና ደረጃ መስፈርቶች በጣም በጥልቀት የተብራሩ እና ከምርቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሁሉንም ጉዳዩች ስለሚዳስሱ መስፈርቱን አሟልቶ መገኘት ትልቅ እና ተከታታይነት ያላቸውን ሥራዎች መስራትን የሚጠይቅ ቢሆንም ሀገሪቷ ይህን በአግባቡ ተወጥታዋለች፡፡

የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ጥራት የተሻለ ጥራት ያለው ዝርያ መጠቀምን ስለሚጠይቅ ዝርያ ማሻሻል እና የዘር ወይም ችግኝ አቅርቦት ላይ በምርምር የታገዘ ከፍተኛ ሥራ እና ጥንቃቄዎች ይወሰዳሉ፡፡ በዘርፉ ያሉትን የባዮቴክኖሎጂ እና የማራባት (breeding) ቴክኖሎጂዎችን ሁሉንም የሀገሪቷ ስነ ምህዳር በሸፈነ መልኩ ይሰራል ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሰፊ እና ተከታታይ ሥራዎች ሰርተዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ ብዙ የተሻሻሉ እና ምርታማነታቸው ከፍተኛ የሆነ የአትክልትና ፍራፍሬ ዝርያዎች ለምርት እየተጠቀሙ ይገኛሉ፡፡

የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርት በተለይም ከትላልቅ የባለሀብቶች ማሳ የሚመረተው በምርት ወቅት አስፈላጊው የሙቀት እና የእርጥበት መጠን የሚጠበቅለት ሲሆን በእድገት እና በመሰብሰብ ወቅትም በበሽታ እንዳይጠቃ አስፈላጊው የተቀናጀ የበሽታ መቆጣጠሪያ መንገዶችን በመተግበር የምርት ጥራት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ሰፊ የክትትል ሥራዎች ይሰራሉ፡፡ ምርቱ ከተሰበሰበም

በኋላ አስፈላጊው የሙቀት ሰንሰለት እንዲጠበቅለት እና ተቀነባብሮ ጥራት ባለው ማሸጊያ ከታሸገ በኋላ ኤክስፖርት ይደረጋል፡፡ ይህ ትኩረት ሰጥተው በሰለጠነ ባለሙያ በመታገዝ እና አስፈላጊውን ዋጋ በመክፈል የሚሰሩት ጥራት የማስጠበቅ ሥራ በአለም አቀፍ ደረጃ ጥራት ያለው ምርት በማቅረብ መልካም ሥም ያተረፉ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በየትኛውም ገበያ ተወዳዳሪ የሆነ ምርት ሊኖራቸው ችለዋል፡፡

# ክፍል ሶስት

## 3. *የክፍተት ትንታኔ (Gap Analysis)*

በክፍተት ዳሰሳ ጥናት (Gap Analysis) የሀገር ዉስጥ እና የዓለም አቀፍ ነባራዊ ሁኔታን መዳሰስ፣ የዘርፉን የወደፊት ፍላጎት መወሰን፤ በነባሩ እና በፍላጎት መሃል ያለዉን ክፍተት ማሳየት እና እንዴት ክፍተቱን መሙላት እንደሚቻል ማስቀመጥን ይጠይቃል፡፡ በዚህ ክፍል የኢትዮጵያ የአትክልት እና የፍራፍሬ ልማት የክፍተት ትንታኔ ቤንችማርክ ከተደረጉ ሀገራት አኳያ ከሰዉ ሀይል ልማት፣ ከቴክኖሎጂ ደረጃ፣ ከመሠረተ ልማት አቅርቦት፣ ከሎጂስቲክስ፣ ከገበያ፣ ከምርት ጥራት እና ከግል ባለሀብቶች ተሳትፎ አኳያ ተዳሷል፡፡

## 3.1. የሰዉ ሀይል ልማት

የኢትዮጵያ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የማምረት ብቃት የክፍተት ትንታኔ የሰዉ ሀይል የሀገሪቷን ወቅታዊ ሁኔታን እና የቤንች ማርክ ሀገር ሁኔታን በመጠቀም በዘርፉ ያለዉ ክፍተት እንደሚከተለዉ ለማሳየት ተሞክሮአል፡፡

| የቤንች ማርክ ሀገር ሁኔታ | የኢትዮጵያ ሁኔታ | ክፍተት |
|---|---|---|
| የአትክልት እና የፍራፍሬ ልማት ዘርፍ በብራዚል ብቁ የሰለጠነ የሰው ኃይል የተሰማራበት ዘርፍ ሲሆን ባለሙያዎቹ በሀገሪቷ በታየዉ የዘርፉ እድገት ያላቸው ተጽእኖ ትርጉም ያለው ነው፡፡ በሀገሪቱ የሚገኙ ከ2000 በላይ የሚሆኑ የግል እና የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በዓመት ከ5 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎችን የሚያስተምሩ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ በቀጥታም ሆነ በተጓዳኝ በአትክልት እና በፍራፍሬ ልማት ሳይንስ የሚሰለጥኑ ተማሪዎች ቁጥራቸዉ ትልቅ ነዉ፡፡ ሀገሪቷ ከ100,000 በላይ በምርምር ላይ የተሰማሩ የሰለጠነ የሰው ኃይል ያላት ሲሆን በየአመቱም ከ13,000 በላይ በሦስተኛ ዲግሪ (PhD) ተመርቀው የሰው ሀይል ገበያውን ይቀላቀላሉ፡፡<br><br>በፌዴራል የግብርና ምርምር ኮርፖሬሽን (EMBRAPA) በሆርቲካልቸር ምርምር ከ10,000 በላይ ከፍተኛ ተመራማሪዎች ይገኛሉ፡፡ የካምፕናስ (Campinas) የአግሮኖሚ ኢንስቲቱዩት (institute for agronomia-IAC) ብቻ በአበባ፣ በመዓዛማ ሰብሎች እና በአትክልት ሰብሎች ላይ ምርምር የሚያደርጉ ከ20 በላይ የሚሆኑ በሶስተኛ ዲግሪ(PhD) ደረጃ የሰለጡኑ ተመራማሪዎች አሉ፡፡ ይህ በአጠቃላይ የሚያሳየን ሀገሪቷ በዘርፉ የሰዉ ሀይል ልማት ላይ በትኩረት እየሰራች ያለች መሆኗን ነዉ፡፡<br><br>የብራዚል የፍራፍሬ ምርት በከፍተኛ የሰው ሃይል በመጠቀም ላይ የተመሰረተ ሲሆን በአንድ ሄክታር የፍራፍሬ ማሳ ከ2-5 ሰዎችን ይማራሉ፡፡ ከሀገሪቱ የሰው | በሀገሪቱ ከ32 በላይ የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያሉ ሲሆን በሆርቲካልቸር እና ተዛማጅ በሆኑ የትምህረት መስኮች የአመቱ ከ2000 በላይ በመጀመሪያ ዲግሪ (under graduate) ከ13 ዩኒቨርሲቲዎች ይመረቃሉ፡፡ በአትክልትና ፍራፍሬ ልማትና ምርምር ላይ ብቻ የተሰማሩትን የሰው ኃይል ብዛት፣ የሙያ ስብጥርና የትምህርት ደረጃ የሚያሳይ መረጃ ማግኘት ከባድ ቢሆንም ዘርፉ በሚፈልገው ደረጃ በብዛትና በጥራት የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት አለበት፡፡<br><br>በተወሰኑ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ለምሳሌ በሐረማያ፣ በጅማና በሀዋሳ የተማሪዎች ቁጥር ጥቂት ቢሆንም በሁለተኛ እና በሶስተኛ ዲግሪ ደረጃ በዘርፉ ስልጠና ይሰጣል፡፡<br><br>በክልሎች ደረጃ በጣም የተወሰኑ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ውስጥ በሆርቲካልቸር መስከ በሰርተፍኬት እና በዲፕሎማ ደረጃ ስልጠና በመስጠት የተሻለ ጅማሬ በሀገሪቷ አለ፡፡ ከእነዚህ | ከምርትና የቴክኖሎጂ እድገት ፍላጎት ጋር የተመጣጠነ የሰለጠነ ባለሙያ አቅርቦት ስርዓት ለአትክልትና ፍራፍሬ መገንባት አለመቻል ፤<br><br>ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመረቁ ቁጥራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ቢሆንም ዘርፉን ለማዘመን በሚፈለገው ኮሜርሻል ስኬል ለማምረት የሚያስችል ዕዉቀት፣ ክህሎትና ልምድ አለመያዝ፤<br><br>ለአትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች በተለይም አዲስ ጀማሪዎችና ወጣቶች በቂ የስራ ላይ ስልጠና ድጋፍ የሚሰጡ ተቋማት በየአካባቢው አለመኖር፤<br><br>የተጠናከርና ዘርፉን ትራንስፎርም ማድረግ የሚችል የሆርቲካልቸር ኤክስቴንሽን ስርዓት መገንባት አለመቻል ናቸው፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| ጉልበት (labor force) ስብጥር 19.3% የግብርና ሰራተኞች ሲሆኑ ከዚህ ዉስጥም በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ዘርፍ የተሰማሩት ሰዉ ሀይል ድርሻም ትልቅ ነዉ።<br>በሀገሪቱ ከ7.3 ሚሊዮን በላይ በአትክልት ልማት በመካከለኛና በከፍተኛ የትምህርት ደረጃ የሰለጠኑና በሥራ ላይ እንደተሰማሩ የ2014 መረጃዎች ያመለክታሉ ። | ኮሌጆች የሚመረቁትና ዘርፉ በዚህ ደረጃ ከሚፈልገዉ ቁጥርና ጥራት አኳያ ሲታይ ግን አሁንም ብዙ መስራት እንደሚያስፈልግ ያሳያል።<br>በሀገሪቱ ባሉት የምርምር ማዕከላት የዘርፉ ተመራማሪዎች ብዛት እና የትምህርት ደረጃ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ለዘርፉ የቴክኖሎጂ እድገት ማነቆ እንደሆነ ነዉ። | |

## 3.2. የቴክኖሎጂ ደረጃ

ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና እድገት በጣም ወሳኝ ነዉ፡፡ ቴክኖሎጂ ምርት እና ምርታማነትን ከማሳደግ በተጨማሪ ጥራት ያለዉ ለማምረት እና በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ለመሆን ትልቅ ድርሻ ያበረክታል፡፡ ከዚህ አኳያ በኢትዮጵያ ያለዉ ክፍተት እንደሚከተለዉ ተተንትኗል፡፡

| የቤንች ማርክ ሀገር ሁኔታ | የኢትዮጵያ ሁኔታ | ክፍተት |
|---|---|---|
| ከአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ሀገራት የተሻለ ተጠቃሚ የሚሆኑት በዘርፉ የሚያስፈልጉትን ወሳኝ ቴክኖሎጂዎችን ማለትም ግሪን ሀዉስ መጠቀምን፣ መስኖን ማስፋፋትን፣ ዝርያን ማሻሻልን፣ ምርትን በኢንዱስትሪ ማቀነባበርን (ዕሴት መጨመርን) በዋናነት መስራት ሲችሉ ነዉ፡፡ ብራዚል የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ለማሳደግ  የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን ከመጠቀም ረገድ ከፍተኛ ስኬት አስመዝግባለች፡፡ ይህም የአትክልት እና የፍራፍሬ ዝርያዎችን ከማሻሻል ጀምሮ የአመራረት ዘዴን እና የድህረምርት አያያዝ ሁኔታዎችን ከማሻሻል ጋር የተያያዙ የእዉቀት እና የግብአት ማሻሻያዎች ሥራ በተጠናከረ እና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ በማከናወኗ ነዉ፡፡ ከዚህም የተነሳ በብራዚል ለምሳሌ ከ300 በላይ የተለያዩ የፍራፍሬ ዝርያዎች ይገኛሉ፡፡ ይህም ሀገሪቷ የፍራፍሬ ዝሪያዎችን ለማሻሻል ያደረገችዉን ከፍተኛ ጥረት ዉጤት ነዉ፡፡<br>የሀገሪቱ የፍራፍሬ ምርት ለገበያ የሚቀርበው ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ እሴት ከተጨመረበት በኋላ ነው፡፡ ለምሳሌ 98 ከመቶ ኤክስፖርት የሚደረግ የብርቱካን ምርት በኢንዱስትሪ የተቀነባባረ ነዉ፡፡ | የሀገሪቷ የዘመናዊ ግብርና ቴክኖሎጂ አጠቃቀም አነስተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የምርት ብክነት፣ የጥራት ጉድለት እና የተወዳዳሪነት ማነስ በዘርፉ የሚታይ ነዉ፡፡<br>በአማካይ በአብዛኛው አምራች የተደረሰበት የአትክልትና ፍራፍሬ ምርታማነት ካለው አቅም አንፃር በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ የሽንኩርት እና የቲማቲም ምርታማነት በአማካይ 90 ኩንታል በሄክታር እና 70 ኩንታል በሄክታር ሲሆን በራሳችን ምርምር አቅም የሽንኩርት 400 ኩንታል በሄክታር እና  ቲማቲምን 350 ኩንታል በሄክታር በቅደም ተከተላቸው ማግኘት ይቻላል፡፡ ይህ ክፍተት በአለም አቀፍ ምርታማነትና የዲቃላ ዝርያዎች አንፃር ሲታይ በጣም ሰፊ ነው፡፡<br>ከአትክልት ዘርፍ በሽንኩርት እና ከስራስር ደግሞ በድንች ዝርያ ማሻሻል በምርምር ደረጃ ጉልህ ስኬቶች ያሉ ቢሆንም ለአምራቾች የዘር ወይም/እና ችግኝ አቅርቦት አንጻር ግን ከፍተኛ እጥረት ይታያል፡፡<br>የተሻሻሉ የፍራፍሬ ዝርያዎች የማቅረብ አቅም በጣም ውስን ስለሆነ ከበሽታ የፀዳና ምርታማ ዝርያዎች ለምሳሌ ለብርቱካን፣ ለመንደሪንና ለሎሚ ችግኞችን ማግኘት የማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሶአል፡፡ | በፍራፍሬ ረገድ በሀገሪቷ የሚደረጉ ምርምሮች ዝርያዎችን ምርታማነትና ጥራት ከማሻሻል አንፃር ክፍተት መኖር፤<br>በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ የዘር ወይም የችግኝ ብዜት ስርዓት አለመኖር ፤<br>በኢትዮጵያ ጥብቅ እርሻ እና የመስኖ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም በጣም አነስተኛ መሆን፣<br>የኢትዮጵያ የአትክልት እና የፍራፍሬ የቲሹካልቸር አጠቃቀም እና  የድህረ ምርት አያያዝ የሚታዩ ሰፊ ክፍተቶች፤<br>አብዛኛዎቹ ቴክኖሎጂዎች ከውጭ ሀገር የሚገዙ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ |

| | | |
|---|---|---|
| በብራዚል በርካታ ግሪንሀውስ የሚያመርቱ ተቋማት በመኖራቸዉ በተመጣጣኝ ዋጋ መግዛት ስለሚቻል የጥብቅ እርሻ አጠቃቀማቸዉ በጣም ከፍተኛ ነዉ::<br>ብራዚል ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በከፍተኛ መጠን የመስኖ ቴክኖሎጂ የምትጠቀም ሀገር ስትሆን ካላት ለመስኖ ምቹ ከሆነ መሬት ውስጥ 3.5 ሚሊየን ሄክታር (12.1%) ተጠቅመዋል:: ለመስኖ የሚያስፈልጉት ግብአቶች የኢምፖርት ታክስ ስለማይጨመርባቸዉ በተመጣጣኝ ዋጋ አምራቾች ያገኛሉ::<br>የአትክልትና ፍራፍሬ ዘር እና ችግኝ ለማባዛት የቲሹካልቸር ቴክኖሎጂ መጠቀም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ የተሻለ የዘር እና የችግኝ አቅርቦት ስርዓት አለ::<br>የተደራጀ የሰብል ጥበቃ ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ ስለሚጠቀሙ በምርት ላይ የሚደርስ ጉዳት አነስተኛ ነው:: ይህን በማድረግም በዓለም አቀፍ ገበያ ጥራት እና ተቀባይነት ያለው ምርት ለአውሮፓ ገበያ ጭምር ማቅረብ ችለዋል::<br>የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርታማነት ለማሳደግ መንግሥት ከፍተኛ በጀት ለምርምር (R&D) ሥራ በየዓመቱ የሚመድብ ሲሆን በዘርፉ የለዉን የቴክኖሎጂ ፈጠራ በቀጣይነት በማሳደግም ጥልቅ ድርሻ ተጫዉቶአል:: በሀገሪቱ ለሚደረገዉ የዘርፉ የተክኖሎጂ ምርመር የብራዚል የግብርና ምርምር ኮርፖሬሽን (EMPRAPA) ትልቁን የስራ ድረሻ እየተወጣ ነዉ::<br>ብራዚል ከፍተኛ የማቀነባበሪያ ቴክኖሎጂዎችን ስነምትጠቀም ኤክስፖርት የምታደርጋቸው የፍራፍሬ ምርቶች 90% ያህል የሚሆነዉ በኢንዱስትሪ እሴት የተጨመረበት ነው:: | በምርት ሂደት ላይ ያሉትም ዝርያዎች ከረጅም አመታት በፊት የገቡና ማሻሻያ ያልተደረገባቸዉ በመሆኑ ምርታማነታቸው በጣም ዝቅተኛ (ከ10 ቶን/ሄ ያነሰ) ነው::<br>የተቀናጀ የሰብል ጥበቃ ቴክኖሎጂ በአግባቡ በሁሉም አምራቾች ዘንድ ስለማይተገበረ የአትክልትና የፍራፍሬ ምርቶች በኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ለበሽታና ተባይ ጥቃት የተጋለጡ ናቸው::<br>አሁን ባለውም ደረጃ በየአካባቢው ለሚመረተው ምርት በቂ የማከማቻ፣ የማዘጋጃ ክፍል (pack house) እና የቅዝቃዜ ክፍል (cold room) መሰረተ ልማት አለመኖር በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ብክነት ይታያል:: እነዚህ ቴክኖሎጂዎች ከፍተኛ ካፒታልና የሰለጠነ የሰው ኃይል ስለሚፈልጉ በሀገራችን በስፋት ጥቅም ላይ አልዋሉም:: በሀገሪቱ በሚገኙ ጥቂት ኮሜርሻል እርሻዎች ውስጥ እነዚህ ቴክኖሎጂዎች የሚገኙ ሲሆን አጠቃቀማቸው ውጤታማ ግን አይደለም::<br>በኢትዮጵያ የጥብቅ እርሻ(ግሪንሃውስ) በብዛት ለአበባ ልማት በውጭ ባለሀብቶች ጥቅም ላይ ከመዋል አልፎ በስፋት ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ዘርፍ አልተለመደም:: በተወነሰ ደረጃ በጥቂት እርሻዎች ለአትክልት(ቲማቲም) እና ፍራፍሬ (ስትሮቤሪ) ማምረት ጅምር ስራዎች አሉ:: የጥብቅ እርሻ ግብአቶች በሙሉ ወደ ሀገር ዉስጥ የሚገቡ ስለሆነ ዋጋቸዉ ለአምራቹ ዉድ ነው:: የጥብቅ እርሻ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዕዉቀትና ክህሎት አነስተኛ በመሆኑ የአትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ቴክኖሎጂዉን በስፋትና በውጤታማነት ሲጠቀሙበት አይታዩም::<br>በኢትዮጵያ በመስኖ መልማት የሚችል ሰፊ መሬት ቢኖርም እስካሁን ማልማት የተቻለዉ 5.8% ብቻ ነው:: | ዋጋቸው ለአምራቹ ከፍ ያለ መሆን ፤ የአትክልትና ፍራፍሬ አመራረት ከኢንዱስትሪው ጋር ያልተሳሰረ እና አብዛኛዉ ምንም እሴት ሳይጨመርባቸው ለሀገር ዉስጥ እና ኤክስፖርት ማድረግ ናቸው:: |

## 3.3. የመሠረተ ልማት አቅርቦት

ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት በዘርፉ የሚያስፈልጉ ወሳኝ የሆኑ መሰረተ ልማቶች ማለትም የሀይል፣ የመስኖ፣ የገበያ፣ የመገናኛ ዘዴዎች አቅርቦት ምርት ሳይበላሽ የማቆያ ቴክኖሎጂዎች የፓኬጂንግ  እና ሌሎች መሰረተ ልማቶችን ጨምሮ ማሟላት ይጠይቃል፡፡ የነዚህ መሰረተ ልማቶች አለመኖር ወይም በተመጣጣኝ ዋጋ አገልግሎት ማግኘት አለመቻል የምርቶቹ ዋጋ ለሸማቹ እንዲጨምር ከማድረጉም በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥራት ያለው ምርት ለገበያ ማቅረብ አይታሰብም፡፡ ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያ  የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት የክፍተት ዳሰሳ እንደሚከተላዉ ተመልክቶአል፡፡

| የቤንች ማርክ ሀገር ሁኔታ | የኢትዮጵያ ሁኔታ | ክፍተት |
|---|---|---|
| በብራዚል የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርት በብዛት በሚመረትበት በሀገሪቱ የደቡብ እና የደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች የተጠናከረ እና የተሻለ የመንገድ መሰረተ ልማት አቅርቦት አለ፡፡ በሀገሪቷ 29,000 ኪ.ሜ የባቡር ሀዲድ ያለ ሲሆን የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርቶችን በሀገር ውስጥ እና ወደ ወደብ በማጓጓዝ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ይጫወታል፡፡<br>በሀገሪቷ ያሉ የዓለም አቀፍ የአዉሮፕላን ማረፊያዎች ለዕቃ (cargo) ማጓጓዣም ጭምር በስፋት ጥቅም እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ የአውሮፕላን ማረፊያዎች ጣቢያዎች የተሻለ የማቀዝቀዣና የማከማቻ ክፍሎች የተሟሉላቸው ስለሆነ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርቶችን ከሀገሪቷ ወደ አሜሪካ እና አውሮፓ ሀገራት ለማጓጓዝ ጥቅም ላይ እየዋሉ ይገኛሉ፡፡<br>በአጠቃላይ 98% የሀገሪቱ ሕዝብ እና 93% የገጠር ማህበረሰብ | የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በባህሪው ቶሎ የሚበላሽ ስለሆነ ቶሎ ወደ ገበያ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ለዚህ ደግሞ የመንገድ መሰረተ ልማት መኖር እና አለመኖር ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ በኢትዮጵያ 90% የሚሆነው የትራንስፖርት አገልግሎት በመንገድ መሰረተ ልማት በኩል ነው፡፡ የኢትዮጵያ ዋና ዋና ከተሞች ደረጃውን በጠበቀ አስፋልት መንገድ በመገናኘታቸው እና የገጠር ወረዳዎች እና ቀበሌዎችም ጭምር በመንገድ መረብ የተያያዙ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ የመንገድ መሠረተ ልማት አቅርቦት ዘርፍ የተሻለ ስኬቶች ተመዝግበዋል፡፡<br>በገጠር የኤሌክትሪክ ከበቂ የሃይል አቅርቦት እጥረት የተነሳ አነስተኛም ቢሆኑ በገጠሪቱ የሀገራችን ክፍሎች የሚከናወነው የአትክልትና ፍራፍሬ ኮመርሻል እርሻዎች የኤሌክትሪክ መሰረተ ልማት ችግር ባይኖርባቸዉም በተደጋጋሚ የሀይል መቆራረጥ ስለሚያጋጥማቸው ለከፍተኛ ወጪ እየዳረጋቸው ይገኛል፡፡<br>ለአትክልት እና ለፍራፍሬ ልማት የሚያስፈልጉ ቀዝቃዛ መጋዘኖች፣ ዘመናዊ የገበያ መሠረተ ልማቶች፣ የመስኖ መሠረተ ልማቶች እንደሚፈለገዉ በሀገሪቱ ገጠር አካባቢዎች አልተስፋፉም፡፡ | የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ለማከማቸት እና ለማጓጓዝ የሚያስፈልጉ መሰረተ ልማቶችና አገልግሎት በምርት አካባቢ አለመገኘት፤<br>ለሀገር ውስጥ ገበያ የምርት አቅርቦትና የዋጋ አለመረጋጋት፣<br>የሀገራችን ምርቶች በኤክስፖርት ገበያ ላይ ዋጋቸው ዝቅተኛ መሆን፤ |

| | | |
|---|---|---|
| የኤሌክትሪክ ሀይል አቅርቦት ያገኛሉ፡፡<br><br>በአውሮፓ የጥራት ደረጃ ግሪንሀውስ የሚያመርቱ 40 ተቋማት ከመኖራቸዉ ጋር ተያይዞ አምራቾች በተመጣጣኝ ዋጋ ጥብቅ እርሻ መሰረተ ልማቶችን ማግኘትይችላሉ፡፡ | የቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፍያ የካርጎ ተርሚናል በዘርፉ የሚያስፈልጉትን መሠረተ ልማቶች የተሟሉለት ቢሆንም የሀገሪቷ የጭነት ማጓጓዝ ፍላጐት በከፍተኛ መጠን እያደገ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የሚፈለገውን አገልግሎት መስጠት አልቻለም፡፡ በዚህ መሠረት የተርሚናሉን ተጨማሪ መሠረተ ልማቶች ማስፋፋትና በሌሎች ትላልቅ ከተሞች ተመሳሳይ አቅም ለመፍጠር እየተሰራ ይገኛል(ለምሳሌ የመቀሌና ባህርዳር)፡፡ | |

## 3.4. የሎጂስቲክስ እና ገበያ ልማት

በኢትዮጵያ የአትክልት እና የፍራፍሬ ልማት አስፈላጊ የሆኑትን የገበያ  እና የሎጂስቲክስ   ክፍተት ትንታኔ እንደሚከተለዉ ተተንትኗል፡፡

| የቤንች ማርክ ሀገር ሁኔታ | የኢትዮጵያ ሁኔታ | ክፍተት |
|---|---|---|
| ብራዚል ከፍራፍሬ ምርት ገበያ በዓመት እስከ 5.8 ቢልዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ የምታገኝ ሲሆን ዋነኞቹ የንግድ መዳረሻ ሀገሮች አሜሪካ፣ አርጀንቲና ቻይና፣ ጀርመን፣ ኒዘርላንድ፣ ጃፓን እና ቺሊ ናቸው፡፡ ብራዚል 80% የአለምን የብርቱካን ጁስ አቅርቦት የምትሸፍን ሲሆን 98% የሚሆነው የብርቱካን ምርቷን ኤክስፖርት ታደርጋለች፡፡ የብራዚል 68.04% የሚሆነው የፍራፍሬ ምርት ለአውሮፓ ገበያ ይቀርባል፡፡ የአውሮፓን የጥራት ደረጃ ያሚላ እና እሴት የተጨመረበት ምርት ኤክስፖርት ስለሚደረግ በገበያ ላይ ተወዳዳሪ እና ከፍተኛ ዋጋ አላቸው፡፡ የብራዚል የአትክልት እና የፍራፍሬ ገበያ በሀገር ውስጥ እና በኤክስፖርት ደረጃ ሲታይ ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ያለ ዘርፍ ነዉ፡፡ | በኢትጵያ የሚመረቱ የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርቶች ለሀገር ዉስጥ እና ለኤክስፖርት ገበያ ሲቀርቡ የአቅርቦት ሰንሰለታቸዉም ረጅም እና ብዙ ተዋኒያኖች የሚሳተፉባቸዉ ናቸዉ፡፡ በደላላ (brokers) ተጽእኖ ስር የወደቀ የዋጋ ተመን ያለ ሲሆን ይህም አምራቾችን እና ተጠቃሚዎችን የሚጎዳ ሆኖ ይስተዋላል ፡፡ በተጨማሪም ምርቶቹ የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ የማያሚሉ ስለሆኑ ኤክስፖርት ሲደረጉ ሳይሸጡ ይባክናሉ፣ ገዢ ያጣሉ ወይም አነስተኛ ዋጋ ይኖራቸዋል፡፡ | በኢትዮጵያ ገበያ ተኮር የሆነ ምርት የማምረት ተግባር የዳበረ አለመሆን፤ ወቅታዊ የሆነ የገበያ መረጃ አቅርቦት ስርአት በተሟላ መልኩ አለመዘርጋት፤  ምርቱ ጥራቱን ጠብቆ እንዲመረት እና በገበያ የተሸለ ዋጋ እነዲያወጣ በቂ የባለሙያ ክትትል እና ድጋፍ አይደረግም፤ እና  የምርት መጠን፣ ዓይነትና ምርታማነት እጅግ አነስተኛ ስለሆነ የገበያ አቅርቦቱ ቀጣይነት የለውም፡፡ |
| በብራዚል በ2013 እ.አ. በተደረገው ጥናት 30% የፍራፍሬ ምርት እና የ35% የአትክልት ምርት ለብክነት የሚዳረግ ሲሆን ይህም በዋናነት ከማጓጓዣ እና ከአያያዝ ጉድለት ጋር ተያይዘዉ የተከሰቱ ናቸዉ፡፡ ባለፉት 10 ዓመታት ሀገሪቷ የአትክልት እና የፍራፍሬ ማጓጓዝ አቅሟን ከሁለት እጥፍ በላይ አሳድጋለች፡፡ ይህ እድገት የተገኘዉ  የወደብ አገልግሎት፣ የጉምሩክ ክሊራንስ፣ እና የመጓጓዣ ዘዴዎችን በማዘመን ረገድ የተሳኩ ሥራዎችን ስለተሰራ ነዉ፡፡ በሀገሪቷ 60% የአትክልት ምርት የቅዝቃዜ መጠበቂያ መሰረተ ልማቶች | በኢትዮጵያ የአትክልት ምርት ተመርቶ እስከ ተጠቃሚዎች ድረስ ባለው ሁኔታ የ25-35% ብክነት ያጋጥማል፡፡ አጠቃላይ የሀገሪቷ የምርት መጠን ትንሽም ሆኖ ከዚህም የብክነት መጠኑ ከፍ ያለበት ምክንያትም ምርቱ ከተመረተ በኋላ የማሸግ እና የማከማቸት ሥሪዎች በአግባቡ ስለማይሰሩ እና በሚፈለገው ጊዜ ተጓጉዞ ተጠቃሚዎች ጋር ስለማይደርስ ነው፡፡ ከኢትዮጵያ ኤክስፖርት እየተደረጉ ያሉት የአትክልት እና | የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርቶች  እንዳይበላሹ ተገቢውን የማሸግ አገልግሎት፣ የቅዝቃዜ ሰንሰለቱን ለመጠበቅናና ለምርቱ ባሕሪ የሚመች የማከማቻ መጋዘኖችን ማዘጋጀት ላይ በኢትዮጵያ የጎላ ክፍተት ይታያል |

| | | |
|---|---|---|
| እና ሎጀስቲክስ የተሟሉላቸው ስለሆነ ምርቶቹ ጥራታቸውን ጠብቀው ወደ ሚፈለገው ቦታ መድረስ ይችላሉ፡፡<br>የብራዚል ኢኮኖሚ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የሎጀስቲክስ ፍላጎትም በከፍተኛ መጠን ማደግ ችሏል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሀገሪቱ የአየር የካርጎ ትራንስፖርት በየአመቱ በ10.13% ያድጋል፡፡ የተቀናጀ የሎጀስቲክስ አገልግሎት ለመስጠት መንግሥት ተከታታይ የለውጥ ሥራዎች በመስራት ሊጠቀስ የሚችል የለዉጥ ዉጤት በዘርፉ አገኝቶአል፡፡ | የፍራፍሬ ምርቶች በቂ የማጓጓዣ መኪና እና ቀዝቃዛ ኮንተይነር ስለሌላቸዉ ጥራቱን እና መጠኑን ጠብቆ ወደሚፈለግበት ቦታ አይደርሱም ፤ ቢደርሱም ለማጓጓዝ የሚያስፈልገው ገንዘብ በጣም ከፍተኛ ስለሆነ የመሸጫ ዋጋቸዉ የናረ ነው፡፡ | |

## 3.5. የግል ባለሀብቶች ተሳትፎ

በአትክልት እና በፍራፍሬ ልማት የግል የአርሶ አደሩን የማምረት ስርአት ማዘመንና በዘርፉ የሰለጠኑ ወጣት አምራቾችንና የመንግስት የልማት ተቋማትና የግል ባለሀብቶች ተሳትፎ ወሳኝ ነዉ፡፡በኢትዮጵያ በዚህ ዘርፍ ያለዉን ክፍተት በሚከተለዉ ሠንጠረዥ ተተንትነዋል፡፡

| የቤንች ማርክ ሀገር ሁኔታ | የኢትዮጵያ ሁኔታ | ክፍተት |
|---|---|---|
| በብራዚል በአትክልት እና በፍራፍሬ ልማት ዘርፍ የባለሀብቶች ተሳትፎ በጣም ትልቅ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሀገሪቷ ኤክስፖርት ከምታደርጋቸው 70 ከመቶ ማንጎ እና 60 ከመቶ ወይን ከግል ባለሀብቶች እና ከአነስተኛ ማሳ አምራች ገበሬዎች የሚሰበሰቡ ምርቶች ናቸዉ፡፡<br>በሀገሪቷ 7 ትላልቅ የግል የአትክልት ዘር አቅራቢ ድርጅቶች ያሉ ሲሆን እነሱም የየራሳቸውን የዘር ማባዣ ማዕከል በመጠቀም ለሁሉም የብራዚል ስነ ምህዳር የሚመች ዘር ያመርታሉ፡፡<br>ዩኒቬጅ (UNIVEG) በብራዚል የአትክልት እና የፍራፍሬ የገበያ ስርአቱ እንዲሳለጥ ትልቅ ሚና እየተጫወተ የሚገኙ ሲሆን ቀዝቃዛ መኪናዎችን እና ጥራት ያለው የማሸግ አገልግሎቶችን በማቅረብ የሀገሪቱ ምርቶች ጥራታቸዉን ጠብቀዉ ወደ ሚፈለገው ገበያ እንዲጓጓዙ ረድቷል፡፡<br>የአውሮፓ ትላልቅ የሎጀስቲክስ አቅራቢ ኩባንያዎች በሀገሪቱ ስለሚንቀሳቀሱ ምርቶቹን ተወዳዳሪ በሆነ ዋጋ እና ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ለሀገር ውስጥ እና ለኤክስፖርት ገበያ ማቅረብ ተችሏል፡፡<br>የግሉ ዘርፍ በብራዚል ለአትክልት እና ለፍራፍሬ ግብይት የሚረዱ ሱፐርማርኬት እና ሌሎችንም የገበያ ማዕከላትን ከመገንባት በተጨማሪ የሀገር ውስጥ እና የኤክስፖርት ንግዱ እንዲጠናከር የጎላ ሚና ይጫወታሉ፡፡ | በ2005 ዓ.ም. 36 የግል ኮሜርሽያል እርሻዎች 11768.3 ሄክታር መሬት በማልማት የፍራፍሬ እና የአትክልት ማምረት ዘርፍ ላይ ተሳትፎ ነበራቸዉ፡፡ በኢትዮጵያ በአትክልት እና ፍራፍሬ ልማት የተደራጁ ወጣቶች እና የሀገር በቀል ባለሀብቶች ተሳትፎ አይታይም፡፡ በዘርፉ ከተሰማሩት የግል ባለሀብቶችም ደግሞ ሲታይ ሀገር በቀል የሆኑት ተሳትፎአቸው እጅግ አናሳ ነዉ፡፡<br>በዘርፉ ተሰማርተዉ ያሉትም የግል ባለሀብቶች አትክልት እና ፈራፍሬ በማምረት (Production side) ላይ የተሰማሩ ሲሆን ቀጥራቸዉ በጣም ትንሽ የሆኑት የግል ባለሀብቶች ብቻ በፍራፍሬ እና በአትክልት የማቀነባበር ሥራ ላይ ተሰማርተዉ ይገኛሉ፡፡ በሀገር ዉስጥ ገበያ ላይ የሚገኙ በኢንዱስትሪ የተቀነባበሩ የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርቶች አብዛኞዎቹ ኢምፖርት የተደረጉ ናቸዉ፡፡ | ለዘርፉ የግል ባለሀብቶች ተሳትፎ አናሳ መሆን በዋናነት የሚጠቀሱ ምክንያቶች የካፒታል (የብድር አቅርቦት)፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም አነስተኛ መሆን፣ ለማምረቻ እና ለማሸጊያ የመሳሰሉት የመሠረተ ልማቶች አቅርቦት በሚፈለገዉ መጠን አለመሟላት ናቸው፡፡ |

## 3.6. የጥራት እና ደረጃ ሁኔታ

ለአትክልት እና ለፍራፍሬ ገበያ ጥራት ያለዉ ምርት ማቅረብ የሀገራትን ተወዳዳሪነት የሚጨምር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ በዘርፉ በጥራት በኩል የሚታየዉን ክፍተት እንደሚከተለዉ ተዳሶአል፡፡

| የቤንች ማርክ ሀገር ሁኔታ | የኢትዮጵያ ሁኔታ | ክፍተት |
|---|---|---|
| በብራዚል ጥራት ላይ ትኩረት ተደርጎ ስለሚትሰራ በፍራፍሬ ምርት የአዉሮፓን እና የመካከለኛ ምስራቅን ገበያዎችን መቀላቀል ችላዋል፡፡<br>ሁሉም ኤክስፖርት የሚደረጉ የፍራፍሬ ምርቶቿ በዘርፉ የተቀመጠውን የዓለም የመልካም እርሻ (Global GAP) እና ISO ደረጃዎች የሚያሟሉ ስለሆነ በቀላሉ ምርቶቿ በአውሮፓ፣ በአሜሪካ እና በመካከለኛው ምሥራቅ ገበያ ቀርበው ተወዳዳሪ መሆን ችለዋል፡፡<br>በሀገሪቱ BRC Global Food የሚባል የምግብ ደህንነት እና የጥራት ደረጃዎችን በማዉጣት ሁሉም የሀገሪቱ የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርት እና ድህረ ምርት አያያዝ ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን እየሰሩበት ይገኛሉ፡፡<br>በብራዚል የተሻለ ጥራት ያለው ዝርያ ለመጠቀም ዝርያ ማሻሻል እና የዘር ወይም ችግኝ አቅርቦት ላይ በምርምር የታገዘ ሥራ እና ከፍተኛ ጥንቃቄዎች ይወሰዳሉ፡፡ | በኮሜርሻል የግል ባለሀብቶች እርሻ ላይ የሚመረቱት የGlobal-GAP የጥራት መስፈርትን ስለሚያሟሉ ምርቶቻቸው ወደ አውሮፓ ገበያ እና ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ገበያ እየተላኩ ናቸው፡፡<br>በኢትዮጵያ የሚመረቱ በተለይም ከግል አምራች ገበሬዎች የሚሰበሰቡ የአትክልት እና ፍራፍሬ ምርቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቀመጡትን Global-GAP እና ISO መስፈርቶች የማያሟሉ ስለሆነ ለኤክስፖርት ተወዳዳሪ ሊሆኑ ስለማይችሉ አብዛኛው ምርቶቻቸዉ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ይውላል፡፡<br>የኢትዮጵያ አበባ አትክልትና ፍራፍሬ አምራች ላኪዎች ማኅበር ባወጣዉ የአሰራር ኮድ መሰረት በ2005 ብቻ 55 እርሻዎች ለነሃስ፣ 12 እርሻዎች ለብር፣ 3 እርሻዎች ለወርቅ ደረጃዎች ብቁ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ | መልካም እርሻን (Good Agricultural Practices/GAP) ተግባራዊ በማድረግ የምርት መጠን ብቻ ሳይሆን የምርት ጥራትን በማሻሻል ዙርያ ሰፊ ክፍተት አለ፡፡<br>በሀገር ደረጃ የጥራት መስፈርቶችን ከማዉጣት ባሻገር ተግባራዊነቱን ክትትል በጣም ደካማ ነው፡፡ |

# ክፍል አራት

## 4. የዘርፉ ተግዳሮቶች እና መልካም አጋጣሚዎች

በአትክልት እና የፍራፍሬ ምርት እና ግብይት ኢትዮጵያ ካላት እምቅ አቅም አኳያ እንደሚፈለገዉ አለማደጉ በቀጣይ በዘርፉ ሊሰሩ በታቀዱት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራሉ፡ ፡ ለዚህም በምክንያትነት የሚጠቀሱ ኢኮኖሚያዊ፣ ተቋማዊ፣ ማህበራዊ ምክንያቶች ሲሆኑ በሚጥሉት ሠንጠረዥች የምርምሩና የልማቱ ተግዳሮቶች እና መልካም አጋጣሚዎች በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡

## 4.1. በሰው ሃይል ልማት

በዘመናዊ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ዘርፍ የሰለጠነ ሰው ኃይል በከፍተኛ ደረጃ ማፍራት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ የሰለጠነ የሰዉ ሀይል ከመፍጠር አንጻር ያሉትን ተግዳሮቶች እና መልካም አጋጣሚዎች እንደሚከተለዉ ቀርቦአል፡፡

| ተግዳሮቶች (challenges) | መልካም ዕድሎች (Opportunities) |
|---|---|
| በሆርቲካልቸር የትምህርት መስክ አሁን በብዛት በተከፈቱት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በመስራት በርካታ ምሩቃን ማፍራት ይቻላል፡፡ ከዩኒቨርሲቲ ተመርቀዉ የሚወጡ ባለሙያዎች ብዛት ሲታሰብ በተግባር የተደገፈ ስልጠና በመስጠት ተመራቂዎች በቂ የተግባር ልምድ ወይም ክህሎት ማፍራት እንዲችሉ ማድረግ ያለው ያልተጠናከረው መሰረተ ልማት በዘርፉ ተግዳሮት ነዉ፡፡<br>በመስኩና በሌላ የትምህርት መስክ ከTVT's እና ኮሌጆች የሚመረቁትን በርካታ ወጣቶች በማደራጀት በሁሉም አካባቢዎች በአጭር ጊዜ ወደ ስራ ማሰማራትና ውጤታማ ማድረግ መቻል ተግዳሮታችን ነዉ፡፡<br>የአነስተኛ ማሳ አርሶአደሮችን በዘርፉ በማሰማራት የአለም ዓቀፍ ጥራትን የጠበቀ ምርት ማምረት እንዲችሉ መስራት መቻል ሌላኛዉ ተግዳሮት ነዉ፡፡ | በሀገር ውስጥ ከ32 በላይ የሚሆኑ ዩኒቨርስቲዎች በመኖራቸው በቀላሉ ወጣቶችን በአትክልትና ፍራፍሬ ማምረት ሙያ ማሰልጠን ይቻላል፡፡ በአሁኑ ወቅትም 13 የተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች በሆርቲካልቸር ሳይንስ ዘርፍ በመጀመሪያ ዲግሪ እና ከዚያ በላይ በሆነ ሥልጠና እየሰጡ መሆናቸዉ ለዘርፉ እድገት መልካም አጋጣሚ ነዉ፡፡<br>የግብርና የቴክኒክ እና ሙያ ኮሌጆች በመላው ሀገሪቱ የተቋቋሙ ስለሆነ በመለስተኛ ማስተካከያ በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የአጭር ጊዜ ሥልጠናዎችን ለባለሙያዎች ሊሰጡ የሚችሉ መሆናቸዉ በዘርፉ በመካከለኛ ደረጃ ለሚያስፈልገዉ የሰለጠነ የሰዉ ሀይል ለማፍራት መልካም ዕድል ያመቻቸ ነዉ፡፡<br>በሁሉም የሀገራችን ቀበሌዎች የገበሬዎች ማሰልጠኛ ማዕከላት ተገንብተው ያሉ መሆናቸዉ እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም በተግባር የተደገፈ በአትክልት እና በፍራፍሬ ልማት ስልጠና ለአርሶ አደሩ በስፋት መስጠት ያስችላል፡፡ በተለይ ደግሞ መጭዉ አምራች ሀይል ወጣትና የሳይንስ መሰረታዊ ዕዉቀት ያላቸዉ መሆኑ ለዘርፉ ዕድገት መልካም ዕድል ነዉ፡፡<br>እንዲሁም በሀገሪቱ ትላልቅ ከተሞች ዙሪያ አትክልት የማምረት ተሞክሮ ያላቸዉ አርሶአደሮች በብዛት መኖራቸዉ እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም የእነርሱን የዳበረ ልምድ ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር የአምራቹን ቁጥር በማሳደግ ማዘመን ይቻላል፡፡ |

## 4.2. የቴክኖሎጂ ደረጃ

ቴክኖሎጂ ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት እድገት የሚጫወተዉ ድርሻ ትልቅ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በዘርፉ ያሉትን ተግዳሮቶች እና መልካም አጋጣሚዎች በመለየት መስራት በቀላሉ የሚታይ ጉዳይ አይደለም፡፡ ከዚህም አንጻር በዘርፉ ያለዉን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ተግዳሮቶች እና መልካም አጋጣሚዎችን እንደሚከተለዉ ተብራርተዋል፡፡

| ተግዳሮቶች (challenges) | መልካም ዕድሎች (Opportunities) |
|---|---|
| በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ዘርፍ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና አቅርቦት አቅም ዝቅተኛ መሆን የኤክስፖርት ጥራት የሚያሟሉ አዳዲስ ዝርያዎች ማግኘት መቻል በቀዳሚነት ሊነሳ የሚችል የዘርፉ ተግዳሮት ነዉ፡፡<br>የድህረ ምርት ብክነት መቀነስ የሚያስችሉ በዘርፉ ያሉትን ቴክኖሎጂዎችን ካሉበት ቦታ በማምጣት እና በማላማድ መጠቀም መቻል የግድ ነዉ፡፡ በሰፊዉ የሚታየውን የድህረ ምርት አያያዝ ድክመት በማሻሻል በብዛት እና በጥራት ለአውሮፓ ገበያ ማቅረብ ከአጭር ጊዜ አኳያ ትልቅ ተግዳሮት ነው፡፡<br>በኢትዮጵያ የሚመረቱ ለዘርፉ እድገት የሚያስፈልጉ ቴክኖሎጂዎች ማለትም የግሪንሃውስና የመስኖ ቴክኖሎጂዎች የግብአት አናሳ ስለሆነ በሀገር ውስጥ በማምረት አቅርቦትን ማሳደግ እና ዋጋው በሚፈለገው ደረጃ ተመጣጣኝ ማድረግ መቻል ተግዳሮታችን ነው፡፡<br>አብዛኞቹ የአትክልትና ፍራፍሬ ቴክኖሎጂዎች ከውጭ ሀገር የሚገኙ ስለሆነ ሙሉ አቅማቸዉን አሟጦ ለመጠቀም አቅም መገንባት ሊያጋጥም የሚችል ተግዳሮት መሆኑ ታዉቆ በዚህ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት መቻልን ይጠይቃል፡፡ | በሀገራችን የምርምር ተቋማት እና ዩኒቨርስቲዎች የተሻሻሉ ዝርያዎችን እና ቴክኖሎጂዎችን የማውጣት ተልዕኮ ይዘው የተመሰረቱ በየስነምህዳሩ ስለሚገኙ እነሱን በማጠናከር እና ተልዕኮአቸዉን በአግባቡ እንዲወጡ በማድረግ ርገ የዘርፉን ችግር ለመፍታት የእነሱ መኖር መልካም አጋጣሚ ነዉ፡፡<br>በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚያስፈልጉ ቴክኖሎጂዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ በግልጽ የሚታወቁ እና የሚገኙ ስለሆነ ከሀገራችን ሁኔታ ጋር ማላመድ ፣ መቅዳት እና መጠቀም መቻሉ ቴክኖሎጂ ደረጃን ለማሻሻል ለሚደረገዉ ጥረት መልካም ዕድል ነው፡፡<br>የአነስተኛና መካከለኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት እና የብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን መኖር ቴክኖሎጂዎችን የማፍለቅ እና የማላመድ አቅም ግንባታ ጋር የግሪንሀውስ፣ የመስኖ፣ የማቀዝቀዝ እና የማጓጓዣ ግብአቶችን ሀገር ውስጥ ማምረት አቅም እየተፈጠረ ስለሚመጣ ቴክኖሎጂን በሀገር ዉስጥ ለማላመድና ለማባዛት የሚደረገዉን ጥረት የሚያግዝ መልካም ዕድል በመሆኑ መጠቀም ይቻላል፡፡ |

## 4.3. የመሠረተ ልማት አቅርቦት

ለአትክልት እና ለፍራፍሬ ልማት የመሰረተ ልማት አቅርቦት ወሳኝ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የዘርፉን ልማት ለማዘመን እና ተወዳዳሪ ለማድረግ በዘርፉ ያሉትን ተግዳሮቶች እና መልካም አጋጣሚዎች መለየት አስፈላጊ ነዉ፡፡ በዚሁ መሰረት በኢትዮጵያ የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርት የሚያግዙ የመሠረተ ልማት ተግዳሮቶች እና መልካም አጋጣሚዎች እንደሚከተላዉ ተዘርዝረዋል፡፡

| ተግዳሮቶች (challenges) | መልካም ዕድሎች (Opportunities) |
|---|---|
| የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ቶሎ የመበላሸት ባህርይ ስላለዉ ወደ ገበያ መቅረብ ስለሚኖርበት የመንገድ መሰረተ ልማት አሁን ካለበት በላይ በሀገራችን ማስፋፋት ይጠይቃል፡፡ ለሆርቲካልቸር ልማት የሚፈለጉ መሰረተ ልማቶች የኤሌክትሪክ ሀይል ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የሀይል መሰረተ ልማቶችን አሁን በተጀመረዉ አቅጣጫ በከፍተኛ ደረጃ አቅም በፈቀደ መጠን ማስፋፋትን የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑ አይቀርም፡፡ በዘርፉ ያሉትን የመሰረተ ልማት ቴክኖሎጂዎች (hydroponics, airoponics and others) የመጠቀም አቅማችን እየዳበረ በሄደ ቁጥር በዘርፉ የሀይል ፍላጎት በከፍተኛ መጠን እየጨመረ መሄዱ የማይቀር ጉዳይ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ይህን የዘርፉን ተግዳሮት መፍታት መቻል ያስፈልጋል፡፡<br>የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ለማከማቸት እና የቅዝቃዜ መጠኑን ጠብቆ ለማቆየት የቀዝቃዛ መጋዘን መሰረተ ልማት | በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ዋና ዋና ከተሞች ደረጃውን በጠበቀ አስፋልት መንገድ በመገናኘታቸው እና የገጠር ወረዳዎች እና ቀበሌዎችም ጭምር በመንገድ መረብ የተያያዙ ከመሆናቸው አንፃር በቀላሉ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ወደ ገበያ መዉሰድ ስለሚቻል ለዘርፉ እድገት መልካም አጋጣሚ ፈጥሮአል፡፡<br>በአሁኑ ጊዜ ሀገሪቱ የሀይል አቅርቦትን ለማሻሻል ከፍተኛ የሆነ የመሠረተ ልማት ማስፋፋት ሥራዎች እየተሰሩ ሲሆን ከነዚህም ሥራዎች በዋናነት የሚጠቀሱት የኢትዮጵያ ህዳሴ ኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድብ፣ የግቤ 3 የሀይል ማመንጫ ግድብ፣ የንፋስ እና የጂኦተርማል ሀይል ማመንጫ ግንባታዎች እና የሀይል ማስተላለፍያ መሠረተ ልማት ግንባታዎች ናቸው፡፡ የእነዚህ መሠረተ ልማት ግንባታዎች እየተጠናቀቀ አዲስ የሀይል አቅርቦት እንዲኖር ሲደረግ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ዘርፍም ከዉጤቱ ተቋዳሽ የሚሆንበት መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል፡፡<br>የቀዝቃዛ መጋዘን መሠረተ ልማት ባንዳንድ የግል ባለሀብቶች እና በህብረት ሥራ ማህበራት ተገንብተዉ የሚገኙ ሲሆን ይህኑ መሠረተ ልማት በጋራ የሚጠቀሙበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች (ለምሳሌ፡ በአዳሚ ቱሉ ዩኒዮን) አምራች ገበሬዎች በማህበራት በመደራጀት የጋራ የማከማቻ መጋዘኖችን የመገንባት እና የመጠቀም ጅማሮዎች የሚታዩ ሲሆን ይህን ልምድ ለሌሎች እንዲሰፋ ማድረግ እና እና ይህንን እንደመልካም አጋጣሚ ወስደን ማስፋት ያስፈልጋል፡፡<br>የኢትዮጵያ አየር መንገድ የካርጎ ተርሚናሎችን መሠረተ ልማት በሀገሪቱ ለማስፋፋት የጀመረው ሥራ ለአትክልትና ፍራፍሬ ኤክስፖርት እድገት ትልቅ ድርሻ ያበረክታል፡፡ ሁሉንም የሀገሪቱን ክልሎች እና ሀገራቱን ከአጎራባች ሀገሮች ጋር ለማስተሳሰር ሲባል እየተስፋፋ ያለው የባቡር መሠረተ ልማት በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ትልቅ ድርሻ ሊያበረክት የሚችል መልካም አጋጣሚ ነዉ፡፡ በሁሉም አቅጣጫ ሀገሪቷ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር የመንገድ መሠረተ ልማቶች ተገዘርግተዋል፣ ደረጃቸውም አድጓል፡፡ የዚህ መንገድ |

| | |
|---|---|
| መኖር ለዘርፉ እድገት ወሳኝ ነው፡፡ በኢትዮጵያ በብዛት በአርሶ አደር ማሳ የሚመረተውን ምርት አይነት መቀየርና በአካባቢው የማከማቻና ቀዝቃዛ መጋዘን መሰረተ ልማት በህብረት ስራ ማህበራት እና በግል ባለሀብቶች ተሳትፎ እንዲስፋፋ ማድረግ መቻል ሊያጋጥመን የሚችል ተግዳሮት ነው፡፡ | መሠረተ ልማት መስፋፋት ለወደፊት የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችንና ግብአቶችን በቀላሉ ከአካባቢው ገበያ ጋር ስለሚያስተሳስር ለዘርፉ ልማት መልካም አጋጣሚን ይፈጥራል፡፡<br>በዘርፉ የሰለጠኑና የተደራጁ ወጣት ባለሙያችም ሆኑ የግሉ ባለሀብቶች በዘር ማባዛት ቢዝነስ፣ በግሪንሃዉስ፣ በሃይድሮፖኒክስና ኤሮፖኒክስ ማምረቻ ዘዴ የመሳተፍ ዕድላቸዉ ሰፊ ስለሆነ የግብርና ምርምር ማዕከላት ያለው ተሞክሮ እንደ መልካም ዕድሎች ናቸዉ፡፡ |

## 4.4. የሎጀስቲክስ እና ገበያ ልማት

የሎጀስቲክስ አገልግሎት የአትክልት እና የፍራፍሬ የምርት ዋጋ እንዲንር ከማድረጉም በተጨማሪ የምርቶቹ ጥራት እንዲጓደል ከፍተኛ ተጽዕኖ በማሳደር ይታወቃል፡፡ ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያ የሎጂስቲክስ እና ገበያ ሁኔታ ተግዳሮቶች እና መልካም አጋጣሚዎች እንደሚከተለዉ ተብራርቶአል፡፡

| ተግዳሮቶች (challenges) | መልካም ዕድሎች (Opportunities) |
|---|---|
| በዓለም ገበያ በአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ግብይት ብቁና ተወዳዳሪ ምርት ማምረት አለመቻል የሚታይና ከፊታችን የተጋረጠ ችግር ነው፡፡ በዘርፉ ያለዉን የገበያ ተወዳዳሪነት ለማሳደግ በዓለም አቀፍ መስፈርቶች መሰረት ጥራቱን የጠበቀ ምርት ማምረትን፣ በሀገር ዉስጥ በስፋት የሚታየዉን ረጅም እና ውስብስብ የገበያ ሰንሰለት ማሳጠር እና በቂ የገበያ መረጃ ስርዓት መገንባት ተግዳሮቶችን መፍታት መቻል ይጠይቃል፡፡<br>በመካከለኛዉ ምስራቅ እና ከፍተኛ የጥራት ደረጃ በሚጠይቀዉ የአዉሮፓ ያለዉ የአትክልትና ፍራፍሬ ገበያ በጣም የዳበረ እና ብዙ ተወዳዳሪዎች ያሉበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ገበያዉን ሰብሮ የመግባት እና ገበያ ዉስጥ መቆየት መቻል በዋናነት ሊጠቀስ የሚችል የዘርፉ ተግዳሮት ነዉ ፡፡ | መንግስት ዘርፉን ለማሳደግ ያለው አቋም እና ተግባር ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ለሚሳተፉ ልዩ ማበረታቻ መዘርጋቱ አምራቾች በዘርፉ በአለም አቀፍ ደረጃ ብቁ ተወዳዳሪ እንድትሆን መልካም አጋጣሚ ይፈጥርላታል፡፡<br>በዓለም አቀፍ ደረጃ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ጥራት መለኪያዎች በግልጽ የተቀመጡ መሆናቸዉ እነዚህኑ በመውሰድ እና በሁሉም ባለድርሻዎች ዘንድ ግንዛቤን በመፍጠር መተግበር መቻሉ እንደመልካም አጋጣሚ ሊጠቀስ ይችላል፡፡<br>ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ምቹ የሆኑ የስነምህዳር ያለባት ሀገር ከመሆኗ ጋር ተያይዞ በሁሉም የምርት ወቅቶች በማምረት በዓለም አቀፍ ገበያ እጥረት በሚፈጠርበት ወቅት ምርት ማቅረብ መቻሏ በዘርፉ ሊጠቀስ የሚችል መልካም ዕድል ነዉ(Seasonal difference advantage)፡፡ በተለይ በአዉሮፓ የአትክልት እና የፍራፍሬ አምራቾች ካለባቸዉ የአየር ሁኔታ አስገዳጅነት ዓመቱን ሙሉ በሁሉም አቅማቸዉ ስለማያመርቱ የሚፈጠረዉን የገበያ ክፍተት ኢትዮጵያ እንደ መልካም አጋጣሚ ለመጠቀም ከዚህ በፊት ሀገሪቷ ኤክስፖርት ስታደርግ የነበረዉን ልምዷን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ምርቶችን በስፋት መላክ ትችላለች፡፡ |
| ለአለም ኤክስፖርት ገበያ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርትን ለማቅረብ የሚረዳ በቂ ሎጂስቲክስ አቅርቦትን ይጠይቃል፡፡ በኢትዮጵያ የአትክልት ምርት ተመርቶ እስከ ተጠቃሚዎች ድረስ ባለው ሰንሰለት ከፍተኛ ብክነት | ሰፊ የኤሌክትሪክ፣ የመንገድ፣ የባቡር፣ የመርከብ እና የቴሌኮም መሰረተ ልማቶች በሀገሪቷ እየተስፋፉ ስለሆነ ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊያጋጥም የሚችል የሎጀስቲክስ አገልግሎቶችን መፍታት ያስችላል፡፡ ለአትክልትና ፍራፍሬ ከምርት እስከ ኤክስፖርት |

| | |
|---|---|
| ያጋጥማል፡፡ ይህ ብክነት ሊጨምር የሚችልባቸው ምክንያቶች ውስጥ ምርቱ በሚመረትበት ቅርብ አካባቢ የማሸግ እና የማከማቸት ሥራዎች በአግባቡ ስለማይሰሩና በሚፈለገው ጊዜ ተጓጉዞ ተጠቃሚዎች ጋር ስለማይደርስ ነው፡፡<br><br>ጥራትን በመቀነስ እና አነስተኛ ምርት ለገበያ እንድናቀርብ ስለሚያደርግ በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶት መስራት መቻልን ይጠይቃል፡፡ እንደዚሁም ኤክስፖርት የሚደረጉ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በቂ የማጓጓዣ እና ቀዝቃዛ ኮንተይነር እጥረት የሚያጋጥምበት ስለሆነ የሚፈለገዉን ጥራት እና መጠን ጠብቆ ወደሚፈለግበት ቦታ ስለማይደርስ ይህን ተግዳሮት ትኩረት ሰጥቶ መፍታት መቻል ይጠይቃል፡፡<br><br>የሎጂስቲክስ አገልግሎትን በማሻሻልና ተገቢውን የማሸግ ሥራ መስራትን፣ የቅዝቃዜ ሰንሰለቱን መጠበቅን እና ለምርቱ ባሕሪ የሚመች የማከማቻ መጋዘኖችን በማዘጋጀት ደረጃዉን የጠበቀ ምርት ለኤክስፖርት ገበያ ለማቅረብ ብቃቱን መፍጠርና ዘላቂ ማድረግ መቻል ደግሞ ሌላኛዉ የዘርፉ ተግዳሮት ነዉ፡፡ | ላለዉ የሎጂስቲክስ ጥያቄ በአበባ ኤክስፖርት እና የተወሰኑ የአትክልት እና የፍራፍሬ ኤክስፖርት ለማብቃት የተጀመሩትን ዘመናዊ ትራንስፖረት እና የተሟላ የካርጎ አገልግሎት ግንባታ፣ በየአካባቢዉ ሊፈጠር የሚችለዉ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በኢትዮጵያ አየር መንገድ ለማጓጓዝ ያለውን የአለም አቀፍ የአይሮፕላን ማረፊያ ጣቢያ ግንባታ ለኤክስፖርት እድገት እንደ መልካም አጋጣሚ እንደሆነ የሚቆጠር ነዉ፡፡ |

## 4.5. የግል ባለሀብቶች ተሳትፎ

በኢትዮጵያ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ዘርፍ የግል ባለሀብቶች ተሳትፎ በሁሉም መልክ መልካም ሊባል የሚችል ጅማሮ ያለዉ ሲሆን ከዚህ በበለጠ ተሳትፎአቸዉን ለማጠናከር ግን በዘርፉ የሚታየዉን ተግዳሮቶች መፍታት እና መልካም አጋጣሚዎች አሟጦ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

| ተግዳሮቶች (challenges) | መልካም ዕድሎች (Opportunities) |
| --- | --- |
| የግሉ ዘርፍ በአትክልትና ፍራፍሬ ግብይት በተጨማሪ የማቀነባበርያ፣ የመሸጫ ማዕከላትና መጋዘኖችን በመገንባት ዘርፉን እንዲያጠናክሩና የጎላ ሚና እንዲጫወቱ ዘርፉን ሳቢና አዋጭ ማድረግ ሊያጋጥም የሚችል ተግዳሮት ነው፡፡<br>ከከፍተኛ ተቋማት የሚመረቁ በዘርፍ የተማሩ ወጣቶችን በማደራጀት እና አስፈላጊዉን ድጋፍ በመስጠት ዘርፉ ከሚፈጥረዉ እድል ተጠቃሚ ማድረግ ለማድረግ በዘርፉ የሚታይ የቴክኖሎጂና ፋይናንስ አቅርቦት ተግዳሮት ነዉ፡፡<br>ባለሀብቶችን ወደ ሌላ ዘርፍ በፍጥነት ትርፍ ወደሚያገኙበት እና አነስተኛ ስጋት (Risk) ወዳለበት ኢንቨስትመንት የሚሳቡትን በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ዘርፉን በአግባቡ ማስተዋወቅ እና የድጋፍ ፓኬጆችን አዘጋጅቶ መተግበር መቻልና ከሌሎች ተወዳዳሪ ዘርፎች ሊያጋጥም የሚችል ተግዳሮት መቋቋም የግድ ነዉ፡፡<br>የግሉን ባለሀብቶች ተሳትፎን የሚቀንስ የመልካም አስተዳደር ችግር ማቃለልና ልማታዊ ባለሀብቶችን ለይቶ አብሮ መስራት መቻል ሊጠቀስ የሚገባዉ የዘርፉ ተግዳሮት ነዉ፡፡ | ኢትዮጵያ ከዓለማችን ፈጣን እድገት እያስመዘገቡ ካሉት ታዳጊ ሀገራት ውስጥ አንዷ ከመሆኗ ጋር ተያይዞ ብዙ የውጭ ሀገር የግል ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ በሀገሪቱ በሚመረተዉ ምርት እና ኤክስፖርት ላይ የግል ባላሀብቱ ተሳትፎ ጨምሮአል፡፡ ይህን እያደገ ያለዉን የባለሀብቶች ተሳትፎ እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ዘርፍ ላይ በብዛት እንዲሳተፉ ማድረግ ይቻላል፡፡<br>የተማሩና በቀላሉ ተደራጅቶ መስራት የሚችል ወጣት ሀይል ወይም በቀላሉ ሊለማ የሚችል ጉልበት በስፋት በሀገራችን እየተፈጠረ መሆኑ ዘርፉን በቀጣይነት ለማሳደግ መልካም ዕድል ነዉ፡፡ ባንኮች እና ማይክሮፋይናንስ ድርጅቶች በገጠር ከተሞች እየተስፋፉ መምጣታቸዉ እንደ መልካም ዕድል በመጠቀም በተደራጁ ወጣቶች ን የፋይናንስ ችግር መፍታት ይችላሉ፡፡<br>ሰፋፊ የሸንኮራ አገዳ ልማት ማዕከላትን በመጠቀም ለኤክስፖርት ገበያ ፈጣንና አዋጭ የሆኑ የተለያዩ ፍራፍሬዎች (ማንጎ፣ብርቱካን፣ መንደሪን፣ፓፓያ፣ ወዘተ) በንፋስ ማገጃነት(wind break) በሚረዳ መልኩ በመትከል በስፋት ማምረት ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያ ዉስጥ ከተቋቋሙት ከእያንዳንዱ የስኳር ፋብሪካዎቹ ጋር ተያይዞ እየለሙ እና መልማት የሚችሉ በሺዎች የሚቆጠር ሄክታር መሬት አስፈላጊዉ የመስኖ እና ሌሎች መሰረተ ልማቶች ተሟልቶላቸዋል፡፡ ይህን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም የፍራፍሬ ምርትን በብዛት በማምረት ለሀገር ዉስጥ እና ለኤክስፖርት ገበያ ለማቅረብ መልካም ዕድል ፈጥሮአል፡፡ |

## 4.5. የጥራት እና ደረጃ ሁኔታ

የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የምርት ጥራት እና ደረጃ ተግዳሮቶች እና መልካም አጋጣሚዎች በመፈተሽ የዘርፉን እድገት አስተማማኝ እና በአለም አቀፍ ገበያ ብቁ ተወዳዳሪ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የምርት ጥራት እና ደረጃ ተግዳሮቶች እና መልካም አጋጣሚዎች እንደሚከተለዉ ተብራርቷል፡፡

| ተግዳሮቶች (challenges) | መልካም ዕድሎች (Opportunities) |
|---|---|
| በተለይ ሁሉም ኤክስፖርት የሚደረጉ የፍራፍሬ ምርቶቿ በዘርፉ የተቀመጠውን የዓለም የመልካም እርሻ (Global GAP) እና ISO ደረጃ የሚያሟሉ ማድረግ ስለሚያስፈልግ ቀላል ሥራ ሊሆን አይችልም፡፡ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ጥራት የተሻለ ጥራት ያለው ዝርያ መጠቀምን ስለሚጠይቅ ዝርያ ማሻሻልና የዘር ወይም የችግኝ አቅርቦት ላይ በምርምር የታገዘ ሥራ መስራት ያስፈልጋል፡፡ ጥራቱን የጠበቀ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ለገበያ በማቅረብ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ጥራት ላይ ትኩረት በማድረግ በመስራት ዘርፉን ከማሳደግ እና ትራንስፎርም ለማድረግ የበርካታ ተቋማት ሚናን አቀናጅቶ መምራት ሊያጋጥም የሚችል ተግዳሮት ነው፡፡<br>ጥራትን የማስጠበቅ ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት በሰለጠነ ባለሙያ በመታገዝ በመስራት በአለም አቀፍ ደረጃ በምግብ አቅርቦት መልካም ሥም ማፍራትን የሚጠይቅ መሆኑ የዘርፉ ተግዳሮት ነው፡፡ | በሀገራችን በሰፋፊ ኮሜርሻል የግል ባለሀብቶች እርሻ ላይ የሚመረቱት የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች የGlobal-GAP እና ሌሎች ተቋማት የጥራት መስፈርትን ስለሚያሟሉ ምርቶቻቸው በቀጥታ ወደ አውሮፓ ገበያ እና ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ገበያ እየላኩ ስለሚገኙ የእነሱን ልምድ ከሀገር ውስጥ በቀላሉ መጠቀም መቻል መልካም አጋጣሚ ነዉ፡፡<br>ያለንን እምቅ አቅም ለመጠቀም የሚያስችሉ የፖሊሲ ማዕቀፎች በተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ፣ ዘላቂ ግብርና እና የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ መኖር፤ የተወሰኑ ደረጃዎችና የጥራት ጉዳዮችን ማስተዳደር የሚችል ሀገራዊ ተቋም መኖር፣ የሰርቲፊኬሽንና አክሬዲቴሽን እና የልኬትና ምዘና ተቋም መኖር፤ በአለም አቀፍ ስታንዳርድ ሰርቲፋይድ የሆኑ የተወሰኑ የመንግስትና የግል ላቦራቶሪዎች መኖር እንደ መልካም መነሻ የሚያገለግሉን ናቸው፡፡<br>ከዚህ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ፣ የሀገራዊ የጥራትና ሰርቲፊኬሽን ድርጅት እና የተስማሚነትና ምዘና ኢንተርፕራይዝ በአዲስ መልክ መደራጀት እንደ መልካም አጋጣሚ ሊወሰድ ይችላል፡፡ የግል ባለሀብቶች የምርት ጥራት ማረጋገጫ የላቦራቶሪ አገልግሎት ውስጥ መግባት መጀመራቸውም ለዚህ መልካም እድል ነው፡፡<br>የኢትዮጵያ አበባ አትክልትና ፍራፍሬ አምራች ላኪዎች ማኅበር የዘርፉን ዘላቂ አመራረት ለማሳደግ የአሰራር ኮድን በማስተዋወቅ ሀገሪቷ ጥራት ያለዉ ምርት ለአለም ገበያ በማቅረብ እና ብቁ ተወዳዳሪ በመሆን ከዘርፉ የተሻለ ጥቅም እንድታገኝ እየሰራ መሆኑ ሌላኛዉ መጠቀስ የሚችል መልካም አጋጣሚ ነዉ፡፡ |

# ክፍል አምስት

## 5. ስትራቴጂያዊ ግቦችና የአፈጻጸም አቅጣጫዎች

ኢትዮጵያ ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ከፍተኛ ዕምቅ አቅም ያላት ሀገር ብትሆንም ከዘርፉ መጠቀም ያለባትን ያህል አልተጠቀመችም፡፡ በዚህ መሰረት በዘርፉ ያለውን አቅም በመለየት መጠቀም እና ሊያጋጥሙ የሚችሉትን ተግዳሮቶች በመለየት እና መፍትሄ ሀሳቦችን በመሻት የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት እድገት አንዱ የቀጣዩ የሀገሪቱ የግብርና እድገት ምንጭ ማድረግ ያስፈልጋል፤ ይቻላልም፡፡ በመሆኑም በሶስተኛዉ የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን መጨረሻ ለዚህ ጥናት ቤንችማርክ ከተደረገችዉ ብራዚል አሁን የደረሰችበት የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት እና ምርታማነት ቁመና በምርት ዓይነት፣ በብዛት፣ በአቅርቦት ቀጣይነት እና በዓለም አቀፍ የገበያ ተወዳዳሪነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሀገሪቷ እንድትደርስ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### *5.1 የአትክልት ልማት እስትራቴጂክ ግቦች እና የአፈፃፀም አቅጣጫዎች*

በኢትዮጵያ የአትክልት ልማት የወደፊቱ የሀገሪቷ የግብርና ፈጣን እድገት ማስቀጠያ ምንጭ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል፡፡ አትክልት ሰፊ ጉልበትን በመጠቀም በአነስተኛ ማሳ ላይ በማምረት ከፍተኛ ገቢ ማስገኘት የሚያስችል ዘርፍ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሰፍ መሬት ባለበት ቆላማ አከባቢዎች ሆነ በሀገራችን ከፍተኛ የመሬት ጥበት እና ሰፊ የሰው ጉልበት ባለበት ደጋማው የሀገራችን ክፍሎች በቀላሉ ሊተገበር ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በከተሞች እና በከተሞች ዙሪያ ለረጅም አመታት የአትክልት ልማት ተሞክሮ እና የዳበረ ክህሎት በመጠቀም እና ዘመናዊ አመራረትን በመከተል ዘርፉ በአጭር ግዜ ዉስጥ ለዉጥ እንዲያመጣ ማድረግ ይቻላል፡፡ የሀገር ዉስጥ የግል ባለሀብቶች እና ወጣቶች በዘርፉ በሰፊው ቢሰማሩ ለኤክስፖርት ገበያ ተወዳዳሪ የሆነ ምርት በማቅረብ ለሀገራቸዉም ሆነ ለራሳቸዉ ከፍትኛ የሆነ ትርፍ ሊያስገኝ እንደሚችል ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ የአነስተኛ ማሳ አምራቾችንና የባለሀብቶችን እርሻ በማስተሳሰር (out growers System) መስራት ከተቻለ በዘርፉ ተጨማሪ አቅም በመፍጠር ተአምር

መስራት ይቻላል፡፡ የአትክልት ልማትን በፍጥነት ለማሳደግ እና ሀገሪቷን ከዘርፉ የተሻለ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚከተሉትን ዋና ዋና ስትራቴጃዊ ግቦች እና የአፈፃፀም አቅጣጫዎችን ማየት ተገቢ ነው፡፡

### *5.1.1. በመካከለኛ እና በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሃይል ማፍራት*

በኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት እና የቴክኒክ እና ሙያ ኮሌጆች በከፍተኛ መጠን መስፋፋት ወጣቶችን በሚፈለጉት ማንኛውም ሙያ በአጭር ጊዜ ለማሰልጠን እንዲቻል አቅም ተፈጥሯል፡፡ ይሁን እንጂ በነዚህ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለአትክልት ልማት ዘርፍ ትኩረት ተሰጥቶ ዘርፉን እራሱን አስችሎ ስርአተ ትምህርት ተቀርጾለት እየተሰጠ ቢሆንም በተሟላ መልኩ አይደለም፡፡ አሁን ባለዉ ሁኔታ የአትክልት ልማትን በተመለከተ በተወሰኑ ዩኒቨርስቲዎች (ጅማ ዩኒቨርስቲ ፣ ሐረማያ ዩኒቨርስቲ እና ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ) እና የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የሆርቲካልቸር ዘርፍ በተለያየ ደረጃ ትምህርት የሚሰጡ ሲሆን የአትክልት ልማትን በተመለከተ ግን ከሌሎች ጋር በማጣመር ትምህርት ይሰጣሉ፡፡ ተቋማቱ የቤተሙከራ እና የተግባር ላይ ስልጠናዎችን በተሟላ መልኩ ስለማይሰጡ በዘርፉ በቂ የሆነ ክህሎት ያላቸዉ ሰልጣኞች ማግኘት ከባድ ነዉ፡፡

የአትክልት ምርት ሥራ የገጠር የሰለጠኑ ወጣት የአርሶ አደር ልጆችን ሰፊ የሥራ ዕድል ሊፈጥር የሚችል ከመሆኑም በተጨማሪ ለገበያ ተብሎ ማምረት ስለሚቻል በሀገራችን ገጠር እና ከተማን በልማት የማስተሳሰር እና የዳበረ ገበያን ከመገንባት አኳያ ትልቅ ድርሻ ይጫወታል፡፡ በመላዉ ሀገሪቱ መባል በሚችል መልኩ የመስኖ ስራዎችን ለማጎልበት እየተሰሩ ያሉት አበረታች ስራዎች ለአትክልት ልማት ምቹ አጋጣሚ ከመፍጠራቸዉም በላይ የተደራጁ ወጣቶች እና ሴቶች በዘርፉ እንዲሰማሩ የተመቻቸ ሁኔታን ፈጥረዋል፡፡

በዘርፉ የሰው ሃይልን ከማብቃት አንፃር ሊሰሩ የሚገባቸው ሥራዎች ያሉ ሲሆን እነሱንም ወቅታዊ ሁኔታዎችን በመፈተሽ መተግበርን ይጠይቃል፡፡ አርሶአደሮች በአቅራቢያቸው ካሉት የገበሬዎች ማሰልጠኛ ማዕከል (farmers training center) በመጠቀም ሙሉ የአትክልት ልማት ፓኬጅ ስልጠና እና የተግባር ልምምድ በመስጠት ወደ ስራ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ዘርፍ ቀድመዉ መልካም አፈጻጸም ማለትም የግንባር ቀደሞችን መልካም ተሞክሮ ለሌሎች የማስፋፋት አቅጣጫን መከተል ጠቃሚ ነው፡፡ የተለያዩ የአትክልት ዓይነቶችን በመለየት እና የተሻለ የምርት ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በተለያዩ የሀገሪቷ ስነምህዳሮች ጋር በማጣጣም ሊተገበሩ የሚችሉ ሙሉ የአመራረት እና ድህረ ምርት የቴክኖሎጂ

ፓኬጆችን ማዘጋጀት እና በፓኬጁ ላይ ሰፊ ስልጠና መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በሀገሪቱ የሚገኙ የግብርና ኮሌጆች እና የቴክኒክ እና ሙያ ማሰልጠኛዎች በአትክልት ልማት ዘርፍ የአጭር ጊዜ እና የረጅም ጊዜ ተግባር ተኮር ስልጠናዎች በስፋት በመስጠት ወጣቱን በዕውቀት እና በክህሎት ብቁ እንዲያደርጉ ማድረግ መስራት ያስፈልጋል ፡፡ ስልጠናዎቹ በሚከተሉት ዘርፎች ላይ ቢሆን ያለዉን ክፍተት ሊሞላ ይችላል፡፡ የትምህርት መስኮቹ፡- Vegetable postharvest and food safety, Vegetable marketing, Commercial vegetables production and management and Home vegetable gardening ናቸዉ፡፡

### *5.1.2. የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ደረጃ ማሳደግ*

አትክልት ለማልማት የሚጠቅሙ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች በሀገራችን እና በቀላሉ ለማላመድ በሚቻል ደረጃ በሌሎች ሀገራትም ጭምር ያሉ ቢሆንም በሀገራችን ግን በሰፊው ጥቅም ላይ አልዋለም፡፡ ጥቅም ላይ ያሉ ቴክኖሎጂዎች እንኳ ቢሆኑ አንድም በተለምዶ ኃላ ቀር ዘዴ የሚሰሩ ስለሆነ ምርት እና ምርታማነትን ትርጉም ባለው መልኩ እንዲጨምሩ ያገዙ አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ ዉስጥ እስካሁን ያለዉን ዘመናዊ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ስንመለከት የሀገር በቀል ዕውቀቶችን እና ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ ሳንፈትሽ ከውጭ ሀገር በተላመዱት ላይ ትኩረት የማድረግ ዝንባሌ በሰፊው ይታያል፡፡ ከውጭ የሚገቡ የዕዉቀትም ሆነ የቁሳቁስ (material) ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም በራሳቸው ችግር ባይኖራቸዉም ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ስለሚጠይቁ የማምረቻ ዋጋንም ከፍ ያደርጋሉ፡፡

በኢትዮጵያ የአትክልት ልማት በቀጣይነት እንዲያድግ ከተፈለገ የቴክኖሎጂ አጠቃቀማችን ደረጃ ማሻሻል ምንም ጥያቄ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም መሻሻል የአትክልት ምርት እና ምርታማነትን ከማሻሻል በተጨማሪ ጥራቱን የጠበቀ ምርት በማምረት ለዓለም ገበያ (በዋናነትም ለአውሮፓ ገበያ) በመላክ ብቁ እና ተወዳዳሪ በመሆን ከፍተኛ ገቢ ማግኘት ይቻላል፡፡

በአትክልት ምርት የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ከማሳደግ አኳያ እና ዘርፉን ለማዘመን አብዛኛዉን የአትክልት ማለትም የቲማቲም፣የቃሪያ ፣ የካሮት ወዘተ ምርቶችን በግሪን ሃውስ እንዲመረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ አሁን ያለዉ የሀገሪቱ የግሪን ሀዉስ አጠቃቀም በጣም አነስተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በየጊዜዉ እያደገ እና እየተሻሻለ እንዲሄድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እነደዚሁም የውሃ አቅርቦትን በማሻሻል እና ያለውን የስነ

ምህዳር፣ የአየር ጠባይ ተለዋዋጭነት በመጠቀም አመቱን ሙሉ የአትክልት ምርቶችን ማምረት ለሀገር ዉስጥ እና ለዉጭ ገበያ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ለአትክልት ምርት የሚውሉ የዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ግብዓቶችን በሙሉ (ለምሳሌ፡- ጥብቅ እርሻ መስሪያ፣ የመስኖ ሥራ ግብአቶች፣ ለማጓጓዣ እና የማቀዝቀዣ መሳሪያዎች እና ሌሎችን) በሀገር ውስጥ በጥቃቅን እና አነስተኛ ተሳትፎ አልያም በብረታ ብረት ኮርፖሬሽን በኩል እንዲመረቱ እና ለገበያ እንዲቀርቡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የቲሹ ካልቸር ቴክኖሎጂዎችን በማስፋፋት እና በመጠቀም በአትክልት ልማት ዘርፍ ያለውን የዘር ወይም የችግኝ ችግር፣ የምርታማነት ማነስ ችግር፣ የምርት ጥራት ችግር እና የበሽታና ተባይ ችግርን ትርጉም ባለው መልኩ መፍታት፡፡ አሁን በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቋቋሙ የቲሹ ካልቸር ማዕከላትን የማጠናከር እና ቁጥራቸውን በማብዛት (ቢያንስ በእያንዳንዱ ዞን አንድ የቲሹ ካልቸር ማዕከል እንዲኖር በማድረግ) የአትክልት ልማትን በዘላቂነት ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡

### *5.1.3. መሰረተ ልማት ማሟላትና አጠቃቀም ማሻሻል*

የአትክልት ምርት በፍጥነት እና በቀጣይነት ለማሳደግ በቂ መሰረተ ልማት መኖር እና ምቹ የቢዝነስ አካባቢን መፍጠር የጎላ ሚና ይጫወታል፡፡ መሰረተ ልማት ሲባል የሚያሰራ የመንገድ መሰረተ ልማትን ጨምሮ፣ የመሬት አቅርቦት፣ የቀዝቃዛ መጋዘኖች አቅርቦት፣ የሀይል መሰረተ ልማቶችን የማሳ ላይ ስራ መሰረተ-ልማቶችን፣ ማቆያና የፓኬጂንግ እና የማጓጓዣ ያጠቃልላል፡፡
ለኮመርሻል የአትክልት ልማት የሚረዳ የመሬት አቅርቦት አስተማማኝ ማድረግ ከመንግስት ተቋማት የሚጠበቅ ሲሆን እርሻቸውን ለማስፋፋት እና አዲስ በዘርፉ ለመሰማራት ለሚፈለጉ ወጣቶች ባለሀብቶች ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ ባለሀብቶች መሬት ተረክበዉ ሳያለሙ በማቆየት ወይም መሬቱን ለሌላ ዓላማ በማዋል የኪራይ ሰብሳቢነት ድርጊት እንዳይስፋፋ አስፈላጊዉን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ለአትክልት ልማት የሚያስፈልጉ የሀይል መሰረተ ልማቶችን በማስፋፋት ለሁሉም ተደራሽ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ቀዝቃዛ መጋዘኖች በአዉሮፕላን ማረፊያዎች ጥራታቸዉን በጠበቀ ሁኔታ እንዲሟሉ ማድረጉ ሀገሪቱ ጥራት ያለዉ የአትክልት ምርት ኤክስፖርት እንድታደርግ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ በሀገሪቱ ገጠራማ አከባቢዎች ላሉ የአትክልት አምራች ባለሀብቶች በክላስተር በማሰባሰብ የሀይል፣ የመንገድ፣ የዉሃ፣ ቀዝቃዛ መጋዘን መሠረተ ልማቶች እንዲሟሉላቸዉ ማድረግ ይቻላል፡፡

የኢትዮጵያ  አየር መንገድ የካርጎ አገልግሎት የትራንስፖርት ጠያቂወች ከሙብዛታቸዉ የተነሳ አሁን ባለበት ሁኔታ  የአትክልት ምርቶችን በሚፈለገዉ መጠን እና ጊዜ ወደሚፈለገዉ የዉጭ ሀገር ገበያ እያጓጓዘ አይደለም፡፡ ከዚህም የተነሳ በሚቀጥሉት ዓመታት የአየር መንገድን የካርጎ አገልግሎት መስጫ መሠረተ ልማቶችን በከፍተኛ ደረጃ ማስፋፋት ያስፈልጋል፡፡

### 5.1.4. የተሟላ የሎጂስቲክስ እና ቀልጣፋ የገበያ አገልግሎት ማስፋፋት

አትክልትን ከማምረት ጀምሮ ተጠቃሚዎች ዘንድ እስከ ማድረስ ድረስ የሎጀስቲክስ አገልግሎቶች የሚያስፈልጉ ሲሆን ምርቱን ጥራቱን ጠብቆ በተፈለገበት ጊዜ ወደሚፈለግበት ቦታ እንዲደርስ ትልቅ ድርሻ ይጫወታሉ፡፡ ለአትክልት ምርት የሚያስፈልጉ ሎጀስቲክስ በበቂ ሁኔታ ካልተሟሉ የምርቱን ጥራት ዝቅተኛ ከማድረጋቸዉ በተጨማሪ የምርቱ ዋጋ እንዲጨምር ስለሚያደርጉ የገበያ ተወዳዳሪነትን ይቀንሳል፡፡

የአትክልት ምርት በባህሪው በብዛት (Bulk) ማጓጓዝን የሚፈለግ እና በአጭር ጊዜ የሚበላሽ (perishable) የግብርና ምርት ነው፡፡ ይህን ምርት ከኢትዮጵያ ወደ ሌሎች ሀገሮች ለማጓጓዝ ከሌሎች ሀገሮች (ለምሳሌ ከኬንያ፣ ከብራዚል እና ከደቡብ አፍሪካ) አንጻር ሲታይ በኢትዮጵያ በጣም ውድ እና በተፈለገው ጊዜ ለገበያ ማቅረብ የማይቻልበት ሁኔታ ያለ ሲሆን በዚህ ምክንያት ምርቶቹ በአለም ገበያ በዋጋ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ በተጨማሪም ምርቶቹ ወደ ሚፈለገው ቦታ ሳይደርሱ የመበላሸት አጋጣሚዎችም ሰፊ ናቸዉ፡፡

የአትክልት ምርቶች ትኩስነታቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ በአግባቡ የማሸግ፣ የማከማቸት እና የቅዝቃዜ ሰንሰለታቸዉን (cold chain) መጠበቅ የሚያስፈልግ ሲሆን በኢትዮጵያን ግን ለማሸግ የሚያገለግሉ ግብአቶች ጥራት መጓደል እና በከፍተኛ ወጭ ከውጭ ሀገር የሚገቡ በመሆኑ፤ የማከማቻ መጋዘኖች አለመኖር በተለይም በአነስተኛ አምራቾች አካባቢ፣ በቂ የማቀዝቀዣ መሣሪያዎች አለመኖር፣ በኤሌክትሪክ መቆራረጥ እና አለመኖር ምክንያት ምርቱ የሚፈለገውን የቅዝቃዜ መጠን መጠበቅ አለመቻል ዋነኛ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

ከዘርፉ ሀገሪቷ የላቀ ተጠቃሚ እንድትሆን እነዚህን እና ሌሎችን ተግዳሮቶች መለየት እና መፍትሄዎችን መተግበር የሚያስፈልግ ሲሆን በዋናነትም የሚከተሉትን ቢያካትት የተሻለ ለዉጥ በዘርፉ ሊመጣ ይችላል፡፡ እነሱም፡- ኤክስፖርት የሚደረጉ የሽንኩርት፣ የድንች፣ የካሮት ወዘተ  ምርቶችን በባቡር እስከ

ወደብ እና ከዚያ በኃላ በመርከብ በማጓጓዝ የሽያጭ ዋጋን በመቀነስ እና ምርቶቹ በፍጥነት ለመካከለኛዉ ምስራቅ ሀገራት ገበያ እንዲቀርቡ ማድረግ  እና ለአዉሮፓ ገበያ ለሚቀርቡት ምርቶች ግን በአየር ትራንስፖርት በመጠቀም የሀገሪቷን የአለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን መጨመር ይቻላል፡፡ ምርቶቹን ለማሸግ የሚውሉ ግብአቶችን ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ጥራታቸውን ጠብቀው ሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የአትክልት ምርት ቦታዎችን በተለይም ኮመርሻል (commercial) እርሻዎችን በክላስተር (cluster) በማቀናጀት የኤሌክትሪክ፣ የመንገድ፣ የዉሃ አገልግሎቶችን ሳይቆራረጥ የሚቀርብበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤ የማጓጓዣ ዘዴዎች እና የማከማቻ ቦታዎች ሁሉ በቂ የማቀዝቀዣ መሣሪያዎች እንዲኖራቸው ለማድረግ ግብአቶቹን በብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን እንዲመረቱ ማድረግ፤ ከአርሶአደሮች ማሳ እና በተደራጁ ወጣቶች ለሚያመረቱት ምርቶች የሚሆን በአቅራቢያቸው የጋራ ቀዝቃዛ መጋዘን፣ የማሸጊያ ግብአት ማምረቻ እና የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ፤የኤሌክትሪክ፣ የቴሌኮሚኒኬሽን እና የመንገድ አገልግሎቶችን የተጀመረውን የገጠር ተደራሽነትን አጠናክሮ ማስቀጠል ናቸዉ፡፡

### *5.1.5. የተደራጁ ወጣቶች እና የግል ባለሀብቶችን ተሳትፎ ማሳደግ*

ከ95 ከመቶ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ የአትክልት ምርት በአነስተኛ ማሳ ላይ የሚመረት ነው፡፡ በዘርፉ የባለሀብቶች ተሳትፎ እየጨመረ የመጣ ቢሆንም ሀገሪቷ ካላት ዕምቅ አቅም ከመጠቀም እና በዘርፉ ስኬት ካሳዩ ሀገራት (ለምሳሌ፡- ብራዚል እና ሞሮኮ) አኳያ ሲታይ እስካሁን ያለው ተሳትፎ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፡፡

በዋነኛነትም የተማሩ ወጣቶች እና ባለሀብቶች እንዲሁም የውጭ ሀገር ባለሀብቶችን ዕዉቀት እና ክህሎት በመጠቀም እና በዘርፉ በብዛት በማሳተፍ ገበያ ተኮር የአትክልት (commercial vegetables) ምርት በብዛት እና በጥራት በማምረት ሀገሪቱን በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል፡፡ የሴቶች ልማት ፓኬጅ፣ የወጣቶች ልማት ፓኬጅ እና የሀብታም አርሶ አደር ልማት ፓኬጆችን በመጠቀም የሀገር ዉስጥ በአትክልት ልማት ዘርፍ የግል ባለሀብቶችን ተሳትፎ ማሳደግ ይቻላል፡፡ ሀገሪቷ የአትክልት ምርትን በዓይነት እና በብዛት ለማምረት የሚያስችሉ የተፈጥሮ ፀጋዎች ባለቤት ስለሆነች የዉጭ ኢንቨስተሮችም በዘርፉ የተጠናከረ የዲፕሎማሲ ስራ በመስራት ባላሀብቶቹን የመሳብ እና ቀደም ብለዉ በዘርፉ

ለተሰማሩት ምቹ የሥራ አከባቢ ቢፈጠርላቸው ከየትኛውም ሌላ ሀገር በላይ ባለሀብቶችን ወደ ኢትዮጵያ መሳብ ይቻላል፡፡

እንዲሁም ከባላሀብቶቹ ያልተናነሰ በዘርፉ ለውጥ ማምጣት የሚያስችል ተሳትፎ ከሀገር ውስጥ ወጣቶችን በማደራጀት እና አሰልጥኖ ወደ ሥራ በማስገባት ሊገኝ ይችላል፡፡ በሀገራችን በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የተማሩ የአርሶ አደሩ ሆነ ለሎች ልጆች በየአመቱ ከተለያዩ የሀገሪቱ ዩኒቨርስቲዎች እና የቴክኒክ እና ሙያ ኮሌጆች በመመረቅ የሥራ ገበያውን (job market) ይቀላቀላሉ፡፡ እነዚህን የተማሩ ወጣቶች በማደራጀት ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ማድረጉ ብዙ ጥቅም ያለው ሲሆን በዋናነትም ግብርናውን ለማዘመን የተጀመረውን ሥራ ያጠናክራል፣ የወጣቱን የሥራ ዕድል ከማሳደግ ባሻገር በዘርፉ አዳዲስ ልማታዊ ባለሀብቶችን የመፍጠር ማሳደግ እንዲሁም ምርታማነት እንዲጨምር ይረዳል፡፡

የአትክልት ምርት ለማሳደግ የባለ ድርሻ ተሳትፎን ከማሳደግ አኳያ በሚቀጥሉት 10 ዓመታት የሚከተሉት ተግባራት ሊሰሩ ያስፈልጋል፡፡ እነሱም፡-የውጭ ሀገር እና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በዘርፉ ያላቸውን ኢንቨስትመንት በየዓመቱ በከፍተኛ መጠን እያደገ እንዲሄድ ማድረግ፤ ቅድሚያ ሰጥቶ ወጣቶችን በማደራጀት ለአትክልት ምርት አመቺ በሆኑባቸው የሀገራችን ቦታዎች ሁሉ ወደ ሥራ ማስገባት፤ ቀደም ብለው በዘርፉ የተሰማሩትን ባለሀብቶች በማበረታታት እና ያለባቸውን ችግር በቅርበት በመፍታት ወደ ተሻለ አምራችነት እንዲሸጋገሩ ማድረግ፤ በዘርፉ የተሰማሩ እና ሊሰማሩ ለሚፈልጉ ባለሀብቶች እና የተደራጁ ወጣቶች መንግሥት የብድር አገልግሎት፣ የግብር እፎይታ፣ የተቀላጠፈ የመንግሥት አገልግሎቶች በመስጠት ተሳትፏቸው እንዲያድግ እና የዘርፉ ዋና ተዋናይ እንዲሆኑ ማስቻል ናቸዉ፡፡

### *5.1.6. የአዉሮፓን የጥራት ደረጃ የሚያሟሉ ምርት ማምረት*

በሀገር ውስጥም ሆነ በኤክስፖርት ገበያ በአትክልት ምርት ሀገሪቷ ተወዳዳሪ ሁና መዝለቅ የምትችለው ጥራቱን እና አስፈላጊውን ደረጃ የሚያሟላ ምርት ማቅረብ እስከተቻለ ብቻ ነው፡፡ አሁን ያለው የሀገሪቷ የአትክልት ምርት በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በአውሮፓ ደረጃ የተቀመጠውን የጥራት ደረጃዎች ስለማያሟላ በዘርፉ ባለው ትልቁ የአውሮፓ እና የመካከለኛው ምሥራቅ ገበያ ተወዳዳሪ አይደለም፡፡

የምርት ጥራት የሚገለፀው ከግብአት እስከ ድህረ-ምርት አያያዝ ድረስ የሚከናወኑትን ሥራዎች (የምርት ሂደት) የሚያጠቃልል ስለሆነ ብዙ ትኩረት የሚፈልግ ጉዳይ ነዉ፡፡ ግሎባላይዜሽን በፈጠረው የገበያ

ትስስር እና የመገናኛ ዘዴዎች ማደግ ምክንያት ጥራት ያለው የአትክልት ምርት ያመረተ ሀገር በዓለማችን ካሉት የትኛውም ሀገር ጋር መነገድና ትርፋማ መሆን ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያም ከዘርፉ የላቀ እና ቀጣይነት ያለው ጥቅም ለማግኘት ከፈለገች ፔሩእና ብራዚል እንዳደረጉት እና በአጭር ጊዜ በሀገራቸዉ በዘርፉ ለውጥ እንዳመጡት ሁሉ ጥራቱን እና ደረጃውን የጠበቀ ምርት ማምረት የግድ ይላታል፡፡

በኢትዮጵያ የአትክልት ምርት ጥራት እና ደረጃ ከማሻሻል አኳያ በሚቀጥሉት አሥርት ዓመታት በትኩረት ሊሰሩ የሚገባቸው ሥራዎች የመልካም እርሻ አሰራርን (good agricultural practices/GAP) በሁሉም አነስተኛ ማሳ የአትክልት እርሻዎች እና በባለሀብቶች የአትክልት ማሳ ላይ እንዲተገበር ማድረግ፡፡ ለዚህ ትግበራ የሚረዳ የአሰራር ስርአት እና የሕግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀት ሁሉም የሀገሪቷ የአትክልት ምርቶች የአውሮፓን የአትክልት ምርት ጥራት እና ደረጃ (Annex 1) በጠበቀ መልኩ ማምረትያስፈልጋል፡፡ የአዉሮፓ ገበያን የጥራት ደረጃ ያሟላ ምርትም የትኛዉም የአለማችን ገበያ ለመግባት የማያስቸግር ይሆናል፡፡ የአትክልት ዝርያዎችን ጥራት እና ምርታማነትን ለማሻሻል በሀገር ውስጥ ሰፊ የጥናት እና ምርምር ሥራዎች በመስራት የዘርፉን ቀጣይ እድገት አስተማማኝ ማድረግ፡፡ ምርታማ ያልሆኑ እና የጥራት ችግር ያለባቸውን የአትክልት ምርት በሌላ በተሻሻሉ ዝርያ መተካት እና ዘሩ ወይም ችግኙ በበቂ መጠን ገበያ ላይ እንዲገኙ ማድረግ፤ የአትክልት ምርትን ጥራት በሁሉም ደረጃ (ከምርት እስከ ገበያ ድረስ) ያለውን የሚከታተል፣ የሚያማክር እና መረጃን የሚያቀናብር አደረጃጀት ወይም ተቋም ማጠናከር ናቸዉ፡፡

## *5.2. የፍራፍሬ ልማት እስትራቴጂክ ግቦች እና የአፈፃፀም አቅጣጫዎች*

ኢትዮጵያ የተለያዩ የአግሮ-ኢኮሎጅ ዞኖች ስላሏት የተለያዩ የቆላ (tropical) እና የወይና ደጋ (temperate) የፍራፍሬ ምርቶች የማምረት ትልቅ ዕምቅ አቅም አላት፡፡ የፍራፍሬ ምርት እና የገበያ እንቅስቃሴ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የማሳተፍ ዕድል ስላለው ለብዙዎች የሥራ ዕድል ይፈጥራል፡፡ ምርቶቹንም ኤክስፖርት በማድረግ ሀገሪቷ የተሻለ የውጭ ምንዛሪ እንድታገኝ ያስችላል፡፡

ይሁን እንጂ የፍራፍሬ ምርት በኢትዮጵያ በዝቅተኛው የእድገት ደረጃ የሚገኝ እና ወደፊት በዘርፉ በመንግሥት እና በባለሀብቶች ትኩረት ቢሰጥበት በከፍተኛ ደረጃ ማደግ የሚችል ዘርፍ ነው፡፡ አሁን ባለበት ሁኔታ ሲታይ ዘርፉ በብዙ ውስጣዊ እና ውጫዊ ችግሮች የተተበተበ ሲሆን ከነዚህም ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት፣ የተሻሻለ ዝርያ እና የዘር/ችግኝ አቅርቦት እጥረት፣ የሎጀስቲክስ ችግሮች፣ የጥራት ችግር እና ዝቅተኛ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ናቸው፡፡ እነዚህን ችግሮች እና የወደፊት ተግዳሮቶች በመለየት በዘርፉ የተሻለ ስራዎች ቢሰሩ ሀገሪቱ ከፍራፍሬ የምታገኘውን ገቢ በከፍተኛ መጠን ማሳደግ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር የሚከተሉትን ዋና ዋና የአፈፃፀም አቅጣጫዎችን ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡

### *5.2.1. በመካከለኛ እና በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሃይል ማፍራት*

ሀገራችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የዩኒቨርስቲዎች እና የቴክኒክ እና ሙያ ኮሌጆች በእጅጉ መስፋፋት ምክንያት ብዙ ወጣቶች የከፍተኛ ትምህርት ዕድል ያገኙ ቢሆንም በፍራፍሬ ልማት ዘርፍ ግን በየትኛው ተቋም ትኩረት ተሰጥቶት ለብቻው በተደራጀ መልኩ ስልጠና እየተሰጠ አይደለም፡፡ በየወረዳው እና ቀበሌው ተመድበው የሚሰሩ የልማት ሰራተኞች በፍራፍሬ ልማት በቂ ስልጠና ስለሌላቸው በአነስተኛ ማሳ ላይ ለሚመረቱት የፍራፍሬ ምርት በቂ የሙያ ድጋፍ አይሰጡም፡፡ ከዚህ አንጻር በዘርፉ የሚያስፈልገዉን የሰው ሀይል ለማብቃት ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

የተለያዩ ፍራፍሬዎች ማምረት የሚያስችል ዕውቀት አርሶ አደሮችን እና ወጣቶችን ለማሰልጠን የተሟላ የስልጠና ፓኬጅ በማዘጋጀት እና በተግባር በመደገፍ ተከታታይነት ያለው ስልጠና መስጠት፤ ሀገሪቷ

ውስጥ ባሉት ዩኒቨርስቲዎች እና የቴክኒክ እና ሙያ ኮሌጆች በተለይም የፍራፍሬ ምርት የሚዘወተርባቸው አካባቢዎች ባሉት የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከአጭር ስልጠናዎች አንስቶ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ በብቃት ማሰልጠን ያስፈልጋል፡፡ የትምህርት መስኮቹ Fruit production, Fruit processing, Fruit marketing, Fruit post harvest and food safety በቀጥታ ከማምርት ስራ የተያያዙት የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

### *5.2.2. የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ደረጃ በማሳደግ የኢንዱስትሪ ትስስርን ማጠናከር*

የፍራፍሬ ምርት ለማሳደግ የሚረዱ ቴክኖሎጂዎችን በሰፊው መጠን መጠቀም ምርታማነትን ለመጨመር ከመርዳቱም ባሻገር ጥራቱን የጠበቀ ምርት ለገበያ ለማቅረብ ይረዳል፡፡ እስካሁን በዘርፉ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ሀገራችን አነስተኛ ሲሆን ይህን ችግር መፍታት ካልተቻለ በዘርፉ ዕምርታዊ ለውጥ ማምጣት አይቻልም፡፡ በዘርፍ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ከማጎልበት አንጻር በዋናነት ሊሰሩ የሚገባቸው ሥራዎች ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

የቲሹ ካልቸር ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የፍራፍሬ ምርታማነትን እና የዘር ወይም የችግኝ አቅርቦትን በማሻሻል ከፍተኛ ጥራት ያለው ምርት ማምረት ይቻላል፡፡ የቲሹ ካልቸር ቴክኖሎጂዎችን በዩኒቨርስቲዎች እና በምርምር ማዕከላት በብዛት በማቋቋም ለዘርፉ እድገት የላቀ ድርሻ እንዲያበረክት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የፍራፍሬ ምርቶችን በተለይ የማንጎ፣ የብርቱካን፣ የፓፓያ ወዘተ ምርቶችን ለኢንዱስትሪ ግብአትነት በመጠቀም በከፊል ወይም በሙሉ በኢንዱስትሪ የተቀነባበሩ ምርቶችን ለገበያ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ይህን በማድረግ አግሮ ኢንዱስትሪ በሀገሪቱ እንዲስፋፋ እና ተጨማሪ የስራ ዕድሎችን በመፍጠር ሀገሪቷ የተያያዘችዉን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር የማሳካት ሥራን ያግዛል፡፡ በኢንዱስትሪ የተቀነባበሩ የፍራፍሬ ምርቶችን በተለይ የብርቱካን፣ የማንጎ፣ፓይን አፕል እና የእንጆሪ ምርቶች የመሳሰሉትን ለሀገር ዉስጥ እና ለኤክስፖርት ገበያ በስፋት ማቅረብ ያስፈልጋል፤ ሀገሪቷ ካላት ዕምቅ አቅም አኳያ ሲታይም ማሳካት ይቻላል፡፡

ወጣቶችን እነዲሁም ሌሎች የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን በማስተባበር እና በማደራጀት በሰፋፊ የመንግሥት የስኳር ፋብሪካዎች የሸንኮራ አገዳ ማሳዎችን በመጠቀም ለሸንኮራ አገዳ የንፋስ ማገጃ (wind breaks)

በሚያገለግል እና ከፍተኛ ምርትም በሚሰጥ መልኩ ፍራፍሬን (በተለይ ማንጎ፣ አቮካዶ እና ስትሩት ፍሩትስ) ማምረት ይቻላል፡፡ በሀገሪቱ በተለዩት የልማት ኮሪደሮች በመጠቀም እና የአከባቢያዊ ስነ ምህዳር በሚፈቅደዉ መሰረት ዳይቨርሲፊኬሽን እና ስፔሻላይዜሽንን በመተግበር በየአከባቢዉ ከሚገኘው የልማት ፀጋዎች ሀገሪቷ የበለጠ ተጠቃሚ እንድትሆን ማድረግ ይቻላል፡፡ ከአከባቢ ጥበቃ ስራዎች ጋር ተያይዞ በመላዉ ሀገሪቱ በተለይም ለሰብል እርሻ ምቹ ያልሆኑ ተራራማ ቦታዎች እንዲከለሉ በማድረግ የአፈር እና የዉሃ ጥበቃ የጠረጰዛ እርከን ስራዎች ጋር ተያይዞ ለፍራፍሬ ምርት አመቺ የሆኑ ቦታዎች በስፋት ተፈጥረዋል፡፡

ለውሃ አቅርቦት የሚረዱ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በስፋት በመጠቀም ዓመቱን ሙሉ ፍራፍሬን ማምረት ያስፈልጋል፡፡ እነዚህን የውሃ ቴክኖሎጂዎች (የውሃ ፓምፕ፣ ማጣሪያ፣ የውሃ ቱቦ፣ የውሃ መርጫ እና መቆጣጠሪያ) በሀገር ውስጥ በባህለብቶች ተሳትፎ እና በብረታ ብረት ኮርፖሬሽን እንዲመረት በማድረግ አቅርቦታቸውን እና ዋጋቸው ማሻሻል ይገባል፡፡ በግል ባለሀብቶች በአዳዲስ ልማት አካባቢወች ለኢንቨስቲመንት ተብለዉ በተከለሉ መሮቶች የፍራፍሬ እርሻ በማስፋፋት እስከ አግሮ-ፕሮሰሲንግ ማደግ በሚቻል ኢንቨስትመንት ዉስጥ እንዲሳተፉ ማስቻል ተጨማሪ አስተዋጾዉ በቀላሉ የማይታይ ነዉ፡፡

### 5.2.3. መሰረተ ልማት ማሟላትና አጠቃቀም ማሻሻል

በኢትዮጵያ የመሰረተ ልማት አቅርቦት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ያለ ሲሆን ለፍራፍሬ ልማት የሚያስፈልጉ ወሳኝ የሆኑ መሰረተ ልማቶች ማለትም የመንገድ፣ የሀይል፣ የመስኖ፣ የገበያ እና የመገናኛ ዘዴዎች በዋናነት መጠቀስ የሚችሉ ናቸዉ፡፤ የነዚህ መሰረተ ልማቶች አለመኖር የምርቶቹ ዋጋ እንዲኖር ከማድረጉም በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥራት ያለው ምርት ለገበያ ማቅረብ አይታሰብም፡፡
ለገጠር የሀገራችን ክፍሎች ያለው የቀዝቃዛ መጋዘን፣ የገበያ፣የመረጃ መሠረተ ልማቶች በበቂ ሁኔታ ካለመዳረሳቸዉ የተነሳ በዚያ አከባቢ የሚመረቱ የፍራፍሬ ምርቶች ጥራት እና ምርታማነት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ከማሳደሩም አልፎ በዘርፉ ያለዉ ኢንቨስትመንት በነዚህ ቦታዎች እንዳይስፋፋ አድርጓል፡፡ ለፍራፍሬ ምርቶች ዘመናዊ የማምረቻ ፋሲሊቲዎችና ለፓኬጂንግ ስራ የሚገለግሉ ግብአቶች ለማምረት የሚያስፈልጉ መሠረተ ልማቶችን ማስፋፋት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የፍራፍሬ ተረፈ ምርቶችን ለእንስሳት መኖነት እና ለሌሎች የኢንዱስትሪ ግብአት እንዲዉል ማድረግ ስለሚቻል ለዚህ የሚያስፈልገዉን መሠረተ ልማቶችን በመለየት ማስፋፋት ያስፈልጋል፡፡ አምራቾችን ደረጃ በደረጃ ግን

በሰለጠነ መንገድ ሁል ጊዜ ወደ ላቀ የፍራፍሬ የማምረት ስርአት ዉስጥ እያሸጋገሩ መጓዝ የዘርፉን ትራንስፎርሜሽን ለማረጋገጥ ወሳኝ ነዉ፡፡

### *5.2.4. የተሟላ የሎጀስቲክስ እና ቀልጣፋ የገበያ አገልግሎት ማስፋፋት*

ኢትዮጵያ ፍራፍሬ ምርቶቿን ለመካከለኛ ምስራቅ፣ ለአፍሪካ ጎረቤት ሀገሮች እና ለአውሮፓ ገበያወች ትልካለች፡፡በኢትጵያ የሚመረቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ለሀገር ዉስጥ እና ለኤክስፖርት ገበያ ሲቀርቡ የአቅርቦት ሰንሰለታቸዉም ረጅም እና ብዙ ተዋኒያኖች የሚሳተፉባቸዉ ከመሆኑም ጋር ተያይዞ ደላሎች (brokers) ትልቅ የዋጋ ተጽእኖ ያሳድሩበታል፡፡ በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ ገበያ ተኮር የሆነ የፍራፍሬ ምርት ማምረት ትኩረት መስጠት፣ ወቅታዊ የሆነ የገበያ መረጃ አቅርቦት ስርአት በተሟላ ማቅረብ፣ ምርቱ ጥራቱን ጠብቆ እንዲመረት እና በገበያ የተሻለ ዋጋ እንዲያወጣ በቂ የባለሙያ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የፍራፍሬ auction ገበያ መዳበር ለአስተማማኝ የጥራት ምርትና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ የዋጋ ስርኣት የተተከለበት ማድረግ ያስችልል፡፡

የፍራፍሬ ምርት የሚገኘውን ጥቅም ለማሳደግ በዘርፉ ያሉትን የሎጀስቲክስ አገልግሎት እና የተሻለ ተቋማዊ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በኢትዮጵያ የፍራፍሬ ምርት ተመርቶ እስከ ተጠቃሚዎች ድረስ ከፍተኛ ብክነት ያጋጥማል፡፡ ለዚህም ዋናዉ ችግር ከተመረተ በኋላ የማሸግ እና የማከማቸት ሥራዎች በአግባቡ ስለማይሰሩ እና በሚፈለገው ጊዜ ተጓጉዞ ተጠቃሚዎች ዘንድ ስለማይደርስ ሲሆን በዚህ በኩል ያለዉን ችግር መፍታት ያስፈልጋል፡፡ ኤክስፖርት የሚደረጉ የፍራፍሬ ምርቶች ቢሆኑም እንኳ በቂ የማጓጓዣ መኪና እና ቀዝቃዛ ኮንተይነር እጥረት ስላለው ጥራቱን እና መጠኑን ጠብቃ ወደሚፈለግበት ቦታ አይደርስም ቢደርስም ለማጓጓዝ የሚያስፈልገው ገንዘብ በጣም ከፍተኛ ይሆናል፡፡ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች እንዳይበላሹ ተገቢውን የማሸግ ሥራ መስራት፣ የቅዝቃዜ ሰንሰለቱን መጠበቅ እና ለምርቱ ባሕሪ የሚመች የማከማቻ መጋዘኖችን ማዘጋጀት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይጠይቃል፡፡

### *5.2.5. የተደራጁ ወጣቶች እና የግል ባለሀብቶችን ተሳትፎ ማሳደግ*

ዘርፉን ከማሳደግ አኳያ መንግሥት ከሚያደርገው የማመቻቸት እንቅስቃሴ በተጨማሪ የግል ባለሀብቶች እና የወጣቶች ድርሻ ትልቅ ነው፡፡ ሀገር በቀል ወይም የውጭ ባለሀብቶች ሰፋፊ ኮሜርሻል የፍራፍሬ እርሻዎችን በመጠቀም በዘመናዊ ዘዴ ከፍተኛ ምርት ማምረት ይችላሉ፡፡ እነዚህ ባለሀብቶች ለፍራፍሬ እርሻ ምቹ በሆኑ የሀገራችን ቆላማ ስፍራዎች መሰማራት ቢችሉ በዘርፉ ዕምርታዊ ለውጥ ማምጣት ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የግል ባላሀብቶቹ የፍራፍሬ ምርትን በግብአትነት የሚጠቀም አግሮ-ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም እሴት የተጨመረበትን የፍራፍሬ ምርት እንዲመረት ትልቅ ድርሻ መጫወት ይችላሉ፡፡ ከባላሀብቶቹ ባልተናነሰ መልኩ የአርሶ አደሩ ወጣት ልጆች ተደራጅተው እና ያለባቸው የክህሎት፣ የፋይናንስ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ችግራቸው ተፈቶ ወደ ዘርፉ ቢሰማሩ በዘርፉ ተአምር መስራት ይችላሉ፡፡ በተፋሰስ ልማት እና በአከባቢ ጥበቃ ስራዎች በተፈጠሩት ለፍራፍሬ ምርት ምቹ ቦታዎች በመጠቀም ወጣቶችን እና ሴቶችን በማደራጀት በቦታዎቹ በፍራፍሬ ምርት ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ ይቻላል፡፡ እነዚህ ወጣቶች እና ሴቶች በሂደት ወደ ባለሀብትነት ስለሚቀየሩ ዘርፉን በዘላቂነት ለማሳደግ በሚደረገዉ ጥረት ትልቅ ድርሻ ያበረክታሉ፡፡

የፍራፍሬን ምርት ለማሳደግ የባለሀብቶች እና የወጣቶች ተሳትፎ በማንኛውም መልኩ ሲታይ ወሳኝ ሲሆን ተሳትፎአቸውንም ለማሳደግ በዋናነት የሚከተሉትን ሥራዎች መሰራት ያስፈልጋል፡፡ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በዘርፉ እንዲሰማሩ ማበረታታት፤ የውጭ ሀገር ባለሀብቶች በዘርፉ ያላቸዉ ተሳትፎ በቀጣታይነት እንዲያድግ መስራት፤ በተለይ እና በዋናነት ወጣቶችን በማደራጀት እና በማሰልጠን በፍራፍሬ ልማት ላይ ማሰማራት ፤ ለስኳር ፋብሪካ ግብአት ተብለው በሰፋፊ እርሻዎች ላይ ለሚመረቱ የሸንኮራ አገዳ ለንፋስ ማገጃ (wind breaks) በሚያግዝ መልኩ የተለያዩ የፍራፍሬ ምርቶችን ማስፋፋት፡፡ በዚህ ላይ የተደራጁ ወጣቶች በሰፊው ሊሳተፉ የሚችሉ ሲሆን የእርሻ ማሳዎቹ ሰፊ ከመሆናቸው አንፃር መንግሥት ሁኔታዎቹን እያመቻቸ የፍራፍሬ ምርትን በትልቁ በኮመርሻል ስኬል እነዲመረት ማድረግ ያስችላል፡፡

## 5.2.6. የአዉሮፓን የጥራት ደረጃ   የሚያሟሉ ምርቶች ማምረት

ለሀገር ውስጥ ገበያ ይሁን ለኤክስፖርት ሊውሉ የሚችሉ የፍራፍሬ ምርቶች ጥራታቸውን እና ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን ጠብቀው ካልተመረቱ በሀገር ውስጥ ይሁን በሌሎች ሀገሮች ተወዳድረው ገበያ ሊያገኙ ስለማይችሉ ለሀገሪቱ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኙ አይችሉም፡፡ በተጨማሪም ይህ አካሄድ ወደ ሀገራችን ኢምፖርት በሚደረጉ የፍራፍሬ ምርቶች እንድትጥለቀለቅ የሚያደርግ እና የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሬ የሚመጥ ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ሀገራችን የዘርፉን እምቅ አቅም በላቀ ደረጃ እንድትጠቀም ጥረት እና ደረጃው ከፍ ያለ እና በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ የሆነ የፍራፍሬ ምርት ማምረት ግድ ይላታል ማለት ነው፡፡ በዚህ ረገድ በዋናነት በሚቀጥሉት ዓመታት ሊሰሩ የሚገባቸው እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡ እነሱም-መልካም እርሻ አሰራርን (good agricultural practices) በሁሉም የሀገራችን የፍራፍሬ አምራቾች ዘንድ መተግበር፤ ሁሉም የፍራፍሬ ምርት የአውሮፓን እና የዓለምን የጥራት ደረጃን (GFSI, ISO 2200 AND ERUEGAP) በሚያሟላ ደረጃ እንዲመረቱ ማስቻል ያስፈልጋል፤ የተሻሻለ ዝርያ አቅርቦትን ማረጋገጥ የሚያስፈልግ ሲሆን ይህን ለማድረግ በዩኒቨርስቲዎች እና በምርምር ማዕከላት የሚደረጉትን የዘርፉን ምርምሮች ማጠናከር፤ ከምርት እስከ ተጠቃሚው ወይም ገበያ ድረስ ያለውን የፍራፍሬ ምርቶች ጥራት ማስጠበቂያ ዘዴዎችን  እና ቴክኖሎጂዎችንም ጭምር በስፋት መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

# ክፍል ስድስት

## 6. ማጠቃለያ - የአትክልት እና የፍራፍሬ ልማት ለኢትዮጵያ ህዳሴ ያለው እንደምታ

ኢትዮጵያ ለዘመናት ከምትታወቅበት የድህነት አረንቋ ለመውጣት ባለፉት ሁለት አሥርት አመታት ቀጣይነት ያለው እና ባለ ሁለት አሀዝ የኢኮኖሚ እድገት እያስመዘገበች ያለች ሀገር መሆኗ ይታወቃል፡፡ ለዚህ እድገት በዋናነት ሊጠቀስ የሚገባዉ ምክንያት ግብርናን እና ገጠርን ማዕከል ያደረገ የልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጅ ተነድፎ በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል በመቻሉ ነው፡፡

የግብርና ምርት እና ምርታማነት ከመቼው ጊዜ በላይ ማሻሻል በመቻሉ በገጠሪቱ የሀገራችን ክፍል ካፒታል መፈጠር በመጀመሩ ምክንያት ከተሞቻችን፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ሥራዎች እና የኤክስፖርት ክንውኖች ከመቸዉም ጊዜ በላይ መነቃቃት አሳይተዋል፡፡ በግብርና ልማት ረገድ እስካሁን ድረስ የተመዘገበው እድገት በዋናነት በሰብል እና በእንስሳት ልማት ዘርፉ የተገኙ ውጤቶች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም ገና ያልተነኩ የግብርና ዘርፎች ሀገሪቷ ያላት ሲሆን ከነዚህም የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት አንዱ መሆኑ እና ከዘርፉ ከፍተኛ ዋጋ የላቸዉን ምርቶችን ማምረት እንደሚቻል በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች በግልጽ ያመለክታሉ፡፡

በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ኢትዮጵያ ያልተነካ ዕምቅ አቅም ያላት እና ይህን አቅም በመጠቀም አዲስ የግብርና እድገት ማስቀጠያ ምንጭ (Growth driver) እና የሀገሪቷን የኤክስፖርት መጠን ማሳደግ የምትችልበት ሁኔታ ይታያል፡፡ ሀገራችን ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት አስፈላጊ የሆኑ ምቹ እና የተለያየ የአየር ንብረት፣ ለም አፈር፣ የዝናብ መጠን፣ ወንዞች እና የከርሰ ምድር ውሃ የተፈጥሮ ፀጋዎች ባለቤት ነች፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በቀላሉ መሰልጠን የሚችል ሰፊ የሰው ጉልበት ያላት እና በቅርብ ርቀት ለአውሮፓ ገበያ እና ለመካከለኛው ምስራቅ ገበያ መገኘቷ ሌላው ለዘርፉ እድገት መልካም አጋጣሚዎች ናቸው፡፡ አሁን በሀገሪቷ እየታየ ያለው ፈጣን እድገት እና ከየትኛው ጊዜ በላይ በሁሉም የሀገሪቷ ክፍሎች እየተስፋፋ ያለው መሰረተ ልማት (መንገድ፣ ውሃ፣ የትምህርት ተቋማት፣ የጤና ተቋማት፣ ቴሌኮም፣ ...) ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚያስፈልጉትን ግብአቶች ከማሟላት በተጨማሪ ለሀገሪቷ እና ለዘርፉ ህዳሴ ከፍተኛ መነቃቃትን ፈጥሯል፡፡

ሀገሪቷ ካላት አቅም እና ፍላጎት አኳያ ሲታይ አሁን እየተመረተ ያለውም ሆነ ለኤክስፖርት እየዋለ ያለው የአትክልት እና የፍራፍሬ ምርት መጠን እጅግ በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ለዚህም በዋነኛነት የሚጠቀሱት ተግዳሮቶች በቂ የሰለጠነ የሰው ሀይል እጥረት፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና ደረጃ ዝቅተኛ መሆን፣ የሎጀስቲክስ እጥረት፣ የዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃን ያልጠበቀ ምርት ለገበያ ማቅረብ እና በዘርፉ በተደማሪነት የሰለጠኑ ወጣቶችን  ተሳትፎ አነስተኛ መሆን ናቸው፡፡ ዘርፉን ለማዘመን እና በቀጣይነት እንዲያድግ በማድረግ ለሀገራችን ህዳሴ የበኩሉን እንዲያበረክት ለማድረግ ሀገሪቷ ያላትን ዕምቅ አቅም አሟጦ በመጠቀም እና ከላይ የተጠቀሱትን ተግዳሮቶች ለመፍታት ትኩረት ሰጥቶ መሰራትን ይጠይቃል፡፡

ሀገራችን የጀመረችውን የልማት ጉዞ ያለቆምታ እንድታሳካው የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት እድገት የጎላ ድርሻ ይጫወታል፡፡ ይህም በአንድ በኩል ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚውል በቂ ምርት በማምረት የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ እና ከውጭ ወደ ሀገር ዉስጥ የሚገቡትን የዘርፉን ምርት በማስቀረት የውጭ ምንዛሬ የማዳን ድርሻን ይጫወታል፡፡ በሌላ በኩል ምርቶቹን በብዛት እና በጥራት ኤክስፖርት በማድረግ ለሀገራችን ያልተቋረጠ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት ይቻላል፡፡ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት በባሕሪው ሰፊ ጉልበትን የሚጠቀም ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የዘርፉ እድገት ለብዙ ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራል፡፡ በተጓዳኝም ወጣቱን በማሳታፍ ልማታዊ ባለሀብትን ማፍራት ያስችላል፡፡ ዘርፉን በቀላሉ ከኢንዱስትሪ ጋር በማያያዝ እና ሀገራችን በስፋት በአሁኑ ወቅት የተያየዘችውን የአግሮ ኢንዱስትሪ የማስፋፋትን ሥራ የማቀላጠፍ እና የማሳደግ ድርሻ በከፍተኛ መጠን መጫወት ይችላል፡፡

በአጠቃላይ ሀገራችን ያላትን እምቅ የአትክልትና ፍራፍሬ የማምረት ችሎታ አሟጦ በመጠቀም የግብርና ምርትን እና የአግሮ ፕሮሰሲንግ ሥራን በማሳለጥ እና በማሳደግ ሀገሪቷ ለተያያዘችው የትራንስፎርሜሽን እና የህዳሴ ጉዞ ስኬት የላቀ ድርሻ ማበርከት ይቻላል ፤ ያስፈልጋልም፡፡

## ዋቢ (References)


Cardoso Costa, M.G., Xavier, A. and Campos Otoni, W. 2006. HORTICULTURAL BIOTECHNOLOGY IN BRAZIL. Acta Hort. (ISHS) 725:63 72 http://www.actahort.org/books/725/725_3.htm

Council Regulation (EC) No 2200/96 of 28 October 1996 on the common organization of the market in fruit and vegetables http://www.mof.gov.cy/mof/customs/Customs.nsf/0/1B6330534E3DAA9CC225730D001F2DB3/$file/2200-1996.pdf?OpenElement

CSA (Central Statistical Agency) (2013). Agricultural Sample Survey: Report on Area and Production of Major Crops for Private Peasant Holding, Vol. I. Statistical Bulletin 532. CSA, Addis Ababa, Ethiopia.

Diop, N. and Jaffee, S. M. (Undated). FRUITS AND VEGETABLES: GLOBAL TR ADE AND COMPETITION IN FRESH AND PROCESSED PRODUCT MARKETS http://siteresources.worldbank.org/INTPROSPECTS/Resources/GATChapter13.pdf

EHDA (Ethiopian Horticulture Development Agency), 2012. Ethiopian Horticulture Sector Statistical Bulletin Available at http://www.ehda.gov.et/Downloads/Statistical_Bulletin%282012%29.pdf Acceesed on April 07, 2015

EHDA (Ethiopian Horticulture Development Agency), 2014. ዓመታዊ ሪፖርት

EHDA (Ethiopian Horticulture Development Agency), ከ 2001 እስከ 2005 ዓመታዊ ሪፖርቶች

EU legislation: Quality standards for the marketing of fresh fruit and vegetables http://www.cci-fed.org.lb/Library/Files/EU%20Legislation%20-%20Quality%20standards%20fresh%20fruit%20&%20vegetables.pdf

Filho, P. F., Ormond, J. G., and Paula, S. R. (undated) BRAZILIAN FRUIT PRODUCTION: IN SEARCH OF AN EXPORT MODEL http://www.bndes.gov.br/SiteBNDES/export/sites/default/bndes_en/Galerias/Download/studies/fruit.pdf

Food and Agriculture Organization (FAO) 2014. http://www.freshplaza.com/article/101367/World-production-of-tropical-fruit-expected-to-increase-in-2014

GeoHive (2015). http://www.geohive.com/charts/ag_vegetables.aspx

Guedes, Ítalo M. R. (2010). Greenhouse vegetable production in Brazil :Current status and research needs https://labexkorea.files.wordpress.com/2013/04/2-italo_presentation.pdf

Joosten, Frank, Dave Boselie, BekeleWolde and Lemma Desalegn (2011).Exporting Fruit and Vegetables from Ethiopia: Assessment of Development Potentials and Investment Options in the Export-oriented Fruit and Vegetable Sector.Ethiopia-Netherlands Horticulture Partnership Programme.

Nelson, Nicole (2013) Sustainable Horticultural Crop Production in Brazil. University of Minnesota, U.S.A. http://conservancy.umn.edu/bitstream/handle/11299/97239/Brazil%20(Nicole%20Nelson).pdf?sequence=1

Reporter (Dec 2013). IATA calls Ethiopian air cargo market the fourth fastest growing in the world. http://www.thereporterethiopia.com/index.php/news-

headlines/item/1401-iata-calls-ethiopian-air-cargo-market-the-fourth-fastest-growing-in-the-world

Rosa , 2011 http://www.fao.org/docrep/014/i1909e/i1909e00.pdf

Statista (2015). http://www.statista.com/statistics/264065/global-production-of-vegetables-by-type/

Temesgen, (2006). The role of the transport sector in Ethiopia''s economic development. Economic Focus. http://www.eeaecon.org/sites/default/files/publications/Economic%20Focus%20%20Vol%209%20No%204_0.pdf

Zuurbier, P. (2013) Market developments in the Brazilian horticulture sector: Identification of opportunities for Dutch companies and institutions. Wageningen http://www.greenporthollandinternational.nl/wp-content/uploads/Horticulture_Brazil-2013-final-version.pdf

ዕዝል (Annex)

# EU legislation: Quality standards for the marketing of fresh fruit and vegetables

### Introduction

The EU quality standards for fresh fruit and vegetables are legally binding requirements which aim to ensure that the products on the market are of acceptable quality and accurately labelled. Fresh fruit and vegetables may be offered for sale only if they comply with the specified standards and produce of unsatisfactory quality is kept off the market. The quality standards are fully harmonised in the EU.

Exporters from developing countries should be aware of the existing quality standards since the responsibility for ensuring that the produce which is sold or offered for sale complies with the EC marketing quality standards lies with every fresh fruit and vegetable trader. Where the EU standards do not exist, United Nations Economic Commission for Europe (UNECE) or Codex standards need to be consulted for internationally accepted product standards.

### Outline of the legislation

In the EU, marketing standards for quality of fruit and vegetables are laid down in **Regulation (EC) 2200/96.** The Regulation sets up a common organization of the market in fresh fruit and vegetables. The main requirement of marketing standards relate to *quality classification* and *information labelling* of the produce. The standards do not apply to processed or prepared fresh produce for instance packs of sliced carrots. The following table lists fruits and vegetables, which are subject to EC marketing standards.

| **Fresh fruits and vegetables subject to EC marketing standards (EC 2200/96)** | |
|---|---|
| Fruits | Almonds, apples, apricots, avocados, cherries, citrus fruit, grapes, hazelnuts, kiwis, melons, oranges, papayas, peaches and nectarines, pears, plums, strawberries, walnuts, watermelons |
| Vegetables | Artichokes, asparagus, aubergines, beans, Brussels sprouts, cabbage, carrots, cauliflower, celery, courgettes, cucumbers, garlic, lettuce, curly and escarole chicory, leeks, mushrooms (cultivated), onions, peas, spinach, sweet peppers, tomatoes, witloof chicory |

Specific standards apply to the different fruits and vegetables. For all of the above listed fruits and vegetables there are Community marketing standards laid down in Regulations for individual types of fruit and vegetable. It is advisable to always check the specific product category, as products, which do not comply with the standards are not permitted in the EU. In case product is not covered by an EU quality standard the UNECE standards apply.

➲ For more information on fruit and vegetable specific Community standards please refer to the website *Fresh Quality Guide* (includes also UNECE standards) in the external links section.

### *Quality standards requirements*

The person selling or offering produce for sale has the responsibility of ensuring that the product meets the minimum requirements of the Community marketing standards. For certain products additional requirements are required. All requirements must be always checked for individual fruit or vegetable. The following table provides a general overview of the standards.

| **Community Standards** | **Requirements** |
|---|---|
| Minimum requirements | Applicable for all produce<br>• Intact<br>• Sound (products rotting or deteriorating excluded)<br>• Clean (free of visible foreign matter)<br>• Free from pests, damage caused by pests<br>• Free of abnormal external moisture<br>• Free of any foreign smell and/or taste |

| | |
|---|---|
| Uniformity | • Products packed together must be of the same origin, variety or commercial class and quality |
| Commercial classification | ***'Extra' class***[1]<br>• *Produce of superior quality*[2]<br>• Free of any defects with the exception of slight superficial defects provided these do not affect the general appearance and its quality<br>• Maximum 5% by number of weight of the total produce does not satisfy the requirements of the class, but meets those of Class I or exceptionally is within the tolerances of that class |
| | ***Class I***<br>• *Good-quality*[2] (well shaped and coloured, free of marks)<br>• Slight defects may be allowed<br>• Maximum 10% by number of weight of the total produce does not satisfy the requirements of the class, but meets those of Class II or exceptionally is within the tolerances of that class |
| | ***Class II***<br>• *Sound marketable quality* produce (satisfies minimum requirements)<br>• May present defects (healed cracks)<br>• Maximum 10% by number of weight of the total produce does not satisfy the requirements of the class, nor the minimum requirements with the exception of products affected by rotting or other deterioration rendering them unfit for consumption |
| Additional requirements[3] | • Sizing[4]<br>• Tolerances<br>• Presentation[5]<br>• Marking[6]<br>• Official control mark[7] |
| Mixed consumer packs | Sales of packages of a net weight of three kilograms or less may contain mixes of different types of fresh fruit and vegetables provided that:<br>• Products are of uniform quality; they must be in identical quality class<br>• Mix is not such as to mislead the consumer |
| Miniatures | Produce marketed in the form of miniature produce (e.g. cauliflowers, courgettes, aubergines)<br>• Size requirement does not apply |

[1] Applies only to selected produce including apples, apricots, avocados, cherries, kiwifruit, lemons, mandarins, nectarines, oranges, peaches, pears, plums, clementines, tangerines, strawberries, grapes, artichokes, asparagus, beans, carrots, cauliflower, chicory, cucumbers, garlic, mushrooms, tomatoes.
[2] Quality characteristic of the variety or commercial type.
[3] Additional requirements are always specified for individual variety of fruits and vegetables; not all of them are always required for all produce.
[4] For instance by weight, length, diameter.
[5] Uniformity and packaging requirements are often specified in the regulations for specific products.
[6] See below labelling requirements.
[7] This requirement is optional.

➲ For more information on Regulation (EC) 2200/96 fresh fruit and vegetables standards and Regulation (EC) 48/2003 on mixes in the same package please refer to the external links.

***Labelling***
The marking information required by the quality standards must be shown legibly in an obvious position on one side of the packaging either printed directly onto package or on a label which is an integral part of or firmly fixed to the package. For products shipped in bulk, a document accompanying the goods should be placed on obvious position inside the means of transport. The minimum requirement for marketing standards applies to all fresh fruits and vegetables. However, additional requirements are very common for the majority of produce.

| Community standard | Labelling requirement |
|---|---|
| Minimum requirement | Each container or display must be clearly marked with the correct information regarding:<br>• Variety<br>• Origin<br>• Quality class<br>• Net weight[1] |
| Original packaging | Packages which constitute a sales unit to the final user or consumer at the point of purchase<br>• Minimum requirements apply<br>• Must include identification information of packer or dispatcher[1] in wording *packaged by*[2] |
| Pre-packs | Offered for sale in pre-packs<br>• Minimum requirements apply<br>• Net weight<br>• Identification of packer and dispatcher[2] in wording *packaged by*[2]<br>• Identification of seller in wording *packaged for*[2] |
| Mixed consumer packs | • Variety of each fruit or vegetable in the pack<br>• Origin of all produce in the pack<br>• Quality class<br>• Identification of packer and dispatcher in wording *packaged by*[2] |
| Miniatures | • *Mini* or *baby* or other term for miniature must be indicated |

[1] Only for pre-packaged products; however, does not apply for pre-packaged products sold by number.
[2] Name and address or officially issued code.

➲ For more information on Regulation (EC) 1135/2003 on provisions concerning sizing, presentation and labelling (includes miniature) please refer to the external link.

➲ For more information on Regulation (EC) 48/2003 on mixes of different types of fresh fruit and vegetables in the same sales packege please refer to the external link.

***Certificate of Conformity***

According to Commission **Regulation (EC) 1148/2001** on checks on conformity to the marketing standards, fresh fruit and vegetables from outside the EU require a *Certificate of Conformity* (sample in Annex I of the Regulation) before they are allowed into the EU. Products intended for processing require a *Certificate of Industrial Use* (sample in Annex II).

**Exempt from the EC standards requiring Certificate of industrial Use.**

The products intended for processing are not required to comply with marketing standards. Such products must be suitably labelled and accompanied by a processing certificate stating the end-use. The packaging of products intended for processing must be clearly with the words "*intended for processing*" or other equivalent wording. In case of bulk transport this indication must be given in a document accompanying the goods or on a notice placed in an obvious place inside the means of transport.

➲ For more information on Regulation (EC) 1148/2001 please refer to the external link.

Source: EU legislation: Quality standards for the marketing of fresh fruit and vegetables